


Scanned by CamScanner

@BOOKALEM




Info

t.me/BookAlem

Invite Link

@BOOKALEM

# አሁንም ‹ከስኬታማ ወንድ ጀርባ ጠንካራ ሴት አለች› ወንዶች ከፍቅረኛቸው ሴት የሚያገኙዋቸው ጥቅማ ጥቅሞች

‹ከወንድ ልጅ መረጃ ይልቅ
የሴት ልጅ ግምት ማመን ይሻለኛል›

ስታንሊ ባልድዊን

ብዙ ወንዶች ‹የፍቅር ጓደኛ› ሲባል ቀድሞ ድቅን የሚልብን ‹የግብረ ስጋ ግንኙነት፣ የተቃራኒ ፆታ ግንኙነት፣ ፆታዊ ተራክቦ፣ እንሰሳ መጋፈፍ፣ ፍትወተ ስጋ…› የሚሉ በርካታ ስያሜዎች የተሰጠውና በአጭሩ ‹ወሲብ› ተብሎ የሚገለፀው ተወዳጁና ዝነኛው የተፈጥሮ ፀጋ ነው፡፡ በአገራችን ብዙ ጊዜ በአደባባይ ስሙና ጥቅሙ የማይወሳው ‹ወሲብ› ወይም ደግሞ በእኔ ቋንቋ ‹ጣፋጭ የፍቅር ጭማቂ› ከእውነተኛ የፍቅር ግንኙነት የሚወለድ ክቡር የተፈጥሮ ስጦታ ነው ቢባል ያንስበታል እንጂ አይበዛበትም፡፡

ከልብ አፍቅራችሁ… ከእውነተኛ ግንኙነት ውስጥ ጣፋጭ የፍቅር ጭማቂ የጠጣችሁ ሁሉ በአገላለፁ እንደምትስማሙ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

አልጠራጠርም፡፡ ምንም እንኳን ይህ ‹ወሲብ› የተባለው ጣፋጭ የፍቅር ጭማቂ ለወንድና ለሴት የፍቅር ግንኙነት ጠንካራ መሰረት መሆኑ ባይካድም ወንዶች ከሴት ፍቅረኞቻቸው የሚያገኙት ብቸኛ ጥቅም ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡በዓለማችን ብዙ ወንዶች በሴት ፍቅረኞቻቸው ምክንያት የአስገራሚ ፈጠራዎችና ስኬቶች ባለቤት ሆነዋል፡፡ ሴቶች ለብዙ ወንዶች ሚሊየነርና ቢሊየነር መሆን ምክንያት ናቸው፡፡ በርካታ ወንዶች በሴት ፍቅረኞቻቸው አገዛ ወደ ከፍተኛ የሃብት፣ የዝናና የስልጣን ጣሪያ ወጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ሴቶች በውበታቸው፣ በእውቀታቸው፣ በተሰጥኦዋቸው፣ በፍቅራቸው፣ በተፈጥሯቸው... የብዙ ወንዶች የህይወት ጣዕምና የመኖር ተስፋ ናቸው፡፡ በእርግጥ ለአንዳንድ ወንዶች ደግሞ ከህይወት ለመገለል ምክንያት የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎችም አይታጡም፡፡

## ፍቅረኛ ሴት... ለዝና፣ ለፈጠራና ለስኬት

ሰርተውና ፈጥረው የገነኑ... ባለሃብት የሆኑ ስኬታማ ሰዎችን ማድነቅና ማክበር ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ከአድናቆትና ከክብር ውስጥ ደግሞ መውደድና ማፍቀር ሊወለድ ይችላል፡፡ ስለዚህ ሴቶች ሃብታም፣ ዝነኛና ስኬታማ በሆኑ ወንዶች መማረካቸው አይደንቅም፡፡ ወንዶችም የተመሳሳይ ስኬት ባለቤት በሆኑ ሴቶች ይማረካሉ፡፡ ስለሆነም ብዙ ወንዶች የሚወዷቸውን ሴቶች ትኩረት ለመሳብ ከዚያም አልፎ የግላቸው ለማድረግ ሲሉ ይሰራሉ፣ ይፈጥራሉ፤ ሃብታም፣ ዝነኛና ስኬታማ ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶች ለሃብት፣ ለዝና እና ለስኬት ምክንያት የሆኗቸውን ሴቶች በማግባት ተጨማሪ ስኬት ይጎናፀፋሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ለስኬት ያበቋቸውን አመስግነው ሌሎች ዕድለኞችን ያገባሉ፡፡

ባፈቀሯቸው ሴቶች ተነሳስተው እንዲሁም ያፈቀሯቸውን

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ሴቶች ለመማረክ ሲሉ ትላልቅ ስኬቶች የተጎናፀፉ፣ የፈጠሩ፣ የሰሩ፣ የከበሩ፣ የገነኑ… በሴቶች ምክንያት የህይወታቸውን አቅጣጫ ለውጠው የተለወጡ ወንዶች እጅግ በርካታ ናቸው። በሴቶች ምክንያት ከተሰሩ ትላልቅ ሥራዎችና ፈጠራዎች እንዲሁም ስኬታማ ከሆኑ ወንዶች የተወሰኑትን እንመልከት።

## ከፌስቡክ ጀርባ

ወንዶች ከፈጠሯቸው በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጀርባ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሴቶች አሉ። በአሁኑ ሰዓት ከአንድ ቢሊየን በላይ ተጠቃሚዎች ያሉትና ለብዙዎች መፋቀርና መጋባት ምክንያት እየሆነ ያለው ‹ፌስቡክ› የተፈጠረው እ.ኤ.አ ፌብሩዋሪ 4 ቀን 2004 በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነው። ፌስቡክን በመፍጠር በወጣትነቱ ቢሊየነር የሆነው ማርክ ዙከርበርግ ይህንን የዓለም ህዝብ መገናኛ የሆነውን ‹ፌስቡክ› የፈጠረው የሚወዳትን ልጅ ለመማረክና በጓደኞቹ ተቀባይነት ለማግኘት ሲል ነበር።

ማርክ ዙከርበርግ ይህን የዓለማችን ትልቅ የህዝቦች መገናኛና ሚዲያ የሆነውን ‹ፌስቡክ› እንዲፈጥር ልቡ ውስጥ ገብታ ከፍተኛ የማነሳሳት ሚና የተጫወተችው የቻይና እና የቬትናም ዝርያ ያላት ፕሪሲላ ቻን የተባለች ወጣት ነች።

ማርክ ለዚህ ትልቅ ሃብትና ስኬት ካበቃችው ፕሪሲላ ቻን ጋር እ.ኤ.አ ሜይ 19 ቀን 2012 ቀለበት አሰሯል። ለፍቅሯና ለውለታዋም በሳምንት አንድ ቀን፤ ከቤት ውጪ የመቶ ደቂቃዎች ጊዜ ሙሉ ትኩረቱን እርሷ ላይ በማድረግ ከእርሷ ጋር በፍቅር ለመዝናናት ውል ተፈራርሟል። ማርክ ዙከርበርግና ፕሪሲላ ቻን በተፈራረሙት በዚህ የመቶ ደቂቃ የፍቅር ጊዜ ስምምነት ላይ ከእርሷ ጋር ከመጫወት ውጪ ምንም ነገር አያደርግም - የፌስቡክ ገፁንም ጭምር ቼክ አያደርግም።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## ከሞና ሊዛ ጀርባ

ለብዙ የኪነ ጥበብ ፈጠራዎች ምክንያት በመሆን ትልቅ ድርሻ የሚይዘው ያለ ጥርጥር የሴቶች ፍቅር ነው። በተለይ ወንዶች ከሚሰሯቸው የኪነ ጥበብ ሥራዎች ጀርባ እውነተኛ ወይም ገፀ ባህርይ ሴቶች አሉ።

- እጅግ ታዋቂ የሆነው… ብዙ የተሣፈለት፣ የተወራለት፣ የተዘመረለትና በከፍተኛ ሁኔታ የተጎበኘው የዓለማችን ቁጥር አንድ ስዕል ‹ሞና ሊዛ› ነው። ይህንን የፕላኔታችን ድንቅ ስዕል ለማጠናቀቅ ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ ሦስት ዓመታት (ከ1503 እስከ 1506 እ.ኤ.አ) ወስዶበታል። ከዚህ ዝነኛ የ‹ሞና ሊዛ› ስዕል ጀርባ ያለችው ሴት ሊሳ ግራርዲኒ ነች።
  ይህች ሴት በወቅቱ ባለትዳር ብትሆንም ሌዮናርዶ ዳ ቪንቺ በድብቅ በፍቅሯ ይሰቃይ እንደነበር ይነገራል።

## ከሙዚቃ ጀርባ

- አብዛኞቹ ወንዶች የሚያዜሟቸው ዜማዎች የሴቶችን ውበትና ፍቅር የሚያወድሱ ናቸው። ካላመናችሁኝ ሬዲዮ ክፈቱ። ወንዶች ለሚሰሯቸው ሙዚቃዎች ሴቶች መነሻ መሆን ከጀመሩ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል። ቢትሆቨን ከፍተኛ ዝና ከተጎናፀፈባቸው ስራዎቹ መካከል አንዱ እ.ኤ.አ በ1800ዎቹ ለጆሮ የበቃው “Moonlight Sonata” የተሰኘው ሙዚቃው ነው። ቢትሆቨን ‹ጉሊዬታ ጉችያርዲ› ከምትባል ቆንጆ ሴት ጋር በፍቅር ባይወድቅ ኖሮ ይህ አስገራሚ ሙዚቃ አይፈጠርም ነበር።

- ‹ዘ ቢትልስ› የተባለው የእንግሊዛዊያን የሙዚቃ ባንድ እስካሁን ድረስ የምድራችን ቁጥር 1 የሙዚቃ ባንድ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

የሙዚቃ ቡድን በሴት ፍቅር ላይ የተመሰረቱ በርካታ ተወዳጅ ዘፈኖችን ለጆሮ በማብቃት ተወዳጅ መሆን የቻለ ሲሆን የቡድኑ መሪ ድምፃዊ የነበረው ጆን ሌነን ለተጫወተው "Woman" የተሰኘው ታሪካዊ ዘፈኑ መነሻ የሆነችው ባለቤቱ ዮኮ ኦኖ ነች።

- በሙዚቃው ዓለም በከፍተኛ ሽያጭ እስካሁን ድረስ ቁጥር አንድ ደረጃ ይዞ የሚገኘው ሙዚቃ "Candle In The Wind" ነው። ኤልተን ጆን ይህንን ሙዚቃ በ1973 እ.ኤ.አ የሰራው በዝነኛዋ አሜሪካዊት ተዋናይ ማርሊን ሞንሮ ፍቅር ነው። (በኋላ የልዕልት ዲያናን ህልፈት ተከትሎ በድጋሚ እ.ኤ.አ በ1997 በአዲስ መልክ ተጫውቶታል)

- የጆን ሜየር "Your Body Is A Wonderland" በተዋናይት ጄኒፈር ላቭ ሂዊት እንዲሁም የፕሪንስ "Cindy C" በሱፐርሞዴል/ ተዋናይት ሲንዲ ክራውፎርድ ፍቅር መነሻነት ከተሰሩ በርካታ የፍቅር ዜማዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

## ከተዋንያን ጀርባ

- ሊያም ኒሰን ዓለም የሚያደንቀው፣ እንግሊዝና አየርላንድ የሚመኩበት ዝነኛ የፊልም ተዋናይ ነው። በአሁኑ ሰዓት በፊልም ተዋናይነቱ ሆሊዉድ ውስጥ ተፈላጊ ከሆኑት አንዱ የሆነው ሊያም ኒሰን በታዳጊነቱ በሴት ፍቅር ባይከንፍ ኖሮ ምን ዓይነት ሰው ይሆን ነበር ብሎ መተንበይ ራሱ ከባድ ነው። ምስጋና ለዚያች አየርላንዳዊት ሴት ይሁንና ሊያም ት/ቤት ውስጥ በነበረው የቴአትር ቡድን ውስጥ ገብቶ መተወን የጀመረው በፍቅሯ ከመክነፉ የተነሳ ነበር። የቴአትር ቡድኑ አባል የሆነው የመተወን ፍላጎት ኖሮት ሳይሆን ከወደዳት ሴት ... ብቻ ነበር።

James Bond... በህይወት ያለ እውነተኛ ሰው እስኪመስለን ድረስ የምናውቀው ገናና ገፀ ባህርይ ነው። እስካሁን ድረስ በዚህ ገፀ ባህርይ ላይ የተመሰረቱ 23 ፊልሞች ተሰርተው ከ6 ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ በማስገኘት በሲኒማ ታሪክ ውስጥ ሰፋ ያለ ምዕራፍ ይዘዋል። በJames Bond ፊልሞች ላይ 007 ሆኖ መተወን የብዙ ተዋንያን ምኞት ቢሆንም ምኞታቸው የሚሳካላቸው ግን እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ይህን ካሳኩ ጥቂቶች መካከል አንዱ ደግሞ ጆርጅ ላዜንባይ ነው።

ላዜንባይ በጄምስ ቦንድ ፊልም 007 ሆኖ የመተወን ዕድል ያገኘው በችሎታ፣ በልምድና በዕውቀት ሳይሆን በሴት ልጅ ፍቅር ብቻ ነው።

በሴት ፍቅር ብቻ እንዴት?

የመጀመሪያው የጀምስ ቦንድ ፊልም የሆነው "Dr. No" እንደወጣ ጆርጅ ላዜንባይ የሚወዳትን ሴት ለመጋበዝ ወደ ሲኒማ ቤት ገባ። የፊልሙ መሪ ተዋናይ ሾን ኮነሪ ነበር። ጆርጅ ላዜንባይ በፊልሙ አስደስቶ የግሉ ሊያደርጋት ይሻት የገባው ልጅ በፊልሙ መደሰት ብቻ ሳይሆን በሾን ኮነሪ የትወና ብቃት ተማረከች። ፊልሙ አልቆ ሲወጡ ሁኔታው ጆርጅ ከጠበቀው ውጪ ሆነበት። ልጅቷ ፊልሙን የጋበዛትን ጆርጅን ትታ በሾን ኮነሪ ፍቅር ወደቀች። በሁኔታው በጣም የተናደደው ጆርጅ በህይወቱ አስቦትና አልሞት የማያውቀውን ነገር ለማድረግ አሰበ... ጀምስ ቦንድ ሆኖ በመስራት እርሷን ለመማረክ ወሰነ።

የጀምስ ቦንድ ፊልም ፕሮዲዩሰሮች ጀምስ ቦንድ ሆኖ የሚተውን አዲስ ተዋናይ እንደሚፈልጉ ማስታወቂያ እስኪያወጡ ድረስ ሲጠባበቅ የቆየው ጆርጅ አጋጣሚውን እንዳገኘ በ "Dr. No" ፊልም ላይ ሾን ኮነሪ የለበሰውን ሙሉ ልብስና ያሰረውን ሮሌክስ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሰዓት በመግባት እንዲሁም ሾን ወደተስተካከለበት ፀጉር ቤት በመሄድ ልክ እንደ እርሱ ተስተካክሎ ወደ ጄምስ ቦንድ ፕሮዲዩሰሮች ስቱዲዮ ቀጥ ብሎ ገባ፡፡ አለባበሱና ስታይሉ ረድቶት የስቱዲዮውን ጥበቃና ፀሃፊ በቀላሉ አልፎ ከፕሮዲሰሮቹ ጋር ተገናኘ፡፡ በጄምስ ቦንድ አለባበስና ስታይሉ የተማረኩት ፕሮዲዩሰሮቹ... ጆርጅ ከሆንግ ኮንግ እስከ ጀርመን በተለያዩ አገሮች እየተዘዋወረ በብዙ ፊልሞች ላይ መስራቱን ዋሽቶ ሲነግራቸው አምነው አሳለፉት፡፡

ጆርጅ ላዜንባይ ጄምስ ቦንድን ሆኖ ለመተወን ውል ጨርሶ፣ ስክሪፕት ተረክቦ ፊልሙን ዳይሬክት ከሚያደርገው ከፒተር ሃንት ጋር ሲገናኝ የሚይዘውና የሚጨብጠው አጣ፡፡ ምክንያቱም ሰውየው ፍቅር እንጂ ትሎታም ሆነ ልምድ አልነበረውም፡፡ ነገር ግን የፍቅር አምላክ ይሁን የፍላጎቱ ብዛት ረድቶት ዳይሬክተሩና ፕሮዲዩሰሮቹ ዕድል ሊሰጡት ተስማሙ፡፡ ጆርጅ የወደዳትን ልጅ ለመማረክ... ያንን ሴቷን ያሸፈተውን የሾን ኮንሪ ትወና እያሰበ 007 ጄምስ ቦንድ ሆኖ ተወነ፡፡

ፊልሙ በ8 ሚሊዮን ዶላር በጀት ተሰርቶ... "On Her Majesty's Secret Service" በሚል ስያሜ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 18 ቀን 1969 ላይ አዲሱ ጄምስ ቦንድ ጆርጅ ላዜንባይን ይዞ ለዕይታ በቃ፡፡ ጆርጅ ሲኒማ ቤት ይዟት ገብቶ በሾን ኮንሪ ልቧ የሸፈተችውን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ፊልሙን ተመለከቱትና በአጠቃላይ 82 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አስገኘ፡፡

በሚያስገርም ሁኔታ ያለ ምንም ልምድ በአንድ ጊዜ ጄምስ ቦንድ ፊልም ላይ የተወነው ጆርጅ ባልጠበቀውና ባልተለማመደው ሁኔታ በአንዴ የዝና ጣሪያ ላይ ተሰቀለ፡፡ እናም ሴቶችን ለመማረክ ጥረት ማድረግ ሳይጠበቅበት የጄምስ ቦንድ አድናቂ ሴቶች ቤቱ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ጆርጅ ላዜንባይ ባፈቀራት ሴት አማካይነት ተገፋፍቶ በዓለም ሲኒማ ኢንዱስትሪ ላይ ትልቅ ታሪክ ባላቸው የጀምስ ቦንድ ተከታታይ ፊልሞች ላይ የራሱን ምዕራፍ ሊይዝ ችሏል፡፡

## ከላስ ቬጋስ ጀርባ

ላስ ቬጋስ ከዓለማችን እጅግ በጣም ውብ ከተሞች ተርታ የምትመደብ... የዓለማችን አብዛኛው ህዝብ ሊያያትና ሊዝናናባት የሚመኛት... የብዙ ሰው የቀን ህልም ከተማ ነች፡፡ ፍቅረኛሞች ለመጋባት፣ ሙሽሮች ለጫጉላ ሽርሽር አብልጠው የሚመርጧት ... የፍቅር ገነት ነች፡፡ ስለሆነም በቀን 150 ጥንዶች ጋብቻቸውን ለመፈፀም እንዲሁም በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሙሽሮች የማይረሳ የጫጉላ ሽርሽር ጊዜ ለማሳለፍ ወደ ላስ ቬጋስ ይጎርፋሉ፡፡

አሜሪካ ከሚገኙት 20 ትላልቅ ሆቴሎች መካከል 17ቱን የያዘችው ቬጋስ ጋብቻቸውን ለመፈፀም በየቀኑ ለሚጎበኙዋት ፍቅረኛሞች በ15 ደቂቃ ውስጥ የጋብቻ ስርዓቱን ማጠናቀቅ የሚችሉና 24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ 500 የጋብቻ ቻፔሎች (ቤተ መቅደሶች) አዘጋጅታለች፡፡

ላስ ቬጋስ ውስጥ ጋብቻ ለመፈፀም ከ16 ዓመት በላይ መሆንና 50 ዶላር መያዝ ብቻ በቂ ነው፡፡ ላስ ቬጋስ ተጋብተው ወይም ሌላ ቦታ ተጋብተው ለጫጉላ ሽርሽር ወደ ላስ ቬጋስ መጥተው በቁማር አሊያም በሌላ ጉዳይ አምርረው ለሚጣሉ ደግሞ ከላስ ቬጋስ ትንሽ ወጣ ብላ የምትገኘው ‹ሪኖ› ከተማ ፈጣን የፍቺ አገልግሎት ትሰጣለች፡፡

ዛሬ በውበቷና በአዝናኝነቷ እንዲሁም ለፍቅረኛሞችና ለሙሽሮች ባላት ምቹት በዓመት እስከ 40 ሚሊዮን ጎብኚዎችን የምትስበው ላስ ቬጋስ ለመፈጠሯ ምክንያት አንዲት ቆንጆ ሴት

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ነች። ጊዜው እ.ኤ.አ በ1945 ነው... ቤንጃሚን ‹ባግሲ› ሲጌል ከፍቅረኛው ጋር በመኪና ከሎስ አንጀለስ ተነስተው የኔቫዳን ግዛት አቋርጠው በመንገዝ ላይ እያሉ ድንገት በመካከላቸው ጭቅጭቅ ይነሳል። ጭቅጭቁ ሲከር የባግሲ ፍቅረኛ መኪናውን እንዲያቆምላት ኮስተር ብላ ደጋግማ ትነግረዋለች። ባግሲ በተባለው መሰረት በኔቫዳ በረሃ ላይ መኪናውን ያቆማል። ፍቅረኛው በንዴት ከመኪናው ወርዳ በእግሯ ጉዞ ትጀምራለች። ባግሲ ፍቅረኛውን ለምኖ ለመመለስ ከመኪናው ሲወርድ የሆነ ነገር እንደ መብረቅ ይመታዋል። በበረሃው ውበትና በመጣለት ሃሳብ ፈዝዞ ይቀራል።

ከአንድ ዓመት በኋላ ማለትም በ1946 በወቅቱ የዓለማችን ቁጥር አንድ የተቀናጣና ምቹ እንዲሁም የላስ ቬጋስ የመጀመሪያው የቁማር ፓራዳይዝ የሆነው ‹ፍላሚንጎ› ሆቴል ተከፈተ። ቤንጃሚን ‹ባግሲ› ሲጌል ሆቴሉን የገነባው የሆሊዉድ ሃብታም ጓደኞቹን በማሳመን ቢሆንም የግንባታውን ሃሳብ ያገኘው ግን ከፍቅረኛው ነው። ስለሆነም የፍቅረኛው እግሮች ልክ እንደ ፍላሚንጎ ወፎች ረዣዥም ስለነበሩ ሆቴሉን ‹ፍላሚንጎ› ብሎ ሊሰይመው ችሏል። ከዚህ ታሪክ የምትማረው ቁምነገር ምንድነው?
ሴቶች ፍቅራቸው ቀርቶ ጭቅጭቃቸውም ጭምር ለትልቅ ስኬት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ካልክ ልክ ነህ።

## ታጅ ማሃል - በታላቅ ጥበብ ለፍቅር የተሰራ ሃውልት

ህንዶች የሚመኩበት... የዓለም ጎብኚዎች የሚጎርፉበት... የተባበሩት መንግስታት ‹የዓለም ቅርስ› በሚል የሚንከባከበውና በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ የሚንቆለጳጰስ ህንፃ ነው - ታጅ ማሃል። ሲቢያ፣ ቻይና፣ ባንግላዲሽ፣ ማሃራሽትራ እና አሜሪካ በከተሞቻቸው አስመስለው በመገንባት ለዚህ አስገራሚ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ህንፃ ያላቸውን አድናቆት ገልፀዋል።

ፍቅረኛሞች ከተለያዩ አገሮች ወደ ‹ታጅ ማሃል› በመሄድ ‹ፍቅር እስከ መቃብር› እየተባባሉ የፍቅር ቃል ኪዳናቸውን ያድሳሉ… ብዙ ወንዶች በዚህ የተቀደሰ የፍቅር ስፍራ እየተንበረከኩ የእግቢኝ ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ።

ንጉስ ሻህ ጃሃን እና ንግስት ሙምታዝ ማሃል እጅግ በጣም የሚፋቀሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ንግስት ሙምታዝ ማሃል 14ኛ ልጃቸውን ሲወልዱ በድንገት ህይወታቸው አለፈ። ንጉስ ሻህ ጃሃን በባለቤታቸው ሞት ሃዘን ክፉኛ ተጎዱ።

አንድ ዓመት ያህል በሃዘን ካሳለሱ በኋላም ለባለቤታቸው ለነበራቸው ጥልቅ ፍቅር ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በመላው ዓለም አምሳያና ተወዳዳሪ የሌለው የመታሰቢያ ህንፃ ለማስገንባት አቀዱ፡ ፡ ከህንድ፣ ከቱርክና ከኢራን እሉ የሚባሉ የስነ ህንፃ ጠበብትን በማሰባሰብም በ1632 ግንባታውን አስጀመሩ።

ከ19 የግንባታ ዓመታት በኋላም ንጉስ ሻህ ጃሃን በፍቅር… በልባቸው ያቀዱት ህንፃ ተጠናቆ… አምሮ… ተውቦ ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ሲያዩት በደስታ እነቡ።

እንዲህ ሲሉም ተናገሩ…

‹አጥፍቶ የተፀፀተ ሰው ወደዚህ ሲመጣ፤
ይቅርታ አግኝቶ ከፀፀት ነፃ ይውጣ።
ሃጢያት የሰራ ሰው እግሩ እዚህ ሲረግጥ፤
ሃጢያቱ ሁሉ ጠፍቶ ነፅቶ ይመለስ›

ንጉስ ሻህ ጃሃን ለባለቤታቸው ፍቅርና ማስታወሻ ‹ታጅ ማሃል›ን አስገንብተው ከጨረሱ በኋላ ብዙም በህይወት አልቆዩም፤ እዚያው ‹ታጅ ማሃል› በሚገኘው መካነ መቃብር ከባለቤታቸው ጎን አረፉ።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሻህ ጃሃንን በፍቅር አነሳስተው ይህን የዓለማችን ድንቅ የፍቅር ሐውልት ይሰራ ዘንድ ምክንያት ለሆኑት ለንግስት ሙምታዝ ማሃል ምስጋና በማቅረብ ወደ ሌሎች ነጥቦች እንሻገር።

## ከፍቅረኛ ሴት የሚገኙ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች

- የማንኛውም የኪነ ጥበብ አሲያም የፈጠራ ሰው ከሆንክ ሴት ፍቅረኛ ልክ ከላይ እንደተዘረዘሩት ዓይነት ትላልቅ ስራዎች ለመስራት ምክንያት ትሆንሃለች። ፍቅረኛ የምታስፈልግህ ግን ታሪክ ሰሪ ለመሆን ብቻ አይደለም።

- ሲነጋ ‹ብራቮ ነጋ› ብለህ በደስታ ከአልጋህ ተስፈንጥረህ እንድትነሳ ታደርግሃለች - ፍቅረኛህ። እዚያ ላይ ብቻ አያበቃም። ‹እንደምን አደርሽልኝ የእኔ ቆንጆ› ብለህ ቴክስት ካደረግክ በኋላ የተስተካከለና ማራኪ የሰውነት ቅርፅ እንዲኖርህ ጂም እንድትገባ አሲያም ባለህበት ከሻወር በፊት ዱብ ዱብ እንድትል ምክንያት ልትሆንህ ትችላለች።

- ፍቅረኛ ካለችህ ቀጣዩ ዕቅድህ እሷን ማግባት ይሆናል። ስለሆነም በጋራ የምትመሰርቱት ቤተሰብ ሃላፊነት መሸከም የምትችል መሆንህን ለማሳመን ገቢህን ከፍ ለ ማድረግ ጥረት ታደርጋለህ። ስለዚህ በተሻለ ገቢ የተሻለ ህይወት ለመኖር እንድታስብ አነሳሳችህ ማለት ነው።

- ሲኒማ ቤት ለመግባትስ ቢሆን ፍቅረኛ አያምርህም እንዴ? ፍቅረኛ ያሉዋቸው ወንዶች ፍቅረኞቻቸውን አቅፈው ‹እንቁልልጩ› ከሚሉባቸው ስፍራዎች አንዱ ሲኒማ ቤት ነው። ‹እንቁልልጩ› በሚሉት ወንዶች ተከበህ ብቻህን የፍቅር ፊልሞች ከማየትም ትገላገላለህ።

- በሻማ ብርሃን ተውቦ፣ በለስላሳ ሙዚቃ ታጅቦ ጣፋጭ ምግብ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

በሚበላበትና የፈረንሳይ ወይን በሚጠጣበት ደስ የሚል ሬስቶራንት ከተመገብክ ስንት ጊዜ ሆነህ? ከወንድ ጓደኞችህ ጋርም ሆነ ለብቻህ የማትገባበት ቦታ ነው፡፡ ምንም እንኳን በእንደዚህ ዓይነት ውድ ሬስቶራንቶች ከሴት ጋር ስትመገብ ከፋዩ አንተ ብትሆንም... እመነኝ መፈጠርህን ትወደዋለህ፡፡

- የምትወዳት ፍቅረኛ ስትኖርህ እርሷን ሰርፕራይዝ ለማድረግና ለማስደሰት የምታደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ የእውነተኛ ደስታህ ምንጭ ይሆናል፡፡ ፍቅረኞች ያሏቸው ወንዶች የፍቅረኞቻቸው ልደት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ መከበሩ እንደሚያስከፋቸው ታውቃለህ? ‹ምነው ልደቷ በየወሩ በተከበረና በየወሩ ሰርፕራይዝ እያደረግኳት በተደሰትኩ› ይላሉ፡፡ ደስ የሚለው ግን አዲስ ዓመት፣ የፍቅረኛሞች ቀን (ቫለንታይንስ ዴይ)፣ የተለያዩ በርካታ የሃይማኖት በዓላት አሉላቸው፡፡ አንዳንዶቹ እንደ ቦነስ ሜይ ዴይ፣ የአድዋ ድል ቀን፣ የአርበኞች ቀንና ግንቦት 20ን መጨመር ያምራቸዋል፡፡

‹አይ ብርሃኔ አሁንስ አጋነንከው› ልትል ትችላለህ... ግን ደግሞ ስታፌቅር ‹ለካ እውነቱን ነው› ትላለህ፡፡

- የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች የምርጫ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ባለቤቶቻቸውን ከጎናቸው የሚያደርጉት ለምን ይመስልሃል? ‹ክብር... ተቀባይነት ለማግኘትና እምነት ለማሳደር› ካልክ አልተሳሳትክም፡፡ ባለትዳር የሆነ ወንድ ይከበራል፡፡ ለሃላፊነቶች ይታጫል፤ ይመረጣል፡፡ በማህበረሰብ ተቀባይነት ያገኛል፡፡ በዚህ ብቻ አያበቃም... ብዙ አገሮች ላገቡ ሰዎች የተሻለ የባንክ ብድር አገልግሎትና የግብር አከፋፈል ስርዓትም አላቸው፡፡

- ያገቡ ሰዎች በመኪና የመገጨት፣ በጭንቀት የመሰቃየትና በተለያዩ ህመሞች የመጠቃት ዕድላቸው ካላገቡ ሰዎች ጋር

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሲነፃፀር እጅግ በጣም አነስተኛ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ ያገቡ ሰዎች ካላገቡት በበለጠ ጤነኞችና ደስተኞች እንደሆኑም እንደዚያው፡፡

- የፖሊስ ፕሮግራም ዜናዎችን የምትከታተል ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ በአስገድዶ መድፈር ተከሰው ዘብጢያ የሚወርዱት ፍቅረኛ የሌላቸው (ያላገቡ) ወንዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ፍቅረኛ መያዝ (ማግባት) በአስገድዶ መድፈር ተዋርዶ ወህኒ ቤት ከመውረድም ያድንሃል፡፡
- ሌላው የወንድ ልጅ ትልቁ የደስታ ጊዜ የልጅ አባት ሲሆን ነው ይባላል፡፡ የልጅ አባት በማድረግ የዕድሜ ልክ ደስታ የምትሰጥህም ሴት ነች፡፡
- ሴቶች ባይኖሩ ኖሮ እኛ ወንዶች የሙሉ ጊዜ ሥራችን ጦርነት ብቻ ይሆን ነበር፡፡ ዓለማችንም የጦርነት አውድማ ትሆን ነበር፡፡ የሮማው ንጉስ ክላውዲዮስ ሁለተኛ የአገሩ ወንዶች ወደ ጦርነት አንዘምትም ሲሉት እስቦ አሰላስሎ የደረሰበት መፍትሄ ወንዶች ከሴቶች ጋር የፍቅርና የትዳር ህይወት እንዳይኖራቸው መከልከል ነበር፡፡ ንጉስ ክላውዲዮስ ፍቅርና ትዳርን የሚከለክል ህግ ያወጣበት ምክንያት ወንዶች ወደ ጦርነት እንዳይዘምቱ የሚያደርጋቸው የሴቶች ፍቅር ነው በሚል ነበር፡፡ ትክክል ነው፡፡ ህይወት ጣፋጭና አጓጊ እንድትሆን ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት ሴቶች ናቸው፡፡ ወንዶች በሴቶችና በልጆች ፍቅር ይንበረከካሉ፡፡ ንጉስ ክላውዲዮስ ፍቅርና ጋብቻን በሞት ቅጣት ደንግጎ ቢከለክልም ወንዶች ሴቶችን ከማፍቀርና በድብቅ ከማግባት አልተቆጠቡም፡፡ ቂስ ቫሌንታይን ለፍቅረኛሞች ቀን(ቫሌንታይንስ ዴይ)መታሰቢያ ሊሆኑ የቻሉትም በዚህ ንጉስ ዘመን በድብቅ ፍቅረኛሞችን ሲያጋቡ ተይዘው በመገደላቸው ነው፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

- በአጠቃላይ ሴት ልጅ ውበት ነች... ፍቅር ነች... ስኬት ነች... ጣፋጭ ነች... ህይወት ነች... ለኑሮህ እጅግ እጅግ በጣም ታስፈልግሃለች:: ጥያቄው ለስኬትህና ለደስተኛ ኑሮህ ምክንያት የምትሆን ሴት እንዴት ታገኛለህ? ነው:: የዚህ መፅሃፍ ዓላማ ለዚህ ትልቅ ጥያቄ መልስ መስጠት ነው::

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

“በጋለ ምጣድ ላይ እጅህን ለአንድ ደቂቃ ስታስቀምጥ አንዷ ደቂቃ አንድ ሰዓት ትሆንብሃለች። ከቆንጆ ሴት ጋር ለአንድ ሰዓት ስትቀመጥ ግን አንድ ደቂቃ የተቀመጥክ አይመስልህም። ሬላቲቪቲ ማለት ያ ነው”

አልበርት አንስታይን

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



# ሴቶችን የማወቅ... የመማረክ ሳይንሳዊ ጥበብ

> "የዓለም፣ የገነትና
> የምድር ታላቁ ሳይንስ ፍቅር ነው"
>
> ማዝር ቱራዛ

ሴቶች ለወንዶች የደስታ ፣ የስኬት ፣ የህልውና፣ የእርካታና የመኖር ፍላጎት መሰረት ናቸው። በሴቶች ለመደሰት፣ ስኬት ለመጎናፀፍ፣ ለመርካት፣ ጣፋጭ ህይወት ለመኖር ግን መጀመሪያ ሴቶችን በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል። የሴቶችን ስሜት መረዳት ውበታቸውን የማወቅ ያህል ቀላል አይደለም። የሴቶችን ቁንጅና ተመልክቶ፣ መማረክና በፍቅር መውደቅ ለወንድ ልጅ የጥቂት ሰከንዶች ጉዳይ ነው። የወደዳትን ሴት ቀርቦ አነጋግሮ በተመሳሳይ ሁኔታ እሷን በፍቅሩ ማጥመድ ግን ከወራት እስከ ዓመታት እንዲሁም በዕድሜ ልክ ሊቋጭ የማይችል ከባድ የቤት ሥራ ነው።

ይህ የሚሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው... አንደኛ በተፈጥሮ ጥልቅ በሆነው የሴቶች ባህርይና ስብዕና ሲሆን ሁለተኛው

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ደግሞ ወንዶች ይህንን የሴቶች ጥልቅ ስብዕናና ባህርይ መረዳት ባለመቻላቸው ነው፡፡ ሴቶችና ወንዶች ብዙ የሚያመሳስሏቸው ባህርይዎችና ስብዕናዎች የመኖራቸውን ያህል የሚለያዩባቸውም አሉ፡፡

በተቃራኒ ፆታ የመማረክ፣ በፍቅር የመውደቅ ጉዳይ አንዱ የሚለያዩበት ነገር ነው፡፡ ወንዶች በሴቶች የሚማረኩበትና ሴቶች በወንዶች የሚማረኩበት ሁኔታ ይለያያል፡፡

‹ወንዶች በሴቶች የሚማረኩት እንዴት ነው?›

የሚለውን ጥያቄ መመለስ 1+1 ስንት ይሆናል የማለት ያህል ቀላል ነው፡፡

‹ሴቶች በወንዶች የሚማረኩት እንዴት ነው?›

የሚለው ጥያቄ ግን የ"Theory of Relativity"ን ያህል ሳይንሳዊ ጥናትና ትንታኔ የሚፈልግ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ‹ሴቶች በወንዶች የሚማረኩት እንዴት ነው?› በሚለው ጉዳይ ላይ ብዙ ኮሌጆች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሚዲያዎችና ዌብሳይቶች እንዲሁም ሳይንቲስቶች፣ ፀሃፊዎች፣ ሳይኮሎጂስቶች፣ ሶሺዮሎጂስቶች፣ የፍቅር ግንኙነትና የጤና ባለሙያዎች በርካታ ጥናቶችና ምርምሮችን አካሂደዋል፡፡

የሴቶች በአጠቃላይ የሰዎች ፍላጎትና ስሜት በየዘመኑ የመለዋወጥ ባህርይ ስላለው ጥናቱና ምርምሩ ያለማቋረጥ ይቀጥላል፡፡ በርካታ የጥናት ውጤቶች እንደሚያሳዩት ዘመን በተለዋወጠ ቁጥር ሰዎች በሌሎች ሰዎች እንዲማረኩ የሚያደርጓቸው ብቃቶችም በመለዋወጥ ላይ ናቸው፡፡ በተለይ ሴቶች ይማረኩ ዘንድ ወንዶች ሊኖሯቸው የሚገቡ ብቃቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ነው፡፡ ወንዶች በሴቶች ለመማረክ የሚያስፈልጓቸው ብቃቶች ዝርዝር ግን በሚሊዮን ዓመታት ውስጥ ብዙም ለውጥ አላሳየም ማለት ይቻላል፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

# ማራኪነት... መማረክ ምንድነው?

በተቃራኒ ፆታዎች መካከል የሚፈጠረው የመማረክና የመማረክ ነገር ለሰው ልጆች ህልውና እና መራባት ወሳኝ ሚና ከተጫወቱት መሰረታዊ የሰው ልጅ ስሜቶች ውስጥ አንዱ ነው። የመማረክ ስሜት ልክ እንደ መራብ፣ መጠጣትና መተኛት የመሳሰሉ መሰረታዊ የሰው ልጅ ስሜቶች አንዱ ሲሆን ላለፉት ሚሊዮን ዓመታት የሰው ልጅ የዘር ሃረግ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ ሚና የተጫወተ ጥንታዊና መሰረታዊ ትልቅ ስሜት ነው።

ፍርሃት የሚሰማቸው ሰዎች ከማይፈሩት የበለጠ የመኖር ዕድል እንደሚያገኙት ሁሉ በሌሎች ሰዎች የሚማረኩ ሰዎችም ከማይማረኩት የበለጠ ዘራቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ ዕድል አላቸው። የፍርሃት፣ የርሃብ፣ የድካም ስሜት እንዳይሰማን ለማስቆም ወይም ልናቆመው በጭራሽም አይቻለንም። ሲርበን የርሃብ ስሜት ይሰማናል፣ ሲደክመን የድካም ስሜት ይደርስናል። ስንፈራ የፍርሃትን ስሜት እናስተናግዳለን። አንድ ሰው ሲማርከንም ልክ እንደዚያው ነው። የማረከንን ሰው አትማርከኝም ብለን ልንተወው ልንከላከለው አንችልም። በአጠቃላይ መማረክ አስበን የምንወስነውና የምንቆጣጠረው ሳይሆን ከቁጥጥራችን ውጪ በሆነ ሁኔታ የሚሰማን ሃያል የተፈጥሮ ስሜት ነው።

አንድ ሰው በሌላ ሰው የመማረክ ሁኔታ አጠቃላይ ማለት ጭንቅላቱ [illegible] የሚሰጠው፣ ዘሩን ለማራባት የሚረዳው ጥሩ የመራቢያ ጓደኛ እንዳገኘ እየነገረው ነው ማለት ነው። የሰው ልጅ ላለፉት ሚሊዮን ዓመታት ዘሩን እያራባ ህልውናውን አረጋግጦ ሊቆይ የቻለው በዚህ ሁኔታ ነው።

የሰው ልጅ የፍቅርና የመስተሳሰብ ሁኔታ ከዚህ ጋር [illegible]

ሲለዋወጥ ብዙ ነገሮች አብረው ተለውጠዋል። የመማረክና የማራኪነት ስሜት ግን መሰረታዊ ይዘቱን አልለቀቀም ማለት ይቻላል። ይልቁንም የመማረክና የማራኪነት ስሜት ሳይንስና ጥበብ ወደ መሆን ደረጃ አድጓል።

## ማራኪነት ለሴቶች እና ለወንዶች የተለያዩ ናቸው

ከመማረክና ማራኪነት ጋር የተያያዘ ከላይ ሁለት ወሳኝ እውነታዎችን ተገንዝበናል።

፩. ‹መማረክ› ልክ እንደ ርሃብ፣ ድካም፣ ፍርሃት መሰረታዊ የሰው ልጅ ስሜት መሆኑን።

፪. የመማረክ ስሜት አስበን የምንወስነውና የምንቀበለው ሳይሆን ከቁጥጥራችን ውጪ በሆነ ሁኔታ የምናስተናግደው ስሜት መሆኑን።

እሁን ደግሞ ሌሎች ሁለት መሰረታዊ የመማረክ ዕውቀቶችን እንመለከት። የመጀመሪያው ልናውቀው የሚገባ መሰረታዊ እውቀት… ሴቶችም ወንዶችም መርጠው የመውደድ፣ መርጠው የማፍቀር፣ መርጠው የመማረክ ችሎታ የላቸውም።
ሁለቱም ፆታዎች የሚሰማቸው የመውደድ… የማፍቀር… የመማረክ ስሜት ከቁጥጥራቸው ውጪ ነው።

ሁለተኛው መሰረታዊ ዕውቀት… ሴቶች በወንዶች ለመማረክ እና ወንዶች በሴቶች ለመማረክ የሚያስገድዷቸው ነገሮች የተለያዩ ናቸው። ሁለቱ ፆታዎች የመማረክን ስሜት ለማስተናገድ የሚገደዱ ቢሆንም ሴቶች በወንዶች ተማርከው እጅ እንዲሰጡ የሚያደርጓቸው የወንዶች ባህሪይዎችና ብቃቶች፣ ወንዶች በሴቶች ተማርከው እንዲንበረከኩ ከሚያደርጓቸው የሴቶች ባህሪይዎችና ብቃቶች ፍፁም የተለያዩ ናቸው።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ይህንን በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን የመማረክ ስሜት መሰረታዊ ልዩነት አለማወቅ ለሁለቱም ፆታዎች መሳሳትና መክሰር ምክንያት ሲሆን ይስተዋላል። ወንዶች ልክ በሴቶች ሲማረኩ የሚሰማቸውን ዓይነት ስሜት ሴቶችም ይሰማቸዋል የሚል የተሳሳተ ግምት ይዘው ትክክል ባልሆነ አቅጣጫ ሴቶችን ለመማረክ ሙከራ ያደርጋሉ፤ ይህም ሳይሳካላቸው ሲቀር ሴቶቹን ይራገማሉ። ሴቶች በበኩላቸው ወንዶች ለውጪያዊ እንጂ ለውስጣዊ ውበት ቦታ የማይሰጡ ‹እንስሶች› ናቸው እያሉ ይኮንናሉ።

ነገር ግን ከላይ እንደተገለፀው ወንዶችን የሚማርካቸው የሴቶች ብቃትና ሴቶችን የሚማርካቸው የወንዶች ብቃት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የሚማርኳቸው ብቃቶችና ሁኔታዎች በተፈጥሮ የተለያዩ ናቸው።

ወንዶች በውበት ስለተማረኩ ብቻ ሴቶች ‹ለውጪያዊ እንጂ ለውስጣዊ ውበት ቦታ የማይሰጡ እንስሶች ናቸው› ብለው ወንዶችን ይኮንናሉ። ነገር ግን ‹ለምን ራባቸው... ለምን ደከማቸው› እንደማለት ነው። ምክንያቱም የሴቶችን ውበት አይቶ መማረክ የወንዶች ተፈጥሯዊ ስሜት ነውና ነው።

ሴቶችን የሚማርካቸው የወንዶች ባህርይና ብቃት እንዲሁም ወንዶችን የሚማርከውን የሴቶች ውበት በዝርዝር እንመልከት...

## ወንዶች የሚማርካቸው ምንድነው?

ባለፉት 2 ሚሊዮን ዓመታት በሰው ልጅ የአኗኗርና የአስተሳሰብ ህይወት ላይ ብዙ ለውጦች ተከስተዋል። ምንም እንኳን የሰዎች አስተሳሰብ፣ ፍላጎት፣ ምኞት፣ ስሜት፣ ራዕይ፣ ህልም... ከጊዜ ወደ ጊዜ ቢለዋወጥም ወንዶች በሴቶች የሚማረኩበት

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

መሰረታዊ ስሜት ግን አልተለወጠም:: የድሮ የዋሻ ዘመን ወንዶች በሴቶች ውበት ይማረኩ... ይንበረከኩ ነበር:: የአሁኑ ዘመን ወንዶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሴቶች ውበት ይከንፋሉ:: ጥንትም አሁንም የወንዶች የመማረክ ስሜት ፈጥኖ ምላሽ የሚሰጠው ለሚያዩት ውጪያዊ ውበት ነው:: ‹ውጪያዊ ውበት› የሚለው ለእያንዳንዱ ወንድ የተለያየ ቅርፅ፣ ምስልና ትርጉም ሊኖረው ቢችልም በአጠቃላይ ግን ወንዶች በተፈጥሮ የተቀረፅነው በማየት ለመማረክ ነው::

በዚህም ከሴቶች ብዙ የስድብና የትችት ናዳዎች ይሰነዘራሉ:: ‹ወንዶች ብስለትና ጥልቀት ስለሌላቸው ከውጪያዊ ውበት አልፈው ሌሎች ብቃቶቻችንን መመልከት አይችሉም› በማለት ሴቶች ያማርራሉ::

ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎች ደግሞ ‹የወንዶች ለውጪያዊ ውበት መማረክ ተፈጥሯዊ ግዳጅ እንጂ ምርጫ አይደለም› ይላሉ::

የወንዶች መሰረታዊ የመማረክ ሳይንስም ሆነ ተፈጥሮ በሴት ልጅ ውጪያዊ ውበት ላይ (በማየት ላይ) የተመሰረተ መሆኑ እንዳለ ሆኖ አንዳንድ ጊዜ-አመጣሽ ነገሮች በወንዶች የመማረክ ስሜት ላይ ተፅዕኖ አልፈጠሩም ማለት ግን አይቻልም:: ስለሆነም ወንዶች በቅድሚያ የሚማረኩት በሴት ልጅ ውጪያዊ ውበት (በማየት) ሲሆን በመቀጠል በአነጋገር ለዛ፣ በአስተሳሰብ ደረጃ፣ በታማኝነት፣ በችሎታ፣ በአለባበስ ውበትና በስኬት... በመሳሰሉ ብቃቶች ሊማረኩ ይችላሉ::

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## ሴቶች የሚማርካቸው ምንድነው?

ወንዶች አሁን በደንብ ልብ ብላችሁ አንብቡ... ቀጥሎ የምታነቡት ነገር ህይወታችሁን የሚለውጥ ካልሆነ ቢያንስ ሴቶችን በተመለከተ ወደ ትክክለኛ የአስተሳሰብ አቅጣጫ የሚወስድ ሰውቀት ነው፡፡

ወንዶችን የሚማርከውና የሚያንበረክከው ቀዳሚው አስማት የሴቶች ውጪያዊ ውበት ነው፡፡ (አሁንም ‹ውጪያዊ ውበት› የሚባለው ለእያንዳንዱ ወንድ የተለየ ቅርፅና ትርጉም እንደሚኖረው ልብ ይባልልኝ)
ሴቶችን የሚማርከውና የሚያንበረክከው ግን የወንዶች ውጪያዊ ውበት አይደለም፡፡ ወንዶች የምንማረከው በማየት ሲሆን ሴቶች የሚማረኩት ግን በስሜት ነው፡፡ በባህርያቸው፣ በተግባራቸው፣ በስኬታቸው፣ በጀግንነታቸው፣ በዝናቸው፣ በችሎታቸው... የሴቶችን ስሜት ከፍና ዝቅ የሚያደርጉ ወንዶች ሴቶችን በፍቅር ይማርካሉ... ያንበረክካሉ፡፡

### ←←←←←←← ፋስት ሪዋይንድ

## የድሮ ዘመን ሴቶች የሚማርካቸው ምን ነበር?

ለአፍታ ወደ የዋሿው ዘመን ጥንታዊ የሴትና የወንድ የመዋደድ ታሪክ መለስ እንበል... የዚያን ጊዜ ሴቶች በድፍረት ጫካ ገብተው ከአውሬ ጋር ተፋልመው የሚጠበስ ሥጋ ይዘው በጀግንነት በሚመለሱ ወንዶች ይማረኩ ነበር፡፡

ድፍረት፣ ከአውሬ ጋር መፋለም፣ ለቤተሰብ ሥጋ ይዞ በጀግንነት መመለስ... እነዚህ ብቃቶች የዚያን ዘመን ሴቶችን ስሜት ከፍና ዝቅ በማድረግ በፍቅር እንዲወድቁ ያደርጉ ነበር፡፡ በመሆኑም ብዙ የዚያ ዘመን ወንዶች ሴቶችን ለመማረክ ጦራቸውን

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

እያሾሉ በድፍረት ጫካ ገብተው ከአውሬ ጋር ለመፋለም ይገደዱ ነበር፡፡ ተሳክቶላቸው አውሬውን አሸንፈው ‹አንበሳ ገዳይ› ተብለው የጀሮ ጌጥ የሚያንጠለጥሉ ወንዶች የቆንጆ ሴቶች ቆንጆ ሙቀት ይጠብቃቸው ነበር፡፡

ቀጥለው የተቀመጡ ሁለት ምሳሌዎችን ልብ ብላችሁ አንብቡ፡-

**ምሳሌ አንድ**

አንድ መልከ መልካም ወንድ በመልከ መልካምነቱ ተማምኖ መንደሩ ውስጥ ይንጎማለላል፡፡

**ምሳሌ ሁለት**

አንድ ወንድ በድፍረት ጫካ ገብቶ ለበርካታ ቀናት ይጠፋል፡፡ በመጥፋቱም ‹ሞተ … አልሞተም› በሚል የመንደሩ በሙሉ የመነጋገሪያ ርእስ ይሆናል፡፡

ልጆች፣ አዋቂዎች፣ አዛውንቶችና አሮጊቶች የእርሱን መምጣት አሊያም ዜና-እረፍት በጉጉት ይጠባበቃሉ፡፡ ከበርካታ ቀናት በኋላ ሁሉም ተስፋ በቆረጠበት ጊዜ ግን ድንገት ብቅ ይላል፡፡ ትልቅ አውሬ ገድሎ እየፎከረ ሲመጣ ሴቶች በእልልታ፣ ልጆች በጭብጨባ ይቀበሉታል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ ካሉት ሁለት ወንዶች የመንደሩን ቆንጆ ሴቶች ስሜት የሚማርከው የትኛው ነው?

በምሳሌ ሁለት የተጠቀሰውን ጀብደኛ ወንድ ካላችሁ አልተሳሳታችሁም፡፡

ጉዳዩን በደንብ ሰባብረን እንመልከተው…

ሴቶች በፍቅር እንዲወድቁ የሚያደርጋቸው ስሜታቸውን

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

[illegible] ሰራል በማለ

[illegible] ወዘቀ ሰላቶ በማ

[illegible] በሰቀቶ

[illegible] መልኩም ነው ወንዝ

[illegible] ቸውን አየሁት በማዕቱ

[illegible] የወደቀች ሕዝቡ

[illegible] መልኩም ነገር ስለ

[illegible] እንደ ወንዝ ወደ ሰርን

[illegible] የተመሰለ

[illegible] በአመለካከት የማም በመለስ

[illegible] ግን ዉጪውን ለእርን

[illegible] የማክሉን የመለከተል

[illegible] በመሉ የመን ግንባር ርእስ

[illegible] የደረቀል የወጣ በመፕሬቱ

[illegible] መቀል ሐመዴ ጋር ፊት ለፊት

[illegible] አይተለው ነው የመለከት

[illegible] የሚናፈስት ወሬዎች

[illegible] አመለካከት ተኮት እንዲናፈቁው

[illegible] አወሬ ገርሞ ደንነት ወቀ ቢሌ

[illegible] በሚወክለው ሊቀበልት ወደጅን

[illegible] ወጣት ሲቶኝ ካቶው በሆን

[illegible] ሙሉ መለከም ወንድ ለመንደሩ

[illegible] የሰባተቀል [illegible] መንም ካለቶ

[illegible] መለከው ወንድ ልክ በምለል

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሁለት ያለው ወንድ ዓይነት ብቃት ቢኖረውስ ምን ይፈጠር ነበር? ሴቶቹ የበለጠ ይማረኩ… ይዝረከረኩ ነበር።

የሴቶች የመማረክ ስሜት ከመልክ ይልቅ በሌሎች ብቃቶች እንደሚሽመደመድ በቂ ግንዛቤ ያገኙን ይመስለኛል። ነገር ግን በዚህ ጉዳይ እዚህ ላይ አላበቃም።

ሴቶች ምን ይማርካቸዋል? የሚለውን ልክ እንደ እጃችሁ መዳፍ እስክታውቁት ድረስ እቀጥላለሁ።

ከዋሻው ዘመን ሰው ሳንወጣ አንድ ወሳኝ ነጥብ ላስቀምጥና ፋስት ፎርዋርድ አድርገን አሁን ወዳለንበት ዘመን እንመጣለን።

በዋሻው ዘመን ሴቶችን የሚማርካቸው የወንድ ብቃት ሲጨመቅ ‹አቅራቢና ጠባቂ› (Provider & Protector) በሚል ይጠቃለላል።

ቤተሰቡን በሚገባ መመገብ የሚችልና ከተለያዩ አደጋዎች የሚጠብቅ ወንድ በብዙ ሴቶች ተፈላጊ ነበር። ‹አቅራቢና ጠባቂ› በሚሉት ሁለት ወሳኝ ብቃቶች ውስጥ ሊተነተኑ የሚችሉ በርካታ የወንድ ባህርያት እንዳሉ ልብ ማለት ያስፈልጋል። አንድ ወንድ ቤተሰቡን በሚገባ ለመመገብ አደን ሄዶ ከአውሬ ጋር መፋለም ይኖርበታል። ቤተሰቡን ከተለያዩ አደጋዎች የሚጠብቅ ጋሻ መከታ መሆንም እንደዚያው ብዙ ጥረቶችን ይጠይቃል።

## ፋስት ፎርዋርድ →→→→→→
## የአሁኑ ዘመን ሴቶች የሚማርካቸው ምንድነው?

የእኛ የወንዶች የመማረክ ስሜት አሁንም መሰረታዊ ይዘቱን እንዳልቀየረ ሁሉ ሴቶች የሚማረኩበት መሰረታዊ ስሜትም አልተቀየረም።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ወንዶች አሁንም በውጪያዊ ውበት ይማረካሉ፡፡ ሴቶችም በምርጫቸው ሳይሆን ወንዶቹ በሚፈጥሩባቸው ስሜት ለመማረክ ይገደዳሉ፡፡ ነገር ግን ዘመን በተለዋወጠ ቁጥር ወንዶችን የሚማርኩ የሴቶች ውጪያዊ ውበቶች ላይ ለውጦች ተስተውለዋል፡፡ ሴቶችን የሚማርከው የወንዶች ብቃትም በቁጥር ጨምሯል፡፡

ሴቶች የሚማረኩበት የወንዶች ብቃት ቁጥር መብዛቱ ለእኛ ለወንዶች ሲሳይ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ዕድልም ነው፡፡ ወንዶች በቀዳሚነት እንዲማረኩ የሚያደርጋቸው ተፈጥሯዊ ስሜት የሴቶች ውጪያዊ ውበት መሆኑ ለሴቶች ችግር ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ውጪያዊ ውበት ያልታደሉ ሴቶች ወንዶችን ለመማረክ ብዙ ጥረትና ድካም ይጠይቃቸዋል፡፡ ነገር ግን ሴቶች በወንዶች ልዩ ልዩ የስብዕና ብቃቶች የሚማረኩ የመሆናቸው እውነታ ለወንድ ልጅ መልካም ዜና ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ወንድ ሴቶችን መማረክ ከሚያስችሉ በርካታ ብቃቶች መካከል የተወሰኑት ይኖሩታል፡፡ ምንም ባይኖረው እንኳን በልምምድና በሰውቀት ሊያዳብራቸው ይችላል፡፡

## ሴቶችን የሚማርኩ የወንድ ስብዕናዎችና ዋና ዋና ብቃቶች

### ሀ. እቅራቢ እና ጠባቂ

- ልክ በዋሻው ዘመን እንደነበረው ሁሉ በአሁኑ ዘመንም የበለጠ ማቅረብና መጠበቅ የሚችል ወንድ የበለጠ መማረክና ማንበርከክ ይችላል፡፡ ሴቶች በሃብታሞች፣ በገዢዎችና በባለስልጣኖች የሚማረኩት ለምን ይመስልሃል? ቆንጆ ሴቶችን የምታየው ቆንጆ ቆንጆ መኪና ከሚነዱና አሪፍ አሪፍ ቦታ ከሚዝናኑት ጋር ነው ወይስ በእግር ከሚሄዱና በቀበሌ መዝናኛ ክበብ ከሚያሳልፉ? መልሱ ግልፅና መራራ ሃቅ ነው፡፡ አስታውስ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

‹ሴቶች ማቴሪያሊስቶች ናቸው› እንዳትል፡፡ ማቅረብና መጠበቅ ለሚችል ወንድ መማረክ ተፈጥሯዊ ስሜታቸው እንጂ ምርጫቸው አይደለም፡፡ ይልቅ ‹አቅራቢና ጠባቂ› ለመሆን ጣር… ለህይወትህም አስፈላጊ ነውና፡፡ ይህ ማለት ግን ሴቶች ማቅረብና መጠበቅ ለሚችል ወንድ ብቻ ይማረካሉ ማለትም አይደለም፡፡ ንባብህን ቀጥል…

### ሰ. በራስ መተማመን (ልበ ሙሉነት)

- በራስ የመተማመን ስሜት ያለው ልበ ሙሉ ወንድ የሴቶችን ልብ የማቅለጥ አቅም አለው፡፡ በራስ የመተማመን ስሜት ያለው ልበ ሙሉ ወንድ መሆንህን ለማረጋገጥ ልክ እንደ ዋሻው ዘመን ወንድ ጦር ይዘህ ከአንበሳ ጋር ለመፋለም ጫካ መግባት አይጠበቅብህም፡፡ አለመርበትበት፣ አለመቅለስለስ፣ አካሄድ ማሳመር፣ ትኩር ብለህ ዓይናቸውን ለማየትና ዘና ብለህ ለማናገር አለመፍራት… ናቸው የሚጠበቁብህ፡፡ ከዋሻው ዘመን ወንድ ጋር ሲነፃፀር የእኛ ዘመን እጅግ በጣም ቀላል ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡**

- ሴቶች በራስ መተማመን ስሜት ያለውና የሌለውን ወንድ ከርቀት አሽትተው የመለየት ከፍተኛ ችሎታ አላቸው፡፡ ስለዚህ በተፈጥሮ በራስ የመተማመን ስሜት… ልበ ሙሉነት የሚያንስህ ከሆነ ተለማመድ፡፡ ደስ የሚለው ነገር ይህን ብቃት በልምምድ የራስህ ልታደርገው መቻልህ ነው፡፡

- ሁሉም የወንድ ብቃቶች ሁሉንም ሴቶች የመማረክ ሃይላቸው ተመሳሳይ አይደለም፡፡ ሴቶች ለተለያዩ የወንዶች ብቃቶች የተለያየ ግምትና ነጥብ በመስጠት ልዩነት ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ‹በራስ መተማመን› ላይ 99% ሴቶች ይስማማሉ፡፡ በራስ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

መተማመን... ልብ ሙሉነት ሁሉንም ሴቶች የመማረክ ኃይል ያለው መሣሪያ ነው።

## ሐ. ተጫዋችነት (ቀልድ አዋቂነት)

- ሴቶች የሚያስቃቸው... ተጫዋች ወንድ በጣም ይወዳሉ። ለምን? በጣም ግልፅ ነው... መሳቅ ይወዳሉ... ይፈልጋሉ። ለማሳቅ የግድ ኮሜዲያን መሆን አይጠበቅብህም። ጨዋታ መቻልና ቀለል ያለ... ለጨዋታና ለሳቅ ክፍት የሆነ ስብዕና መገንባት በቂ ነው። ሳቅ ለደስተኛ ሕይወትና ለረዥም ዕድሜ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡ ስለዚህ ሴቶች የሳቃቸው ምንጭ የሆነን ጨዋታ አዋቂ ወንድ ቢወዱ አትፍረድባቸው። ይልቅ ፈታ በል። የተለያዩ ቀልዶችን የመስማትና የማንበብ ልምድ አዳብር። ቀልድ አወራር ተለማመድ።

### ምርቃት

ተጫዋችነት (ቀልድ አዋቂነት) ብዙ መልከ መልካም ያልሆኑ ወንዶች ሴቶችን ለመማረክ የሚጠቀሙበት ምስጢራዊ መሣሪያ ነው። መልከ መልካም ሆንክም አልሆንክ መሣሪያውን የግልህ አድርገው... ተጠቀምበት።

### ማስጠንቀቂያ

የጨዋታና የቁምነገርን ጊዜያት እንዳትቀላቅላቸው። ለጨዋታም ለቁምነገርም ጊዜ ይኑርህ። ጊዜህን በሙሉ ለጨዋታና ለሳቅ ብቻ ከሰጠህ 'አጫዋች' (ክላውን) የመባል አደጋ ሊያጋጥምህ ይችላል።

## መ. ዝና

- ዝነኞች የብዙ ሰዎችን ቀልብ ይማርካሉ። በመልካም ስራቸው ዝነኛ የሚሆኑ ሰዎች በህዝብ የመወደድና የመደነቅ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ዕድልም አላቸው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተሰሚነትና ኢኮኖሚያዊ አቅም አላቸው ማለት ነው፡፡ ተሰሚነትና ኢኮኖሚያዊ አቅም ሲመነዘሩ ደግሞ ‹አቅራቢነትና ጠባቂነት› ይሆናሉ፡፡ በዚያ ላይ የዝነኞች ኑሮ ከአብዛኛው ህዝብ ለየትና ደልቀቅ ያለ ሁኔታ ይኖረዋል፡፡ ዝና የሚያስገኛቸው የልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች ባለቤት የሆኑ ዝነኛ ወንዶች ሴቶችን የመማረክ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በእነዚህ እውነታዎች ዝነኛ ወንዶች የብዙ ሴቶች ዓይን ያርፍባቸዋል፡፡ ሴቶች ለዝና እንዲማረኩ የሚያደርጋቸው ዋናው ነጥብ የሚወለደውም እዚህ ላይ ነው… ሴቶች በብዙ ሴቶች በሚፈለጉ ወንዶች ይማረካሉ፡፡ በብዙ ሴቶች የሚፈለጉ ወንዶችን የግላቸው ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡

ዝና ሙዚቃና ፊልምን በመሳሰሉ የጥበብ ሥራዎች አይገደብም፡፡ በማንኛውም ዓይነት ሥራ ስሙ-ጥር መሆን ማለት ነው፡፡

- ሴቶች ፈገግ የሚሉለት ወንድ የበለጠ ብዙ ሴቶችን የመማረክ ዕድል እንዳለው ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ ሴቶች ፈገግ የሚሉለት ወንድ እንደዚህ ዓይነት ዕድል ካለው… ብዙ አድናቂዎች ያሉት ዝነኛ ወንድ ምን ያህል ማራኪ ሲሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

### ሠ. ዕውቀት

- አሁን ዕውቀት ወደ ገንዘብና ወደ ዝና የሚመነዘርበት… የዕውቀት ኢኮኖሚ ዘመን ላይ እንገኛለን፡፡ ገንዘብና ዝና ሴቶችን የሚማርኩ ብቃቶች እንደሆኑ ከላይ አይተናል፡፡ ዕውቀት ለብቻው ወደ ገንዘብና ወደ ዝና ሳይመነዘርም ግን የመማረክ ኃይል አለው፡፡

ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ አንድ ርዕስ ጉዳይ ተነስቶ ሁሉም ግራ በመጋባት ሲቁለጨለጭ አንተ በዕውቀት የታገዘ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

በቂና አሳማኝ ማብራሪያ ከሰጠህ ሴት ጓደኛህ በኩራት እጅህን አሲያም ወገብህን ጭምቅ ታደርግሃለች። በቂ ዕውቀት ሲኖርህ የሰከነና ያገናዘበ ውሳኔ መወሰን ትችላለህ። በዚህ ሁሉ ድምር ደግሞ ሴቶች ስኬታማ ህይወት ሊኖርህ እንደሚችል መተንበይ ይችላሉ። ዕውቀት፣ አስተዋይነት፣ ስኬት... ማራኪ ብቃቶች ናቸው።

## ፈ. የዓላማ ፅናትና አቅም

- አንድ ሰው በህይወቱ ሊያሳካው የሚፈልገው ነገር ሲኖርና ያንን ነገር ለማሳካት ቁርጠኝነት ያለው... በሚያጋጥሙት ችግሮችና መሰናክሎች ተስፋ ሳይቆርጥ የሚፈልገውን ነገር ለማሳካት ተግቶ ወደፊት ሲገሰግስ ‹የዓላማ ፅናት› አለው ይባላል። የህይወት መንገዱን አጥርቶ በመወሰን መንገዱ ላይ በሚገጥሙት እንቅፋቶች ሳይሸበርና ሳይንበረከክ የሚፈልገው መዳረሻ ድረስ የሚጓዝ ሰውም እንደዚያው ባለ ‹ፅኑ ዓላማ› እንለዋለን። አንድን ነገር ለማግኘት አቅዶ ዕቅዱን ለማሳካት ወለም ዘለም ሳይል ጠንክሮ ሌት ተቀን የሚሰራ... እርሱም ‹የዓላማ ፅናት› አለው። በአጠቃላይ ተስፋ የማይቆርጥ፣ የማይበገር፣ ለፈለገውና ላቀደው ዓላማ በፅናት የሚቆምና የሚሠራ ሰው የሴቶችን ልብ በቀላሉ ያሸንፋል። ለዓላማ መፅናት... አለመወላወልና አለመልፈስፈስ ሴቶችን የሚማርክ ጠንካራ ብቃት ነው።
- ሴቶች የወንዶችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የማንበብና የመተንበይ ተሰጥዖ አላቸው። ስለሆነም አሁን ስኬታማ ባትሆን እንኳን ወደፊት ስኬታማ የመሆን አቅም ካለህ ጥሩ ነጥብ ይሰጡሃል። ህልም... ራዕይ ያለውና ራዕዩን ህልሙን ለማሳካት የማይተኛ ጠንካራ ወንድ ሴቶችን ይማርካል። ስለዚህ እስካሁን ስኬታማ ካልሆንክ ባለ ራዕይ ሁን። ራዕይህን ለማሳካት ሁልጊዜ ማልደህ

Scanned by CamScanner @BOOKALEM

ተነስ። አንድ ቀን ራዕይህን እንድታሳካ የምታግዝህ ቆንጆ ሴት ታገኛለህ።

### ሰ. መልክ

- መልክ ሴቶችን ሊማርክ የሚችል ሌላ የተፈጥሮ ፀጋ ነው። ነገር ግን የወንዶች መልክ የሴቶቹ ውበት ወንዶችን ለመማረክ ያለውን ያህል ኃይል የለውም። ምክንያቱም ከላይ እንደገለፅኩት ወንዶች የምንማረከው በምናየው ነገር ሲሆን ሴቶች ግን በማየት ሳይሆን በስሜት ይማረካሉ። ስለሆነም አንድ ወንድ መልከ መልካም ስለሆነ ብቻ ሴቶችን ሙሉ በሙሉ ሊማርክ አይችልም። በመልኩ ተማርከው ከቀረቡት በኋላ ሴሎች ወሳኝ ብቃቶች ከሌሉት ... አቅራቢና ጠባቂ ካልሆነ ይጥሉታል። ከመልክ ጋር አስፈላጊ የሆኑት ብቃቶች ካሉት ግን መማረክ ብቻ ሳይሆን ሊያሳብዳቸው ይችላል።

### ብራድ ፒትን እንደ ምሳሌ

የሆሊዉድ ፊልም ተዋናይ ብራድ ፒት በዓለማችን ከሚኖሩ አጠቃላይ ሴቶች ሩቡን ያህል መማረክ ችሏል። እነዚህ የዓለማችን ሩብ ሴቶች ብራድ ፒትን ማግባት ይመኛሉ። በዚህ የተነሳም ብራድ ፒት ‹የዓለማችን አማላይ ወንድ› በሚል ሁለት ጊዜ በፒፕል መፅሔት ተመርጧል። ያገባውም በተመሳሳይ ሁኔታ በፒፕል መፅሔት ‹የዓለማችን ቆንጆ ሴት› ተብላ የተመረጠችውን አንጀሊና ጆሊን ነው። ብራድ ፒት አንጀሊና ጆሊን ጨምሮ የዓለማችንን ሩብ ቆነጃጅት መማረክ የቻለው በመልከ መልካምነቱ ብቻ አይደለም።

ምክንያቱም ከእርሱ በመቶ እጥፍ የሚበልጡ መልከ መልካም ወንዶች ዓለማችን አፍርታለችና ነው። ከእርሱ የሚበላለጡ መልከ መልካም ‹ሞዴል› ወንዶች እንደ ኒው ዮርክ፣

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ፓሪስ፣ ሮም፣ ሚላን በመሳሰሉ የፋሽን ከተማ ትዕይንቶች ላይ በየቀኑ ያለ መሰልቸት ነገር ግን ህልም ተደምረው የዉበት ፒተን የሆነ ተከራት አያስበም

ብራድ ፒት የሴቶች ማግኔት ሊሆን የቻለው በመልክ መልካምነቱ ባሻገር በዙ ማራኪ ብቃቶች ስላሉት ነው። የፊልም ክበዝ ተምሳይ ነው። ማቀረብ፣ መጠበቅ የሚችል የጤና ዋስትናም ነው። በመላው ዓለም ሰው የሚተወቅ ዝናኛ ነው። የተቸገሩ ሰዎች የተሻለ ሕይወት እንዲያገኙ የመርዳት ስነ ዓላማ ያለውና በተግባር የሚሰራ ሰው ነው። በአጠቃላይ ያሉት በርካታ ብቃቶች ተደማምረው መልክ መልካም ባይሆንም እንኳ ተወዳጅና ማራኪ ሊያደርጉት ይችሉ ነበር።

## ሸ. ጤናማና ማራኪ አቋም

- ዝና፣ ሃብት፣ መልክ፣ ተጨባጭነት የመሳሰሉ ብቃቶች እያንዳንዳቸው ለሁሉም ሴቶች መቶ በመቶ ማራኪ ላይሆኑ ይችላሉ። እስካሁን ካየናቸው የወንድ ልጅ ማራኪ ብቃቶች ሁሉ 99% የዓለም ሴቶችን ልብ በማሸነፍ ቁጥር አንድ ደረጃ ላይ የተቀመጠው በራስ መተማመን ነው። አሁን ግን በራስ መተማመን ቁጥር አንድ የሆነውን ለጤናማና ማራኪ አቋም በመልቀቅ ቁጥር ሁለት ደረጃ እንዲይዝ ይገደዳል። ምክንያቱም 100% የዓለማችን ሴቶች ጤናማና ውብ አቋም ላይ የሚያገኙ ወንድ ይወዳሉ። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያደርግ ልምድ አዳብርና ጤናማና ማራኪ አቋም ያለህ ሰው ሁን።

## ቀ. አልፋ ወንድ

- የዓለም ሴቶች ህልም የወንዶች ወንድ የሆነውን 'አልፋ ወንድ'

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ማግኘት ነው፡፡ አልፋ ወንድ ማን ነው? አልፋ ወንድ ከላይ የተዘረዘሩትን ብቃቶች በሙሉ አሊያም በብዛት የሚያሟላ ባለ ብዙ ብቃቶች ባለቤት የሆነ የወንድ ዓይነት ነው፡፡

## …እና ሌሎችም

- ጥሩ የማድመጥ ችሎታ፣ ተግባቢነት፣ ለእንስሳት ደግ መሆን፣ ራስን መቻልና ነፃነት፣ የመሪነት ብቃት፣ የመወሰን ችሎታ፣ መልካም ስብዕና፣ ከሙዚቃ መሳሪያ እስከ የተነፈሰ ጎማ መቀየር ድረስ ያሉ የተለያዩ ችሎታዎች… ሴቶችን መማረክ የሚችሉ ብቃቶች ናቸው፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

# ቋንቋችንም ይለያያል... ሴትኛ ቋንቋ ትችላለህ?

‹ የሴቶች ገላ ከወንዶች ገላ የለሰለሰ የመሆኑን ያህል፣ የመረዳት ችሎታቸውም ከወንዶች የላቀ ነው ›

ክሪስቲን ዴ ፒዛን

ሴቶች ከቬነስ፣ ወንዶች ከማርስ... ከሁለት የተለያዩ ፕላኔቶች የመጣን እንደመሆናችን መጠን ቋንቋችንም ይለያያል። በፍቅር ግንኙነት ላይ ሴቶችና ወንዶች እንዳይግባቡ ትልቅ እንቅፋት ከሚሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ በቋንቋ አለመግባባት ነው። ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ ሁለት ፍቅረኛሞች (ባለትዳሮች) መግባባት ያቅታቸዋል። ‹ተመሳሳይ ቋንቋ እየተናገርን እንዴት አንግባባም?› ይላሉ። ችግሩም ይሄው ነው - ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ ይመስላቸዋል ፤ ግን የሚያወሩት ተመሳሳይ ቋንቋ አይደለም።

እርግጥ ነው ተመሳሳይ ቋንቋ ነው የሚያወሩት፣ ግን የማያግባባ ተመሳሳይ ቋንቋ ነው። ሴቶች ተመሳሳይ ቋንቋውን

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

በቀጥታ የሚጠቀሙበት ለማህበራዊ ህይወትና ለማህበራዊ ግንኙነት ነው። ለፍቅርና ለፍቅር ግንኙነት ግን ሌላ ቋንቋ አላቸው። ወንዶች ይህንን ቋንቋ ካልተማርን ከሴቶች ጋር በፍቅር መግባባት ሁሌም ይከብደናል። መክበድ ብቻም ሳይሆን በቋንቋ ባለመግባባት ልንለያይም እንችላለን።

ቬነሳዊያን(ሴቶች) ስሜታቸውን በቃላት ከመናገር ይልቅ በሰውነት እንቅስቃሴ መግለፅ ይመርጣሉ። ስለዚህ ማርሳዊያን (ወንዶች) የሴቶች የምልክትና የንግግር ቋንቋዎችን ማጥናት ይኖርብናል።

**ምሳሌ**

ሴት ‹ውይ ይበርዳል!› ስትል የብዙ ወንዶች መልስ የሚሆነው ‹ብጣም እንጂ!› ነው። አንድ ሴት ‹ውይ በረደኝ› ስትል ወንዱ ‹እኤም› ካለ ሴቶች የሚናገሩባቸውን ሴትኛ ቋንቋዎች ማንበብ፣ መረዳት፣ መፃፍ፣ መስማትና መናገር አይችልም ማለት ነው።

እንዴት?

በእርግጠኝነት መጀመሪያ ሴቷ ‹በረደኝ› የምትለው በምልክት ቋንቋ ነው። እንደበረዳት በአካላዊ እንቅስቃሴ... በምልክት ቋንቋ ነግራው ማንበብ ሳይችል ሲቀር የበለጠ ግልፅ ለማድረግ በሁለተኛው ቋንቋዋ ‹ውይ በረደኝ› ትለዋለች። ይሄኔ እርሱ ልክ እንደገባው ሰው ዘሎ ‹እኤም› ይላል። በዚህ ጊዜ ሴቷ እንደማይገባው ሲገባት ሦስተኛውን ቋንቋ ትጠቀማለች - ዝምታ።
የሴቶችን ቋንቋ በደንብ መስማት፣ መናገር፣ መፃፍና ማንበብ የሚችል ወንድ ሴቷ መጀመሪያ በምልክት ቋንቋ እንደበረዳት ስትገልፅ በማቀፍ ወይም ጃኬቱን አውልቆ በማልበስ ይመልስላታል።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

በደንብ መስማት፣ መናገር፣ መፃፍና ማንበብ የማይችል… ትንሽ ትንሽ ቋንቋውን የሚሞክር ወንድ ደግሞ ‹ውዬ በረደኝ› ስትል ዘሎ እቅፍ… ጥምጥም ይልባታል፡፡

በምሳሌውና ከምሳሌው ከፍ ብሎ በፃፍኩት ዲስኩር ማለት የፈለግኩት ጠቅለል ብሎ ሲገለፅ… ሴቶች ፍቅራቸውንም ሆነ ስሜታቸውን ለመግለፅ ቀጥተኛ ቋንቋ አይጠቀሙም ነው፡፡ አካላዊ እንቅስቃሴና ጠመዝማዛ ቋንቋ መጠቀም ይቀናቸዋል፡፡

ስለዚህ አካላዊ እንቅስቃሴያቸውንና ቀጥተኛ ያልሆነ ንግግራቸውን ማጥናት ከተቻለም በሁሉም (ምልክት፣ ቀጥተኛ ያልሆነ ንግግርና ዝምታ) ቋንቋዎቻቸው ማስተርስ ወይም ፒኤችዲ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡

ብዙ ወንዶች የምንሰራው ሌላው ስህተት ቬነሳዊያንን (ሴቶችን) የእኛን ቋንቋ እንዲናገሩ ማስገደድ ነው፡፡ ነገር ግን በማስገደድ ቀርቶ በማግባባትም ቢሆን አይሰራም፡፡ ምክንያቱም ቬነሳዊያን ቋንቋቸው እንዲጠፋ አይፈልጉም፤ ወይም ደግሞ ቋንቋቸውን ይወዳሉ፡፡ ስለዚህ ቋንቋቸውን ማጥናት አማራጭ የለውም፡፡

የቬነሳዊያንን ቋንቋ ለመማር ወደ ትምህርት ቤታቸው እንድትገባ የሚያነሳሱ አንዳንድ ወሳኝ ቃላትና ሃረጎችን ልጨምርልህ…

## እሺ በቃ ጥሩ!

- ብዙ ጊዜ በክርክር መሃል ሴቷ ‹እሺ በቃ ጥሩ!› የሚል ቃል ስትናገር አንተ ሞኞ ‹አሸነፍኳት!› ብለህ ልትዝናና ትችላለህ፡፡
- እርሷ እያለች ያለችው ግን … ‹እኔ የምለው ነገር ነው

ትክክል፡፡ ነገር ግን አንተ የማይገባህ ደ** ስለሆንክ ትቼዋለሁ፡፡ አሁን በቃ አፍህን ዝጋልኝ› ነው፡፡

## አምስት ደቂቃ

- ኢትዮጵያ ቡና እና ደደቢት ለዋንጫ ሲጫወቱ በከፍተኛ ጉጉት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጨዋታውን እየተከታተልክ እያለ በመሃል ፍቅረኛህ መጥታ ለ‹አምስት ደቂቃ› ላናግርህ እፈልጋለሁ ስትልህ የመጀመሪያው ግማሽ ጨዋታ ሊጠናቀቅ የቀረውን ደቂቃ የቲቪው ስክሪን ላይ አየት አድርገህ… ዕረፍት ላይ ካለው 15 ደቂቃ አምስት ደቂቃውን፣ ከፈለገችም ሙሉ 15 ደቂቃውን ልታወራት ‹የመጀመሪያው ግማሽ ሊያልቅ የቀረው አምስት ደቂቃ ነው፣ ትንሽ ታገሺኝ› ብለህ ጨዋታውን መከታተልህን ልትቀጥል ትችላለህ፡፡

- የጨዋታው የመጀመሪያው ግማሽ አልቆ ለማውራት ስትመቻች ወሬው ወደ ክርክርና ወደ ጭቅጭቅ ተቀይሮ አምስት ደቂቃ… 10 ደቂቃ… 15 ደቂቃ ይነጉዳል፡፡ የጨዋታው እረፍት አልቆ የጊዮርጊስና የቡና ጨዋታ ይጀምራል፡፡ ከዚህ በኋላ ቀልብህ ወደ ኳሱ ሄዶ ከልብ ላታዳምጣት ትችላለህ፡፡ ይባስ ብሎ ከጨዋታው በኋላ እንቀጥለዋለን ብለህ ወሬውን ልታቋርጠው ትችላለህ፡፡ ሌላ ትልቅ ስህተት፡፡

‹አምስት ደቂቃ› ማርስ ላይ አምስት ደቂቃ ነው፡፡ ቬነስ ላይ ግን ከ30 ደቂቃ እስከ ሰዓታት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ‹አምስት ደቂቃ› ስትልህ ለ30 እና ከዚያ በላይ ደቂቃዎች ተዘጋጅ፡፡

## ምንም

- ስሜትዋ ቀዝቅዞ… አኩርፋ ስታገኛት ‹ምን ሆነሽ ነው የእኔ ቆንጆ?› ብለህ ‹ምንም› ስትልህ ምንም አልሆነችም ብለህ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ልትደመድምና ሶፋ ላይ ጉብ ብለህ ሪሞት ኮንትሮልህን ይዘህ ቴሌቪዥንህ ውስጥ ያሉትን ቻናሎች በሙሉ ለመቆጣጠር… ኮንትሮል ለማድረግ ሊያምርህ ይችላል። ቆይ ተረጋጋ… መጀመሪያ የፍቅር ግንኙነትህን በስርዓቱ ኮንትሮል አድርግ።

- በሴትኛ ቋንቋ ‹ምንም› ማለት ‹ምን ትጠይቀኛለህ… ያደረግከውን ታውቀዋለህ። ጠብቅ ጉድህ ነው!› ማለት ነው። በ‹ምንም› የተጀመረው ወደ ‹አምስት ደቂቃ› ሄዶ በ‹እሺ በቃ ጥሩ!› ሊጠናቀቅ ይችላል።

## ደህና ችግር የለም

- የሆነ ነገር ጠይቃህ እንደማይሆን ወይም እንደማትችል ነግረሃት ‹ደህና ችግር የለም› ስትልህ ባቀረብከው ትንታኔ ተስማምታለች በሚል ለራስህ ‹ፖለቲከኛ ብሆን እኮ አቶ መለስን እተካ ነበር› ብለህ የማሳመን ችሎታህን እያደነቅክ ፈገግ ልትል ትችላለህ።
- የቬነሳዊያን ‹ደህና ችግር የለም› ሲተረጎም ‹ጠብቅ እሰራልሃለሁ› የሚል ዓይነት ዛቻ ነው። ስለዚህ ‹የእኔ ፍቅር ጓደኛዬ ሚዜ ሁኚኝ አለችኝ እኮ ምን ላድርግ?› የሚል ጥያቄ ከነበረ የጠየቀችህ ከሄድክበት ስትመለስ ‹በደንብ ሳስብበት ሚዜ የማትሆኚበትን ምክንያት ማግኘት አልቻልኩም› ብለህ አስደስታት። አሊያም ጨንገራህን አስነስቶ ለሚያቃጥል ቆንጆ ብቀላ ተዘጋጅ።

## ይሄን ሥራ የግድ አሁን መስራት አለብህ?

- የሆነ ነገር በመሥራት ላይ እያለህ ‹ማሬ… ይሄን ሥራ የግድ አሁን መስራት አለብህ?› ስትልህ ዘና ብለህ ‹አዎ› በሚል ጀምረህ አስፈላጊነቱን በብዙ ቃላት ልትዘረዝር ትችላለህ።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

- እርሷ እያለችህ ያለችው ግን ‹ሌላ ዕቅድ አለኝ ኮምፒዩተርህን ዘጋጋና እንሂድ› ወይም ‹እርሱን ተወውና ለእኔ ጊዜ ስጠኝ› ነው።

## ውሳኔው ያንተ ነው

- የሆነ ነገር መግዛት ፈልገህ ወይም የሆነ ቦታ መሄድ አስበህ ስትነግራት...በተለያዩ ምክንያቶች እንደማይሆን ታስረዳሃለች። አንተ ግን ድርቅ ብለህ ለማሳመን ትሄዳለህ... በዚህ መሃል ‹ውሳኔው ያንተ ነው› ልትልህ ትችላለች። አንተ ቂሎ የመወሰን ሙሉ ስልጣን ተሰጠኝ በሚል ያሰብከውን ለማድረግ ትወስናለህ።

- በሴትኛዋያን ቋንቋ ‹ውሳኔው ያንተ ነው› ማለት ‹የፈለግከውን አድርግ› ማለት አይደለም። ይልቁንም ‹አድርገውና እንተያያለን› ወደሚል ይቀርባል! ግን ከዚህ የከፋም ሊሆን ይችላል... በእውነቱ ምን ሊደርስብህ እንደሚችል መገመት ከባድ ነው።

## ዛሬ ቀኑ ምን እንደሆነ አውቀሃል?

- ‹ዛሬ ቀኑ ምን እንደሆነ አውቀሃል?› ይሄ በጣም አደገኛ ከሚባሉት ጥያቄዎች መካከል አንዱ ነው። ዘለህ ‹... አዎ ሰኞ መጋቢት 3 ነው› በሚል ከመመለስህ በፊት በደንብ አስብ።

- እሷ የምትጠብቀው መልስ ‹አልረሳሁትም የእኔ ቆንጆ› የሚልና እርሱን ተከትሎ ደግሞ ሰርፕራይዝን ነው። ምክንያቱም ቀኑ የእርሷ ልደት ነው ወይም ሁለታችሁ የተገናኛችሁበት ቀን ነው! አሊያም ጋብቻችሁን የፈፀማችሁበት አምስተኛ ዓመት ነው... ብቻ ልታስታውሰው ወይም ልትነቀሰው የሚገባህ ለሁለታችሁ ትልቅ ትርጉም ያለው ዕለት መሆኑን ነው።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

## ላናግርህ እፈልጋለሁ

- ከጓደኞችህ ጋር ስብስብ ብላችሁ በመጫወት ላይ እያላችሁ ሊሆን ይችላል… ወይም በስልክም ሊሆን ይችላል ‹ላናግርህ እፈልጋለሁ› ስትልህ የፍቅር ወሬ ከጠበቅክ በጣም ተሳስተሃል። ‹ላናግርህ እፈልጋለሁ› ማለት ምናልባትም አንዲት ሴት ሁለት የአማርኛ ቃላት ተጠቅማ የምትሰራው እጅግ በጣም አደገኛው ሃረግ ሳይሆን አይቀርም።

ስለዚህ ያደረግከውን ነገር አስብና ለትልቅ ስብሰባ… ጭቅጭቅ ወይም ክርክር ተዘጋጅ። ምክንያቱም ባልተጠበቀ ሰዓትና ሁኔታ እነዚህን አስፈሪ ቃላት ከተጠቀመች ፈታኝ ጊዜ ይጠብቅሃልና።

ለጥንቃቄ እንዲመችህ ከባድና አደገኛ ቃላትና ሃረጎችን ብቻ ዘረዘርኩ እንጂ ሴቶች ፍቅራቸው፣ መልካም ስሜታቸውና ፍላጎታቸውን ለመግለፅም ቀጥተኛ ያልሆኑ ቃላትና ሃረጎች ይጠቀማሉ። ልክ እንደ ‹ውይ በረደኝ› ዓይነት።

ስለዚህ ሴቶች የሚናገሩትን እንዲሁ እንደወረደ ሰምተህ ከመተርጎምና ፈጣን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በደንብ አድምጠህ ለመረዳትና ሰምና ወርቁን ለመለየት ሞክር።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

# አልፋ ወንድ ምን ዓይነት ወንድ ነው?
## 33 የአልፋ ወንድ ብቃቶች

‘ሃብትና ፍቅር ለጠንካራ ሰው ያደላሉ’

አቪድ

‹አልፋ ወንድ› ሁሉም ወንዶች መሆን የሚመኙትና ለደርሱበት የሚፈልጉት የወንዶች ከፍተኛ ደረጃ ነው። አልፋ ወንድ መሆን የወንዶች ትልቁ የስኬት ምዕራፍ ነው። አልፋ ወንድነት ሴቶችን በቀላሉ የመማረክ ጉዳይ ብቻ አይደለም። አልፋ ወንድነት ከዚያም በላይ ርቀትና ጥልቀት ያለው የወንድ ልጅ የህይወት፣ የዕውቀት፣ የስኬት፣ የጥንካሬ፣ የብስለት፣ የፍልስፍና፣ የስብዕና… ምጥቀት ነው።

ሁሉም ወንድ ‹አልፋ› ሊያደርገው የሚችል እርሾ በውስጡ ይዞ ስለሚወለድ ወንድ በሙሉ ‹አልፋ› የመሆን ዕድል አለው። ነገር ግን እርሾውን ተጠቅመው ራሳቸውን ወደ ‹አልፋ› ደረጃ የሚያሳድጉት ጥቂቶቹ ናቸው።

አብዛኞቹ ወንዶች ዕድሉ የሌላቸው/ያልነበራቸው ይመስል ዕጣ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ፊንታቸው በአልፋ ወንዶች መደነቅ ሆኖ ይቀራል።

‹አልፋ ወንድ› ወንዶች ሁሉ የሚያደንቁት ወንድ ብቻ ሳይሆን ሴቶች በሙሉ የሚመኙትና የሚንበረከኩለት ዓይነት ነው።

አንድን ወንድ ‹አልፋ ወንድ› ሊያስብሉት የሚችሉት ብቃቶች ምን ምንድናቸው? የተመረጡት 33 ብቃቶች የሚከተሉት ናቸው፡

1. አልፋ ወንድ ተስፋ አይቆርጥም… የጀመረውን ሳይጨርስ እጅ አይሰጥም።
2. አልፋ ወንድ ራሱንና ቤተሰቡን መንከባከብና መጠበቅ ይችላል።
3. አልፋ ወንድ በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጤናውንና የሰውነት አቋሙን ይጠብቃል። በመሆኑም በቀላሉ ሴቶችን መማረክ የሚችል ተክለ ሰውነት አለው።
4. አልፋ ወንድ ዓላማውን ለማሳካት በድፍረትና በጥንካሬ ይሰራል። ሪስክ ይወስዳል። በመሆኑም ስኬታማ ነው።
5. አልፋ ወንድ ጨዋታ አዋቂ ነው። አጣፍጦ ማውራት ይችላል። ወሬውን ለመስማትም ሰዎች ይከቡታል።
6. አልፋ ወንድ በንባብና በተለያዩ ልምዶች ብዙ ታሪክ ያካብታል። የብዙ ሰዎችን ቀልብ የሚስቡ በርካታ የጀብድ ታሪኮች አሉት።
7. አልፋ ወንድ በራሱ ላይ ይቀልዳል። ቀድሞ ራሱ ላይ ስለሚቀልድ ሰዎች እርሱ ላይ ለመቀለድ ይቸገራሉ።
8. አልፋ ወንድ ትሁት ነው። ስኬታማ ነኝ፣ ማራኪ ነኝ፣ ጀብደኛ ነኝ፣ ዝነኛ ነኝ… ብሎ አይኩፈስም። ሰው አክባሪና የሰው ሃሳብና አስተያየት የሚቀበል ትሁት ነው።
9. አልፋ ወንድ ዕውቀት ይወዳል። ሁልጊዜ ተማሪ ነው። ጠቅላላ ዕውቀት አለው። ከስፖርት እስከ ፖለቲካ፣ ከግብርና እስከ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

መዝናኛ፤ ከታሪክ እስከ ቴክኖሎጂ፤ ከአይቲ እስከ ጂኦግራፊ... በመሳሰሉ ጉዳዮች ከትንሽ እስከ አዋቂ፤ ከቂስ እስከ ሼክ፤ ከገበሬ እስከ ፕሮፌሰር... ካለው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ማውራት ይችላል።

10. አልፋ ወንድ ሁሉም አብሮት ጊዜ ለማሳለፍ... ለመጫወት የሚመኘው ዓይነት ሰው ነው።

11. አልፋ ወንድ ቁጥብ ነው። የራሱን ድምፅ ለመስማት አያወራም። ለቃላት ክብር አለው... ለቃላት ይሳሳል። በከንቱ አያወራም። ሲያወራ በምክንያትና ማውራቱ አስፈላጊ መሆኑን ሲያምን ብቻ ነው። ጮክ ብሎ ማውራት አይወድም። ተረጋግቶ ያወራል፤ ሲያወራም ይደመጣል።

12. አልፋ ወንድ የዓላማ ሰው ነው። ዓላማውን ለማሳካት ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል። በዚህ ዓለም የመኖሩን ምክንያት በሚገባ ተረድቶ ወደዚህች ምድር የመጣበትን ምክንያት ለማሳካት ከልብ ይሠራል። በዓላማው ፅናት ያለውና ላመነበት የሚቆም ሰው ነው። ጠንካራ ሠራተኛ ነው።

13. አልፋ ወንድ አያማርርም። ሁሉም ነገር በቁጥጥሩ ስር እንዳልሆነ ያምናል። ስለሆነም የሚችለውን ያህል ይሠራል... የማይችለውን ለመቻል ይጥራል እንጂ አያማርርም። ስለ ነገ አይጨነቅም፤ ምክንያቱም ዛሬን በመጠቀም ይጠመዳል።

14. አልፋ ወንድ ነገር ጭሮ ወደ ፀብ አይገባም። አይሰዳደብም። ሰዎች ለነገር ሲፈልጉት በትዕግስት ለማሳለፍ ይጥራል። ያዙኝ ልቀቁኝ አይልም። ራሱን ለመከላከል ሲል ብቻ ለመደባደብ ይገደዳል።

15. አልፋ ወንድ የራሱ የሆነ የአለባበስ ስታይል አለው። የሚያምርበትን አለባበስ ያውቃል። ለራሱ ደስታ ሲል ጥሩ የአለባበስ ስታይል ይከተላል። በአለባበሱ ሰዎችን ለመማረክ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

አሊያም ከሴቶች አድናቆት ለማግኘት አያስብም፤ ነገር ግን በአለባበሱ ሰዎች ያደንቁታል… ይከተሉታል።

16. አልፋ ወንድ ሴቶችን ያከብራል። ለሴቶች የሚያስፈልገውን ትኩረትና ክብር ይሰጣል። በር ይከፍትላቸዋል። ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ህልማቸውንና ራዕያቸውን እንዲያሳኩ የቻለውን እገዛ ያደርጋል።

17. አልፋ ወንድ ራሱን ያከብራል፤ ለዓላማው ቅድሚያ ይሰጣል። ሁሉንም ለማስደሰት አይሞክርም። ማንም ከልክ በላይ ላዩ ላይ እንዲፈነጭበት አይፈቅድም… የሚወዳት ሴትም ጭምር። በማንም ቁጥጥር ሥር መሆን አይፈልግም። ቀናተኛና የመቆጣጠር ሱስ ያላትን ሴት አጠገቡ አያስጠጋም።

18. አልፋ ወንድ አቋራጭ አይወድም። ወንጀል ሰርቶ፤ ሰዎችን ጨፈላልቆ መከበርና ስኬታማ መሆን አይፈልግም። ከስኬት በፊት የሞራልና የማህበረሰባዊ እሴቶችን ያስቀድማል

19. አልፋ ወንድ ለጋስ ነው። ብቻውን ስኬታማ ለመሆን አይስገበገብም። የስኬት መንገዱን ለሰዎች ያሳያል። እውነተኛ እርካታ የሚገኘው በስኬት ሳይሆን ለጋሲ ትቶ በማለፍ እንደሆነ ይረዳል። ሌጋሲ የሚገኘውም ሌሎች የተሻለ ዕድል እንዲያገኙ በማገዝ ነው የሚል እምነት አለው።

20. አልፋ ወንድ መሪ ነው። የማያደርገውን ሰዎች እንዲያደርጉት በማዘዝ የሚመራ ሳይሆን ሰርቶ… አድርጎ በማሳየት… በምሳሌ የሚመራ ትክክለኛ የአመራር ብቃት ያለው መሪ ነው።

21. አልፋ ወንድ አዲስ ነገር መሞከር ይደፍራል። ሌሎች ሰዎች በሚፈሩት አዲስ መንገድ መሄድ ይደፍራል። ‹ፍርሃትንና ስጋትን ተቋቁሞ በአዲስና በሚፈራ መንገድ ተጉዞ ድል ማግኘት ይቻላል› ብሎ ያምናል። ከስጋትና ፍርሃት ጀርባ ጥሩ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ዕድል አለ የሚል ጠንካራ መንፈስ አለው፡፡ ትችትና ውድቀትን አይፈራም፡፡ ደጋግሞ መሞከር ለስኬት እንደሚያበቃ ይረዳል፡፡

22. አልፋ ወንድ በራሱ ይተማመናል፡፡ ልበ ሙሉ ነው፡፡ ሰዎች ለሚሉት ነገር ፍፁም ቦታ አይሰጥም፡፡ የመሰለውን፣ ያመነበትን ያደርጋል፡፡ በራሱ ህይወት ላይ ከእርሱ በላይ የሚመለከተው ሰው እንደሌለ ያውቃል፡፡ በራሱ ይተማመናል ብቻ ሳይሆን በራስ የመተማመን ስሜት ተምሳሌት ጥምር ነው፡፡

23. አልፋ ወንድ ስሜታዊ አይደለም፡፡ በስሜት አይወስንም፡፡ በስሜት ማንኛውንም ነገር አያደርግም፡፡ ሰከን ብሎ ያስባል፤ ተረጋግቶ ይወስናል፡፡ በጥቃቅን ነገሮች የሚነጣጣ ሰው አይደለም፡፡

24. አልፋ ወንድ የውሳኔ ሰው ነው፡፡ ውሳኔ ከሌሎች አይጠብቅም፡፡ በህይወት መድረስ የሚፈልግበትን ደረጃ ያውቃል... እዚያ ለመድረስም ጠንቅቆ ይሰራል፡፡ ያቀደውን ለማሳካት ያለመታከት ይሰራል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ከእቅዱ ዝንፍ አይልም፡፡

25. አልፋ ወንድ የመፍትሄ ሰው ነው፡፡ ችግሮች ሲፈጠሩ በችግሮች ከመሸበር ይልቅ ፈጥኖ ወደ መፍትሄ ይሄዳል፡፡ ለችግሮች መፍትሄ በማምጣት ችሎታውም በሚሰራበት ቦታና በአካባቢው ሰዎች ይከበራል፡፡ ሰዎች ችግር ሲያጋጥማቸው ያማክሩታል፡፡ እርሱም አያሳፍራቸውም፡፡

26. አልፋ ወንድ ይመርጣል እንጂ አይመረጥም፡፡ ሙሉ ጊዜውን የሚያሳልፈው የህይወት ዓላማውን ለማሳካት ስለሆነ እንዲሁ በቀላሉ የሚገኝ ሰው አይደለም፡፡ ሴቶችን ለማደን... ሴቶችን ለመማረክ አይጨነቅም፡፡ ይልቁንም ሴቶች እርሱን ለማጥመድ... ለመማረክ ይጥራሉ፡፡ በአልፋነቱ በርከት ያሉ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሴቶች ስለሚፈልጉትም የፈለገውን የመምረጥ ዕድልና ኃይል አለው።

27. አልፋ ወንድ ሲሳሳት ስህተቱን ያምናል፤ ይቅርታ ይጠይቃል። ሌእ አልሳሳትም የሚል ትዕቢት የለውም። ሲሳሳት ስህተቱን ለማመንና ይቅርታ ለመጠየቅ ችግር የለበትም። ሰዎችን ማክበርታታትና ማስደሰት የህይወቱ አንድ መርህ ነው። ነገር ግን ተሳስቶ ሰው ካስቀየመና መሳሳቱን ከተገነዘበ በሰዎች ፊት ያስቀየመውን ሰው ይቅርታ ለመጠየቅ አያመነታም። ያስቀየመውን ሰው መኖሪያ ቤቱ ወይም መስሪያ ቤቱ ድረስ ሄዶ ይቅርታ ከመጠየቅም ወደኋላ አይልም።

28. አልፋ ወንድ የሰዎች ይሁንታና ማረጋገጫ አይፈልግም። የደስታውም፣ የስኬቱም፣ የውድቀቱም፣ የዕድገቱም ዋና ተዋናይ ራሱ ነው። ለመደሰት የሰዎች ይሁንታና ማረጋገጫ አያስፈልገውም። ለሚያጋጥሙት እንቅፋቶችና ውድቀቶችም ሌሎች ሰዎችን ተጠያቂ አያደርግም። የስኬቱም የውድቀቱም ምክንያት ራሱና ራሱ ብቻ ነው።

29. አልፋ ወንድ ሰው ይመርጣል። የመዝናኛ ጊዜውን ከማን ጋር ማሳለፍ እንዳለበት በጥንቃቄ ያቅዳል። ስለሆነም አብረውት እንዲሆኑ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ይመርጣል። ጊዜውን ለማሳለፍ የሚመርጣቸው ሰዎች እንደእርሱ አልፋ ደረጃ ላይ ያሉ አሊያም ከአልፋ አልፈው የሄዱ ናቸው። በመዝናኛ ጊዜውም ቢሆን ከእኩዮቹ አሊያም በዕድሜ ወይም በእውቀት ከእርሱ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር ጊዜውን በማሳለፍ መማር ይፈልጋል።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

አመለካከቱ፡ በጣም ቀና (ፖዘቲቭ) ነው፡፡ ችግሮች ለመልካም መፍትሄዎችና ፈጠራዎች ምክንያት ናቸው የሚል አመለካከት አለው፡፡ ስለሆነም ችግሮች ባጋጠሙት ቁጥር ከማማረር ይልቅ መፍትሄዎችን ማፈላለግ... ከችግሮች ጀርባ ያሉ መልካም አጋጣሚዎችን ማየት ይመርጣል፡፡

31. አልፋ ወንድ ሰዓት አክባሪ ነው፡፡ ጊዜ የስኬታማና የደስተኛ ህይወት ቁልፍ መሆኑን ስለሚያውቅ ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል፡፡ የራሱን ጊዜ የሚያባክንበት ሰው እንደማይወድ ሁሉ እርሱም የሰዎችን ጊዜ ማባከን አይወድም፡፡ ጊዜውን በአግባቡ ስለሚጠቀም ለማንኛውም ነገር አይጣደፍም፡፡ሁሉንም ነገር በእርጋታ ያከናውናል፡፡ ቀጠሮ ያከብራል፡፡ ሰዎችም ቀጠሮ እንዲያከብሩ ይፈልጋል፡፡

32. አልፋ ወንድ የጥንካሬ ምሳሌ ነው፡፡ ያሉት ብዙ ብቃቶች የእውነተኛ ጥንካሬ ተምሳሌት እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ በብቃቶቹ ያረጋገጠው ጥንካሬ ቤተሰቡ፣ ጓደኞቹ፣ ባልደረቦቹ፣ ሠራተኞቹ... በእርሱ እንዲተማመኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ሴቶችም ከእርሱ ጋር ሲሆኑ ምንም ዓይነት ችግር እንደማያጋጥማቸው ስለሚያውቁ ምቾት ይሰማቸዋል፡፡

33. አልፋ ወንድ ‹አልፋ ወንድ› ለመሆን አይሞክርም፡፡ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያደርገው ‹አልፋ ወንድ› ለመሆን ብሎ አይደለም፡፡ የሚያደርገውን የሚያደርገው ስለሚያስደስተው፣ ለህይወቱ አስፈላጊ መሆኑን ስለሚያምንበትና የተሳካና አስደሳች ህይወት መኖር ስለሚፈልግ ነው፡፡ በስራው ስኬታማ የሚሆነው ጠንክሮ የመስራት ጥልቅ ፍቅር ስላለው ነው፡፡ ሰዎች የተሻለ ህይወት እንዲኖራቸው የበኩሉን ሚና የሚጫወተው ከልብ ሰዎችን መርዳት ስለሚያስደስተው ነው፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ለቆመለት ዓላማ እስከ መጨረሻው የሚታገለው ተስፋ መቁረጥና መሸነፍ ስለማይወድ ነው።

ለወደደው የሚሸነፍ ርህሩህ ልብ እንዲሁም ያቀደውን ለማሳካት እስከ ጥግ የሚዋጋ ጠንካራ ልብ አለው።

በተፈጥሮ አሊያም በሂደት ያካበታቸው ብቃቶቹ ተደማምረው ‹አልፋ ወንድ› ደረጃ ላይ ያደርሱታል እንጂ እርሱ ‹አልፋ ወንድ› በመሆን ሴቶችን የመማረክ ውድድር ውስጥ አይገባም።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

# የወደድካትን እንዳታገኝ የሚያደርጉህ ሁለት ቀንደኛ ጠላቶች

‘ ፍቅር የሌለው ህይወት በፀሃይ ብርሃን እጦት የጠወለጉ አበቦች የሞሉት መናፈሻ ነው ’

ኦስካር ዋይልድ

የወደድካትን ሴት ቀርበህ በማነጋገር... ባሉህ በርካታ ብቃቶች ማርከህ ፍቅረኛህ... ባለቤትህ እንዳታደርጋት የሚያደርጉህን ሁለት ቀንደኛ ጠላቶችህን ፍለጋ ብዙ አታስብ፤ አጠገብህ ናቸው። ‹ጠላት ከሩቅ አይመጣም› እንደሚባለው እነዚህ ሁለት ቀንደኛ ጠላቶችህ በአንተ ውስጥ እየኖሩ አንተን የሚያጠቁ ሲሆኑ ‹ፍርሃት› እና ‹ዓይናፋርነት› ይባላሉ።

## ጠላት ቁጥር 1፡ ‹እምቢ ብትለኝስ› የሚል ፍርሃት

### ምሳሌ፡ የአንድ መንደር አጭር ታሪክ...

አንድ ልጅ ነበር... ሲኖር ሲኖር ሰፈራቸው ውስጥ ከነበረች ቆንጆ ልጅ ጋር የዓይን ፍቅር ያዘው። በቀን ቢያንስ አንድ ጊዜ ካላያት ይታመማል። በህይወት የመኖሩ ትርጉም እርሷን ማፍቀር እስኪመስል ድረስ በውኑም በህልሙም የሚያስበው እርሷን ነው።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ልክ የሚተነፍሰውን አየር ያህል ታስፈልገዋለች፡፡

ካላየት አየር ያጥረዋል፡፡ ለቆንጆዋ ልጅ ያለውን ጥልቅ ፍቅር መንደሩ ሁሉ ያውቀዋል፤ ነገር ግን የእርሱ በፍቅሯ መክነፍና መንገዳገድ ያን ያህል የመንደሩ ሰዎችን ሊያነጋግር አልቻለም፡፡ ምክንያቱም በቆንጆዋ ፍቅር የተንበረከከው የመንደሩ ወንድ እርሱ ብቻ አልነበረም፡፡

የመንደሩ ወንዶች (ያገቡም) ጭምር ጠዋት ጠዋት ‹ፀሃይ እሞቃለሁ› በሚል ሰበብ ቆንጆዋ ወደ ሥራ ስትሄድ ለማየት የመንደሩ ዋና መንገድ ላይ ይኮለኮላሉ፡፡

አብዛኞቹ ልክ በህልማቸው እንዳዩት እንድትስቅላቸው፣ ለይታ እንድታናግራቸው፣ እንድታቅፋቸው እንድትስማቸው ይመኛሉ፡፡ በህልማቸው የተመለከቱትና በዕውን የሚሆነውን ለማዛመድ (Sinchronized ለማድረግ) ተስፋ አድርገው… በርጩማቸውን ደጅ አውጥተው…(ቦርጫሞቹ)ቦርጫቸውን ዘርግፈው ቁጭ ብለው ይጠባበቃሉ፡፡

የፀጋዬ እሸቱ ዘፈን ለእርሷ የተዘፈነ በሚመስል ሁኔታ የመንደሩ ቆንጆ ‹ሰበር፤ሰካ› እያለች የመንደሩን መንገድ ትሞላዋለች፡፡ የመንደሩ ወንዶች አፋቸውን ከፍተው… አንዳንዶቹ ለሃጫቸውን እያዝረከረኩ በጎመጁ ዓይኖቻቸው ይሸኙዋታል፡፡ አንዳንዱ በሚስቶቻቸው ድንገተኛ ጥፊ ተነቃቅተው ወደ ቤታቸው ይገባሉ፡፡

የዚህ ታሪክ ዋና ገፀ ባህርይ የሆነው ልጅና የመንደሩ ግልፅና ስውር አፍቃሪዎች በፍርሃትና በዓይናፋርነት ተሸብበው ቆንጆዋን ልጅ ጠዋት እየሸኙ ማታ ሲቀበሉ በርካታ ወራት፣ ዓመታት ካለፉ በኋላ አንድ ቀን እንደለመዱት ምሽት ወደ ቤቷ ስትገባ በዓይኖቻቸው እቀባበል አድርገውላት… በህልማቸው ከእርሷ ጋር ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ ለመኘታ ወደየቤታቸው ሲገቡ አስደንጋጭ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ነገር ገጠማቸው፡፡ ለቆንጆዋ ልጅ ሰርግ የተጠሩበትን የጥሪ ካርድ አገኙ፡፡ ባለትዳሮቹ ሚስቶቻቸው የጥሪ ካርዱን በደስታ ሲሰጧቸው ለመደንገጥና ለመናደድ ዕድል አላገኙም፡፡

የታሪካችን ዋና ገፀ ባህርይ የሆነው አፍቃሪ ግን ከመደንገጥና ከመናደድ አልፎ ራሱን የማጥፋት ሙከራ አደረገ፡፡ በረኪና ጠጥቶ ሆስፒታል ተወሰደ፡፡ ለሰዓታትም ቢሆን ከቆንጆዋ ልጅ ሰርግ ጋር የመንደሩ የወሬ ርዕስ ለመሆን ዕድል አገኘ፡፡ ሆስፒታል ገብቶ ህክምና ከተደረገለት በኋላ ድኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ልጅቷን አይደለም ለማግባት ለማነጋገር ያልታደለው ይህ ልጅ ቢያንስ በህይወት ቆይቶ ሰርጉን ላይ ለመገኘት ቻለ፡፡

የቆንጆዋ ልጅ ሰርግ ለመንደሩ ወንዶች ሁሉ አጓጊ ነበር… ሁሉም እርሷን የሚያገባውን ደፋር፣ መልከ መልካምና ዕድለኛ ወንድ ለማየት ሰፍ አሉ፡፡ የሰርጉ ቀን ደርሶ ሙሽራው ሙሽሪትን (የመንደሯን ቆንጆን) ለመውሰድ ሲመጣ የመንደሩ ወንዶች ሁሉ እርሱን ለማየት ተሰባበሩ፡፡

ሙሽራው ከመኪናው ሲወጣ ከጠበቁት ፍፁም የተለየ ነው፡፡ እነርሱ እንደጠበቁት ረዥም፣ መልከ መልካም… ሞዴል መሳይ አይደለም፡፡

ይሄን ያህል የተለየ ማራኪ መልክ የሌለው አጭር ሰው ነበር፡፡ ሁሉም በመገረም ‹ብጣም ሃብታም መሆን አለበት› አሉ- ለራሳቸው፡፡ ቀጥለውም የኩባንያዎቹን ብዛትና የሃብቱን መጠን ለማወቅ በአካባቢያቸው የነበሩ ሰዎችን ጠያየቁ፡፡ ነገር ግን ሙሽራው እንደገመቱት ባለሃብት ሳይሆን በአንድ የግል ባንክ ተቀጥሮ የሚሰራ ወጣት ነው፡፡ ሁሉም ተቆጩ… ተናደዱ… አበዱ፡፡

የታሪካችን ዋናው ገፀ ባህርይ በሁኔታው ከተቆጩትና ካበዱት መሃል አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ ቆንጆዋ ልጅ ልትፋታ ትችላለች በሚል ሁለት ዓመት ከጠበቀ በኋላ ተስፋ ቆረጠ፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

በመሆኑም እስከነ መፈጠሯ እንኳ ልብ ብሏት የማያውቅ አንዲት የመንደሩ ልጅ ለፍቅር ስትጠይቀው ጥያቄዋ ላይ ዘሎ ተሳፈረበትና አገባት። እናም ፍቅር አልባ ህይወት በመምራት ላይ ይገኛል።

ይህ ታሪክ የአንድ መንደር ወንዶች ብቻ ሳይሆን የብዙ የዓለማችን ወንዶች እውነተኛ ታሪክ ነው።

የታሪካችን ዋና ገፀ ባህሪና አጃቢዎቹ (የመንደሩ ወንዶች) የሌላቸው... ቆንጆዋን ልጅ ያገባው የባንክ ተቀጣሪው ወጣት ያለው ነገር ምንድነው? መልሱ ቀላል ነው... ‹ድፍረት› ነው። የመንደሩ ወንዶች ቆንጆዋን ደፍረው ከማናገር ይልቅ ስለ እርሷ ማለም፣ ጠዋትና ማታ በዓይን መሸኘትና መቀበልን ምርጫቸው አድርገዋል። ያ በመልኩና በገቢው የተሳለቁበት ወጣት ግን እንደእነርሱ ቆንጆዋን ቀርቦ ለማናገር አልፈራም። ወንዶች ቆንጆ ሴቶችን ከመፍራታቸው የተነሳ የሚያምሩ ሴቶች ደፍሮ የሚያናግራቸውን ወንድ የሚያጡበት ጊዜ ቀላል አይደለም። ስለሆነም ልክ ታሪኩ ላይ እንዳየነው ‹ፈሪና ዓይናፋር ወንዶች› እየጎመጁ ቆንጆዎቹን ቀን በዓይናቸው ሌሊት በህልማቸው ሲያዩ እንደ ሙሽራው ዓይነት ደፋር ወንዶች ግን ቆንጆዎቹን ያነጋግሩዋቸዋል፣ ይዳስሷቸዋል፣ ይስሟቸዋል፣ አቅፈዋቸው ያድራሉ...።

## የሚያስፈራው ምንድነው?

ሰዎች የሚወዱትን ሰው ቀርበው በማናገር... በመማረክ... አፍቅረው በማግባት ጥሩ የፍቅርና የደስታ ህይወት ከመኖር ይልቅ የማይወዱት ሰው ላይ ወድቀው ፍቅርና ደስታ አልባ ህይወት እንዲገፉ የሚያደርጋቸው ነገር ‹እምቢ እባላለሁ› የሚል ፍራቻ ነው።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ወንዶች ሲጀመር በጣም ቆንጆ የሆኑና የወደድናቸውን ሴቶች እንፈራለን። በመቀጠል ደግሞ ‹እምቢ ብትለኝስ› የሚል ከግል ክብር ጋር የተቀላቀለ ፍርሃት አለ። ብዙ ወንዶች ሴት ጋር ቀርበው ስልክ ጠይቀው እምቢ ከተባሉ እንደ ትልቅ ውርደት ያዩታል። በመሆኑም ጠይቆ ከመዋረድ በአጉል ኩራት በፍቅር እየተቃጠሉ መኖርን ይመርጣሉ። የሚወዷቸው ሴቶችም በሌሎች ወንዶች እጅ ይገባሉ።

‹እምቢ ብባልስ› ከሚለው ፍርሃት ለመውጣት የሚረዱ ሰባት ወሳኝ ምክንያቶችን እንመልከት:

## 1. ህይወት አልጋ በአልጋ አይደለችም

- ህይወት ላይ የተመኘኸውን ነገር ሁሉ አታገኝም። የምትፈልገው ነገር ሁሉ እንዳቀድከውና እንዳሰብከው አይሆንም። የጠየቅከው ነገር በሙሉ በምትፈልገው መልኩ አይመለስልህም። ሌላው ቀርቶ ሰላም ያልከው ሰው በሙሉ ሰላም ላይልህ ይችላል። ነገር ግን የተመኘሁትን አላገኘሁም... የፈለግኩት አልተሳካም... የጠየቅኩት ሁሉ አልተመለሰልኝም ብለህ መኖርህን አታቆምም። ምኞትህን ለማሳካት፣ ፍላጎትህን ለማሟላት ትጥራለህ። ህይወት ይቀጥላል።

- የሽያጭ ድለላ (ሴልስ) የሚሰሩ ሰዎችን አስባቸው... ዕቃ ወይም ቤት አሊያም አክሲዮን ለማሻሻጥ ብዙ ሰዎችን ያናግራሉ። ቀኑን ሙሉ መቶ ስልክ ደውለው አንድም ላይሳካላቸው ይችላል። ብዙ ሰዎች ስልክ አያነሱላቸውም፣ አንስተው ‹አሁን ሥራ ላይ ነኝ ማውራት አልችልም› የሚሉ፣ ካዳመጡ በኋላ ‹የመግዛት ፍላጎት የለኝም› የሚሉ ያጋጥሙዋቸዋል። ነገር ግን ተስፋ ቆርጠው ሥራውን አይለቁም። ይልቁንም የአነጋገር ዘይቤያቸውን

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

አሻሽለው በሚቀጥለው ቀን ለመሞከር ያቅዳሉ። በተደጋጋሚ በመሞከርም አንድ ቀን ትልቅ አክሲዮን፣ ቤት አሊያም መኪና በማሻሻጥ የድካማቸውን ዋጋ ያገኛሉ።

- ማንኛውንም ነገር ደጋግሞ መሞከር ብቁ ያደርጋል። ስለዚህ ሴቶችን በተገኘው አጋጣሚ መተዋወቅና ማነጋገር የመተዋወቅና የማነጋገር ችሎታህን ያዳብርልሃል። አንዲትን ሴት ለማነጋገር ስትነሳ መቶ በመቶ በደስታ ተቀብላ ስልክ ቁጥሯን ትሰጠኛለች ብለህ አትጠብቅ። መቶ በመቶ ጠብቀህ ስትሄድና እንዳሰብከው ሳይሆን ሲቀር ሊከፋህ ይችላል። አነስተኛ ግምት ይዘህ ቀርበሃት ውጤቱ እንደምትፈልገው ባይሆንም ብዙ ቅር አይልህም። ሞክርከ፤ አልተሳካም በቃ።

## 2. የሞከረ ይሳካለታል… ድፍረት ማራኪ ነው

- በዓለም ላይ ያሉ ስኬቶች በሙሉ የሙከራ ውጤቶች ናቸው። ስኬት ነፍስ ዘርቶ እጃቸውን አጣምረው ወደተቀመጡ ሰዎች አይሄድም። ስኬትን ጠፍጥፈው የሚሰሯት የሚሞክሩ ሰዎች ናቸው። ሁለት ፍቅረኛሞች እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲሄዱ ካየህ ለዚያ ያበቃቸው የአንዳቸው ሙከራ… የአንዳቸው ድፍረት ነው።

- ‹እምቢ ብትለኝስ› ከሚል ፍራቻ ተላቀህ በድፍረት አንዲትን ሴት ስታናግራት ስልክ ቁጥሯን ባትሰጥህ እንኳን ድፍረትህን ማድነቋ አይቀርም። እናም ወይ ሌላ ጊዜ ስታገኛት የተሻለ ፍላጎት ታሳይሃለች፤ አሊያም ድፍረትህን ለጓደኞችዋ ነግራ ፕሮሞት ታደርግሃለች። ምክንያቱም ድፍረት በራሱ የሴቶችን ስሜት ይማርካል።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## 3. ዓለም በሙሉ ፊቱን አያዞርብህም

- አንድ… ሁለት… ሦስት ሴቶች ስላላናገሩህ ወይም ስልካቸውን ስላልሰጡህ መጨነቅ የለብህም:: ጥቂት ሴቶች ፊት ስላልሰጡህ ዓለም በሙሉ ፊቱን እንዳዞረብህ ዓይነት ስሜት ሊሰማህ አይገባም:: ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ከጓደኞችህ መሃል አንተ ተለይተህ በድፍረት ሴቶችን በማናገርህ ብቻ ከጓደኞችህ የተሻልክ ነህ:: ጓደኞችህም ባንተ ድፍረት ይቀናሉ::

## 4. ያንተ ‹እምቢ መባል› ዜና አይሆንም

- የወደድካት ሴት ከቤቷ ስትወጣ ጠብቀህ ልታናግራት ሞክረህ ዘግታህ ስላለፈች ወይም መንገድ ላይ አንዷ ደስ ብላህ አቁመህ ስልኳን ጠይቀሃት እምቢ ስላለችህ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ዜና ሆኖ አይወጣም:: ስለዚህ እንደ ትልቅ ጉዳይ አካብደህ አትየው:: ይልቅ ደፍረህ ብታናግራት ዕድሜ ልክ ደስታና ፍቅር እየሰጠችህ የምትኖር ባለቤትህ ልትሆን ትችላለች::

## 5. ብራድ ፒትም ‹እምቢ› ተብሏል

- የፊልም ተዋናዩ ብራድ ፒት በPeople መፅሔት ሁለት ጊዜ ‹አማላይ ወንድ› ተብሎ የተመረጠ የአልፋ ወንድነት ተምሳሌት ነው:: ነገር ግን እርሱም ቢሆን ‹እምቢ› ተብሎ ያውቃል:: ብራድ ፒት ጠይቋት እምቢ ያለችው ተዋናይት ኤሚ ስማርት ትባላለች:: ይህች ተዋናይት ከፊልሞቿ ይልቅ ብራድ ፒትን እምቢ ማለቷ በጣም ታዋቂ አድርጓታል:: ብራድ ፒት በኤሚ እምቢ መባሉን እንደ ውርደት አላየውም:: ይልቁንም ስማርት እምቢ መባሉን እንደ ውርደት አላየውም:: ይልቁንም የፍቅርና የመገናኘት (የዴቲንግ) ታሪክ ሲነሳበት ራሱ እንደ አንድ የፍቅር አጋጣሚ ያወራዋል::

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## 6. 10% ወንዶችና 90% ሴቶች ያሉበት ዓለም ውስጥ መግባት ትፈልጋለህ?

- ‹እምቢ እባላለሁ› በሚል ፍርሃትና በዓይናፋርነት የተነሳ ዘጠና በመቶ (90%) የዓለም ወንዶች ደስ የሚሏቸውን... የሚወዷቸውን ሴቶች ቀርበው ከማናገር ይልቅ እጃቸውን አጣምረው፣ አፋቸውን ዘግተው ዕድላቸውን መጠበቅ ይመርጣሉ፡፡ አለመታደል ሆኖ ዘጠና በመቶ (90%) የዓለም ሴቶች ደግሞ ወንዶች ቀርበው እንዲያናግሯቸው ቁጭ ብለው ጥፍራቸውን ቀለም እየቀቡ ይጠብቃሉ፡፡

እንግዲህ አስበው የዓለማችን ዘጠና በመቶ (90%) ሴቶች ቁጭ ብለው ወንዶች እስኪያናግሯቸው ሲጠብቁ... ዘጠና በመቶ (90%) የዓለማችን ወንዶች ደግሞ በፍርሃትና በዓይናፋርነት ተሸብበው ከደፋሮቹ አስር በመቶ (10%) ሴቶች አንዷ እንድትደርስላቸው ይቁለጨለጫሉ፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ሴቶችን የማናገር ድፍረት ያላቸው አስር በመቶ (10%) የዓለማችን ወንዶች የሴቶቹን ዓለም እንደፈለጉ ይፈነጩበታል፡፡

ስለዚህ ምርጫው ያንተ ነው... ከዓለማችን ዘጠና በመቶ (90%) ወንዶች ጋር ተቀላቅለህ ከደፋሮቹ አስር በመቶ (10%) ሴቶች አንዷ እንድትደርስህ በተመናመነች የተስፋ ገመድ ላይ ተንጠልጥለህ መጠባበቅ ወይም ሴቶችን የማናገር ድፍረት ያላቸው አስር በመቶ (10%) የዓለማችን ወንዶች ጋር ተቀላቅለህ ወንዶች እንዲያናግሯቸው ከሚጠባበቁት የዓለማችን ዘጠና በመቶ (90%) ሴቶች መሃል የምትወዳትን... የምትሆንህን መርጠህ የግልህ ማድረግ?

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ምርጫህ አስር በመቶ (10%) በሚሆኑት የዓለማችን ደፋር ወንዶች ውስጥ መግባት እንደሆነ አልጠራጠርም። ነገር ግን መገመት እንደምትችለው እዚያ ውስጥ መግባት በጣም ቀላል ቢሆን ኖሮ ሁሉም ወንድ አንድ ላይ ይሆን ነበር። አስር በመቶ (10%) ደፋር ወንዶች በሴት ፍቅር ዓለማቸውን ወደሚቀጩበት የሴት ዓለም ለመግባት የሴቶችን ባህርይና ተፈጥሮ በሚገባ ማወቅና ከእነርሱ ጋር ያለህን ግንኙነት ማሻሻል ያስፈልጋል። የማትፈልጋቸውን (የማትወዳቸውን) ሴቶች በማነጋገር ጭምር ለሴቶች ያለህን አቀራረብና የማነጋገር ብቃት አሻሽል።

## 7. እንቁላል ሳይሰበር እንቁላል ፍርፍር መስራት አይቻልም

- እንቁላል ፍርፍርና እንቁላል ስልስን ጨምሮ የተለያዩ ከእንቁላል የሚሰሩ የቁርስ ዓይነቶች የአብዛኛው የዓለማችን ህዝብ የቁርስ ምርጫዎች ናቸው። የሚጣፍጥ እንቁላል ፍርፍር ወይም እንቁላል ስልስ ለመስራት ግን የሚያምሩ... ቆንጆ ቆንጆ ጫጩቶች ሊሆኑ የሚችሉ እንቁላሎችን መስበር ይጠይቃል።

- ቆንጆ ፍቅረኛ ለማግኘትም ልብህ የሚሰበርባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ‹እምቢ ብትለኝ ስሜቴ ይጎዳል... ልቤ ይሰበራል› ሳትል የጨዋታ ሜዳው ውስጥ ግባ። ዕድለኛ ከሆንክ ልብህ ሳይሰበር ፍቅረኛህን ልታገኛት ትችላለህ። ዕድለኛ ካልሆንክና ልብህ የመሰበር ሁኔታ ካጋጠመው እንደ አዲስ ጠግነህ የልብ ጓደኛህን ፍለጋ ትቀጥላለህ።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## ጠላት ቁጥር 2፡ ዓይናፋርነት

በፍቅር ግንኙነቱ ዓለም ወንዶች የሚፈልጓቸውን የሚወዷቸውን ሴቶች እንዳያገኙ፣ አግባብተው እንዳያገቡ እንቅፋት ከሚሆኑባቸው ነገሮች አንዱ ዓይናፋርነት ነው፡፡ ዓይናፋር ወንዶች በፍቅር የተንዘረከከላቸውን ሴቶች ቀርበው የመተዋወቅ ችግር ስለሚገጥማቸው ብዙ ጊዜ ዕጣ ፈንታቸው በቀላል ጥረት የሚገኙ ሴቶችን አግብቶ ፍቅር አልባ ህይወት መኖርን ይሆናል፡፡ ዕጣ ፈንታህ ተመሳሳይ እንዳይሆን የሚገላግሉህ ወሳኝ ነጥቦች...

### ፩. በሌሎች ስም ተለማመድ

- ለዓይናፋርነት ትልቁ ምክንያት የሚሆነው ‹እምቢ ትለኛለች› የሚል ፍርሃት ነው፡፡ ይህንን ፍርሃት ለማስወገድ ይረዳህ ዘንድ ‹ጓደኛዬ ይወድሻል› በሚል የተለያዩ ሴቶችን እየቀረብክ በማነጋገር ተለማመድ፡፡ ‹ለጓደኛዬ› የሚለው ምክንያት ያ ውርደት መስሎ የሚያስፈራህን የሴቶች እምቢታ ስለሚያስወግድልህ ዘና ብለህ ከተለያዩ ሴቶች ጋር የመቀራረብና የመነጋገር ልምድ እንድታዳብር ያደርግሃል፡፡ ስለዚህ አጋጣሚውን ባገኘህ ቁጥር ሴቶችን እየቀረብክ ‹ጓደኛዬ በጣም ይወድሻልና ስልክ ቁጥርሽን ተቀብዬ በመስጠት ሰርፕራይዝ ላደርገው እፈልጋለሁ› በሚል ዓይነት ዘዴ ሴቶችን በድፍረት ቀርቦ የማነጋገር ጥበብ ተለማመድ፡፡ ‹እምቢ› ቢሉም ላንተ ሳይሆን ለጓደኛህ ስለሆነ ምንም የሚያስፈራ... የሚያሸማቅቅ ነገር አይኖረውም፡፡ በዚህ መንገድ ሴቶች እንደምታስበው የሚያስፈሩ እንዳልሆኑ ትገነዘባለህ፡፡

### ፪. እንቁላል ቀስ በቀስ በእግሩ ይሄዳል

- ዓይናፋርነትህን በአንዴ አራግፈህ ለመጣል ሊያስቸግርህ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ይችላል፡፡ ደረጃ በደረጃ... ቀስ በቀስ ከዘመትክበት ማን ሳይታወቅህ ዓይናፋርነትን አውልቀህ ትጥለዋለህ፡፡ በፈገግታ ጀምር፡፡ ለሴቶቹ አሪፍ ፈገግታ በማሳየት ለመቀራረብ ፍላጎት ያለህ መሆንህን አሳውቅ፡፡ በመቀጠል ታዲያስ የምትል አጭር ግን ወሳኝ የመግባቢያ ድልድይ የሆነች ቃልን የመጠቀም ልምድ አዳብር፡፡ ፈገግታና ታዲያስ ቀለል ላሉ ጠረዎች የመክፈቻ ሥራ ያከናውናሉ፡፡

ከቆንጆ ሴቶች ጋር በፈገግታና በታዲያስ ታግዘህ ጠሬ ለመጀመር የሚያስፈራህ... የሚከብድህ ከሆነ ብዙም ከማያስፈሩህ በጣም ቆንጆ ካልሆኑ ሴቶች ጋር ጀምረው፡፡ ቀስ በቀስ የውበት ቁንጮ ከሆኑ ሴቶች ጋር መግባባት ወደምትችልበት ደረጃ ትደርሳለህ፡፡

## ፱. ሴቶች ሰዎች ናቸው

- ፍርሃቱም ሃፍረቱም የሚመነጨው ሴቶችን ለመቅረብ ስታስብ ለራስህ ከምትነግራቸው የተሳሳቱ ግምቶች ነው፡፡ አምቢ ትለኛለች... በቃሪያ ጥፊ ታጮለኛለች...ሰው ፊት ስድባ ታዋርደኛለች፣ የሚሉ ዓይነት መልዕክቶች፡፡ ሲጀመር ሴቶች ጋር ስትቀርብ እንደ ሰው እንጂ እንደ ወሲብ ዒላማ አታስባቸው፡፡ እንደዚያ ስታስብ ትረበሻለህና፡፡ ሴቶች ከዚያ ባሻገር ልክ እንዳንተ ቤተሰብ፣ ህይወት፣ ዝንባሌ... አላቸው፡፡ ያ ማለት ደግሞ መረበሽን በማይፈጥሩ (ነርቨስ በማያደርጉ) በብዙ ርዕሶ ጉዳዮች ዙሪያ ልታወራቸው ትችላለህ ማለት ነው፡፡ በመቀጠል ሴቶች አንተ ላይ ፍላጎት ባይኖራቸው እንኳን ተግባብህ ስለቀረብካቸው ብቻ ደስተኞች ናቸው፡፡ ስለሆነም አቀራረብህ ጨዋነት የተሞላበት እስከሆነ ድረስ እንደምታስበው የሚያሸማቅቅ ነገር አይኖርም፡፡

## ፲. አትንበፍበፍ

- ሴቶችን ስትቀርብ የሆነ ነገርን ለማሳካት (ስልክ ቁጥር ለመቀበል)

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ከሆነ ትኩረትህ ሁሉ እዚያ ላይ ስለሚሆን ጨዋታህ ለዛ ሲያጣ ይችላል። ስለዚህ ለመጨረሻው ውጤት ሳትጨነቅ ዝም ብለህ ያለውን ሁኔታ ተከትለህ... ዘና ብለህ ተጫወት። ራስህን ሆነህ በነፃነት መጫወትህ በራሱ የመማረክ ኃይል አለው። አንተ ገና ለገና ስልክ ቁጥር ለማግኘት ብቻ የምትንሰፈሰፍ ከሆነ ትረበሽና ሴቶቹን ልታስበረግጋቸው ትችላለህ። ዘና ብለህ ስትጫወት ግን ‹ብል ስልክ እንቀያየርና እንደዋወል› ልትባልም ትችላለህ።

## ፩. ለሰዎች አስተያየትና ትችት ቦታ አትስጥ

- ሰዎች እንዲህ ቢሉኝስ... ሴቶቹ ሙድ ቢይዙብኝስ... ለሚሉ አስተሳሰቦች ቦታ አትስጥ። ሰዎች የራሳቸውን ህይወት በመኖር ቢዚ ናቸው። ስላንተ ጥቃቅን እንቅስቃሴዎችና ድርጊቶች እየተከታተለ አስተያየትና ትችት ለመስጠት ጊዜ ያለው የለም።ቢኖር እንኳን ልትኮራበት እንጂ ልታፍርበት አይገባም። ምክንያቱም ሰዎች ብዙ ነገሮችን ወደ ጎን አድርገው ስላንተ የሚነጋገሩ ከሆነ አንተ ትኩረት የምትስብና በሰዎች ህይወት ውስጥ ቦታ የምትሻማ... የሆነ የሚያስቀና ነገር ያለህ ሰው ነህ ማለት ነው።

## ፮. አድማጭ ይፈለጋል

- ይህቺ ነጥብ ለዓይናፋር ወንዶች መልካም ዜና ናት። ብዙ ጊዜ ዓይናፋር ወንዶች የሚፈሩት ሴቶችን ቀርቦ ለማናገር ነው። ብዙ ሴቶች ደግሞ የሚመኙት ከለፍላፊ ይልቅ የሚያዳምጥ ወንድን ነው። ስለዚህ ጥሩ አድማጭ በመሆን ብቻ የሴቶችን ቀልብ መማረክ ይቻላል። ጥሩ ጥያቄ ጠይቀህ ተመቻችተህ አዳምጥ። ጥያቄህ ከተመለሰ በኋላ ደግሞ ሌላ ጥያቄ አስከትል። በዚህ መንገድ ብቻ በሴቶች ዘንድ ተፈላጊ መሆን ትችላለህ።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## ፮. ሳታማርጥ ቅረብ... አነጋግር

- ሁሉም ነገር ልምድ ያስፈልገዋል። በቀላሉ ሴቶች ጋር ቀርበው ጨዋታ መጀመር የሚችሉ ጓደኞችህን ለደቂቃ ያህል በህሊናህ መለስ ብለህ ገምግማቸው። እነዚያ ጓደኞችህ ከሴቶች ጋር ብቻ ሳይሆን ካገኙት ሰው ጋር ቀርበው ጨዋታ የመጀመር ችሎታና ብቃት አላቸው። ከህፃን፣ ከትልቅ... ከወንድ፣ ከሴት... ከተማሪ፣ ከሰራተኛ... ከአስተናጋጅ፣ ከአስተማሪ... ክፍል ውስጥ፣ ሊፍት ውስጥ... ታክሲ ውስጥ፣ አውቶብስ ውስጥ... መንገድ ላይ፣ አውሮፕላን ላይ... በማንኛውም ቦታ ከማንኛውም ሰው ጋር ጨዋታ የመጀመር ችሎታ አዳብር። በየትኛውም ሥፍራ ከማንኛውም ሰው ጋር የመጫወት ችሎታ ካለህ ከሴቶች ጋር የማውራት ድፍረትም ይኖርሃል።

## ፯. አትፍራ

- ቦክሰኞች ለመቧቀስ ወደ ሪንግ ሲገቡ የማሸነፍና የመሸነፍ ዕድል እንዳለ በማመን ነው። ህይወት ላይ 100 ፐርሰንት የሚባል ነገር የለም። አንተም አንዲት ሴትን ቀርበህ ስታናግር ልጅቷ ፍላጎት ሊኖራትም ላይኖራትም ይችላል የሚል ግምት ይዘህ መሆን አለበት። እዚህ ላይ ግን ወደ ሪንግ የሚገቡ ቦክሰኞችንና ወደ ጦርነት አውድማ የሚገቡ ወታደሮችን አስባቸው። ከአካል መጉደል እስከ ህይወት ማጣት ሊያጋጥማቸው ይችላል። አንተ ግን ምንም ዓይነት አካላዊ ጉዳት አያጋጥምህም። ፍላጎት ካላት ታናግርሃለች (ስልክ ቁጥር ትሰጥሃለች) ፍላጎት ከሌላት ደግሞ ዘግታህ ትሄዳለች። በቃ። ስለዚህ አትፍራ። ሴትን ልጅ ለማናገር ስታስብ ሊፈጠሩ የሚችሉ ጥቃቅን ነገሮችን በአጉሊ መነፅር እያየህ ራስህን አታስጨንቅ። ትኩረትህን በምታናግራት ሴት ውበትና ለዛ ላይ አድርግ።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

## ፱. ሴቶች በሚያዘወትሩበት ስፍራ ተከሰት

- ዓይናፋርነት የሚመጣበት አንዱ መንገድ ከሰዎች ጋር በሚያገናኙ የተለያዩ ማህበራዊ ህይወቶች ላይ አለመሳተፍ ነው። ስለዚህ ሴቶች በሚያዘወትሩባቸው እንደ ጂም፣ ትምህርት ቤት፣ የበጎ ፈቃድ ክበቦችና ማህበራት በመሳተፍ ከሴቶች ጋር ተቀራርበ የመነጋገር ልምድህን አዳብር። በእንደዚህ ዓይነት ቦታዎች ከተለያዩ ሴቶች ጋር የመቀራረብና የማውራት ችሎታህን ካሻሻልክ ከብዙ ሴቶች መሃል በተለየ ሁኔታ የምትማርክህን ሴት ማናገር በፍፁም አይከብድህም።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

‘ ፍቅር ገደብ የሚባል ነገር አያውቅም… አይቀበልም፡፡
መሰናክልና አጥር ዘሎ፤ ግንብ ደርምሶ
መድረስ ያለበት ቦታ ላይ ይደርሳል ’

ማያ አንጀሎ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



# የፍቅር ኬሚስትሪ

"ፍቅር ካለህ ሁሉም ነገር አለህ። ፍቅር ከሌለህ ግን የፈለገው ነገር ቢኖርህም ምንም የለህም"

ጀምስ ኤም ቤሪ

የፍቅር ኬሚስትሪ በሴትና በወንድ መሃል የሚፈጠር ልዩ የመሳሳብ ስሜት ነው። ብዙ ሰዎች የፍቅር ኬሚስትሪን... ‹ኮከባችን ገጥሟል›፣ ‹ልክ እንደተገናኘን ክሊክ አደረግን›፣ ‹ልክ ሳያት ተሰምቶኝ የማያውቅ ስሜት ተሰማኝ›፣ ‹ልክ ሳየው ልቤ ዘለለ›፣ ‹ድምፁን ሳልሰማ መዋል አልችልም›፣ ‹አይኗን ሳላየው ማደር አልችልም›... በሚሉና በመሳሰሉ ጥልቅ ስሜቶችና ከፍተኛ ፍላጎቶች ሲገልፁት የምንሰማው በሁለት ሰዎች መካከል የሚጫር የፍቅር ግንኙነት ነው።

## የፍቅር ኬሚስትሪ ሲተነተን

የፍቅር ኬሚስትሪ በሁለት ሰዎች መካከል ከፍተኛ በሆነ የስሜት፣ የአካልና የአስተሳሰብ መሳሳብ የሚፈጥረው የተጋጋለ የፍቅር ስሜት ነው። የፍቅር ኬሚስትሪ በሴትና በወንድ መካከል

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

የሚፈጠር አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አስተሳሰባዊና መንፈሳዊ ጥምረት ነው። ‹የመዋደድ፣ አብሮ የመሆን ጥልቅ ፍላጎትና ለወሲብ መፈላለግ› በሚሉ ሦስት ጥምር ስሜቶችም ይገለፃል።

በሌላ መልኩ ደግሞ በእንደነ ምግብና መጠጥ የመሳሰሉ ነገሮች ሱስ እንድንያዝ የሚያደርጉን ኒውሮኬሚካልስ የሚባሉት ጭንቅላታችን ውስጥ የሚገኙ ኬሚካሎች ከሚማርከን ሰው ጋር ለመገናኘትና ተገናኝተንም አብሮ የመሆን፣ የማውራት፣ የመሳቅና ወሲብ የማድረግ ሱስ እንዲይዘን ያደርጋሉ። ስለሆነም በከፍተኛ የስሜት፣ የአካል፣ የአስተሳሰብና የመንፈስ መሳሳብ የተሳሰሩ ወይም ደግሞ በአጭሩ ኮከባቸው የገጠመና ‹የፍቅር ኬሚስትሪ› ውስጥ ናቸው የምንላቸው ጥንዶች ሁሌም ለመገናኘትና ተገናኝተውም በሚችሉት መንገድ ሁሉ ፍቅራቸውን ለመግለፅ አስገራሚ ጉልበት አላቸው። ሉተመልካችና ለሰሚ በሚያስገርም ሁኔታ ሁሌም ለመገናኘት ጊዜና ቦታ ያመቻቻሉ።

ከጭንቅላታችን የሚመነጩት ዶፓሚን እና ኦክሲቶሲን የሚባሉት ኬሚካሎች ስራቸው በተለያዩ ስሜቶችና እንቅስቃሴዎች ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ማድረግ ነው። በመሆኑም እነዚህ ኬሚካሎች ከምንም ነገር የበለጠ ከፍተኛ የፍቅር ኬሚስትሪ ከፈጠረብን ሰው ጋር እየተገናኘን እንድንደሰት… ጥሩ ጊዜ እንድናሳልፍ ይገፋፉናል፡ ፡ በመሆኑም ‹ዓይኗን ሳላይ፣ ድምጿን ሳልሰማ አልውልም… አላድርም› በሚል የወደድነውን ሰው ለማግኘት እንሰባበራለን። ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን።

የፍቅር ኬሚስትሪ ዋና መለያው ሰዎች ያለ ምንም መጠናናትና ያለ ማሰላሰል እንዲሁ በጭፍን ኘየው ብለው የሚዘፈቁበት የፍቅር ዓይነት ነው። የዚህ ዓይነት ፍቅር የሚይዛቸው ሰዎች ድንገት ከፍተኛ የመዋደድ ስሜትና ወሲብ የማድረግ ጥልቅ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ፍላጎት ስለሚያጣድፋቸው እርስ በርስ ለመተዋወቅና ለመጠናናት ጊዜ ላይወስዱ... ላይታገሱ ይችላሉ።

## በፍቅር ኬሚስትሪ የመያዝ ምልክቶች

አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ኮከቡ ሲገጣጠም... የፍቅር ኬሚስትሪ ውስጥ ሲገባ የፍቅር ኬሚስትሪ ውስጥ መሆኑን የሚገልፁባቸው አካላዊ፣ አስተሳሰባዊና ስሜታዊ ምልክቶች አሉ።

ሀ. አንድ ሰው ወሲብ ለማድረግ ሲፈልግ ከሚሰማው ስሜት ባልተናነሰ ሁኔታ ያንን ሰው የማየት፣ የመስማት፣ የማሽተት፣ የመዳሰስ... ፍላጎቱ ጣሪያ ላይ ይወጣል።

ለ. የወደደውን ሰው የሚያገኝበት ሰዓት ሲደርስ ትንፋሽ ቁርጥ... ቁርጥ የማለትና ጉልበት የመክዳት ስሜት ያጋጥመዋል።

ሐ. የተዋደዱት ሰዎች ሲገናኙ ቆዳቸው የማተኮስ፣ ፊታቸው የመቀያየርና የመቅላት ሁኔታ ይኖረዋል።

መ. የወደዱትን ሰው በማግኘት ሱስ ይያዛሉ።

ሠ. አንዱ የጀመረውን አረፍተ ነገር ሌላው የመጨረስ እንዲሁም አንድ ላይ አንድን ወሬ አሊያም ሃሳብ እኩል የመጀመር አጋጣሚዎች ይከሰታሉ።

ረ. ያለ በቂ ምክንያት መሳቅና መሳሳቅ እንዲሁም የወደዱትን ሰው እያሰቡ ፈገግ ማለት የፍቅር ኬሚስትሪ ውስጥ የገቡ ሰዎች ሊያሳዩዋቸው የሚችሉ ምልክቶች ናቸው።

## የፍቅር ኬሚስትሪ የሚፈጠረው እንዴት ነው?

በፍቅር ግንኙነት ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ የሚታወቁት ፕሮፌሰር ኬሊ ካምቤል በዚህ ጉዳይ ላይ ያደረጉት ጥናት እንደሚያሳየው ብዙ ጊዜ የፍቅር ኬሚስትሪ ሊከሰት

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

የሚችለው ትሁት፣ ግልፅና ተግባቢ በሆኑ ሰዎች መካከል ነው። ትሁት፣ ግልፅና ተግባቢ የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን የመግለፅና ሌሎችን የመረዳት ችሎታና ግልፅነት ስላላቸው ቶሎ በመግባባት ወደ ፍቅር ኬሚስትሪ ወደሚያደርሰው ፈጣን ባቡር የመሳፈር ዕድል አላቸው። እነዚህ ሰዎች ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ በፍቅር ኬሚስትሪ ባቡር ላይ ተሳፍረው ጣፋጭ ዕብደት በሆነው የፍቅር ዓለም ውስጥ የመንሳፈፍ ዕድል የሚያገኙት በራሳቸው ምቾት የሚሰማቸው፣ ዘና ያሉ፣ በራስ የመተማመን ስሜት ያላቸውና ግልፅ በመሆናቸው ሲሆን ይህም ተመሳሳይ ባህሪና ብቃት ያላቸውን ሰዎች የመማረክ አጋጣሚ ስለሚፈጥርላቸው ነው።

ድብቅና ተግባቢ ያልሆኑ ሰዎች ትክክለኛ ስብዕናቸውና ብቃቶቻቸው በሌሎች ሰዎች እንዲታዩላቸው ስለማያደርጉ በስሜት፣ በአካል፣ በአስተሳሰብና በመንፈስ አጣድፈው የመማረክ ዕድል ላይገጥማቸው እንደሚችል የፕሮፌሰር ኬሲ ካምቤል ጥናት አመልክቷል።

## የፍቅር ኬሚስትሪ አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች

ኬሚስትሪው ጥንዶችን በፍቅር አሳብዶ ወደ ሌላ የፍቅር ዓለም የሚያስወነጭፍ ሲሆን ዘላቂነቱ አስተማማኝ አይሆንም። ምክንያቱም ጥንዶች እንዳቸው በአንዳቸው ፍቅር ስለሚታወሩ፣ ፍቅራቸውን ዘላቂ ሊያደርጉ የሚችሉ ነገሮችን ረጋ ብለው ማየት አይችሉም። ‹ፍቅር እውር ነው› የሚለው አባባል የመጣውም ከዚህ ከኬሚስትሪው ነው። በተለይ ደግሞ የፍቅር ኬሚስትሪው የተፈጠረው በአካላዊና ስሜታዊ መሳሳብ (ወሲባዊ ፍላጎት) ብቻ ከሆነ ፍቅሩ የተወሰነ ጊዜ አብዶ ሊከስም ይችላል።

ኬሚስትሪው በአካልና በስሜት መሳሳብ ብቻ ሳይገደብ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

በአስተሳሰብና በመንፈስ ጭምር የተፈጠረ ከሆነ እውነተኛና ዘላቂ የፍቅር ኬሚስትሪ ሆኖ የመቀጠል ዕድል ይኖረዋል፡፡

ስለዚህ የፍቅር ኬሚስትሪው በምንም ይሁን በምን ሲፈጠር በዕብደት ጋልቦ የፍቅር ግንኙነቱን ዕድሜ በአጭር ከመቅጨት ይልቅ ረጋ ብሎ ለዘላቂነቱ አስፈላጊ የሆኑ ቅመሞችን መጨመር ወሳኝ ነው፡፡

በፍቅር ትኩሳት እየተገናኙ በወሲብ መቀዝቀዝ ብቻ ሳይሆን በመነጋገርና አብሮ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ የበለጠ በአስተሳሰብም መጣመር ለፍቅር ኬሚስትሪው ቀጣይነት ወሳኝ ሚና አለው፡፡

## የፍቅር ኬሚስትሪ፡ ጣፋጭ ዕብደት

በመፅሃፉ መግቢያ ላይ ቃል በገባሁት መሰረት ለዚህ ‹ፍቅር ኬሚስትሪ› ርዕሳችን ምሳሌ የሚሆን አንድ የራሴ ታሪክ… በስብሃት ገ/ሔር አባባል ‹እነሆ በረከት› ብያለሁ…

ቴዲ… ቴዎድሮስ ተሾመ ‹አባይ ወይስ ቬጋስ› ፊልሙን እኔ ደግሞ ‹ሙሴ› ፊልሜን ኤዲት ለማድረግ ወደ ሆሊዉድ ሎስ አንጀለስ በሄድንበት ጊዜ ነበር በፍቅር ኬሚስትሪ የተመታሁት፡፡ ሆሊዉድን መጎብኘት ሆሊዉድ ጋዜጣ ላይ መስራት ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ የተፈጠረና ለበርካታ ዓመታት አብሮኝ የቆየ ምኞቴ ነበር፡፡ ከቴዲ ተሾመ ጋር ፊልም ኤዲት ለማድረግ ወደ ቦታው መሄዱ ደግሞ ምኞቴን ከእቅድ በላይ ማሳካት ነበር፡፡ ቴዲ በጣም አዝናኝና አሪፍ ሰው ነው፡፡ ከእሱ ጋር ከሆሊዉድ ሎስ አንጀለስ እስከ ላስ ቬጋስ መዝናናት እጅግ በጣም ደስ የሚል ስለነበር በጊዜው ሌላ ደስታ የማግኘት ምንም ዓይነት ምኞት አልነበረኝም፡፡ አንድ ምሽት ግን ተጨማሪ ደስታ የሚሰጥ አጋጣሚ ተፈጠረ፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ቴዲ አግብቼ የትዳርን ህይወት እንዳጣጥም ስለሚፈልግ

ቴዲ አግብቼ የትዳርን ህይወት እንዳጣጥም ስለሚፈልግ አልፎ አልፎ በጨዋታችን መሃል ‹አንተ ግን መቼ ነው የምታገባው?› ሲለኝ ‹ሚስቴ ልትሆን በምትችል ሴት ፍቅር ስመታ› እለው ነበር፡፡

አንድ ቀን በአጋጣሚ አንዲት ቴዲን የምታውቀው ቆንጆ ኢትዮጵያዊት አገኘንና ጠበቅ አድርጎ አስተዋውቆን ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡ እኔና ልጅቷ መገናኘት ጀመርን፡፡ ወዲያው በመሃከላችን የፍቅር ኬሚስትሪ ተፈጠረና አንድ ወር ሙሉ በፍቅር አበድን፡ ፡ በፍቅር ኬሚስትሪ መመታቴ አስደሳቹ የሆሊዉድ ሎስ አንጀለስ ቆይታዬን የበለጠ ጣፋጭ አደረገው፡፡ በጣም ከማበዳችን የተነሳ በአጭር ጊዜ ውስጥ እኔ ‹አንቺ ወደ ኢትዮጵያ ጠቅልለሽ መምጣት አለብሽ› ስል እሷ ደግሞ ‹ኖ አንተ ነህ ወደዚህ መምጣት ያለብህ› በሚል ስለ ትዳርና ስለ ልጆች ቀበጣጠርን፡፡

ወደ አገሬ የመመለሻ ጊዜዬ ሲደርስ ቀስ በቀስ ደስታው ይርቀኝና ያሳስበኝ ጀመር፡፡ መመለሻ ቀኔ ደርሶ አውሮፕላን ስሳፈር እኔ ያለሷ፣ እሷም ያለኔ መኖር የምንችል አንመስልም ነበር፡፡ ፊልሜን ይዤ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለስኩ ለጥቂት ሳምንታት ከተደዋወልንና ኢንተርኔት ላይ ቻት ካደረግን በኋላ ያ የሚያሳብድ የፍቅር ስሜት እየከሰመ… እየከሰመ ሄዶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጠፋ፡፡ ጭራሽ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ‹ሙሴ› ፊልምን ለማሳየት ወደ ሎስ አንጀለስ ተመልሼ ሄጄ ስንገናኝ ያንን የዕብደት ጊዜ ያሳለፍነው ፍፁም እኛ አንመስልም ነበር፡፡

የፍቅር ኬሚስትሪ አንዱ ገፅታ እንደዚህ ነው፡፡ የፍቅር ኬሚስትሪው ሲፈጠር ጥልቀት ባለው ትውውቅ ታግዞ በጥንቃቄ ካልተያዘ በሚገርም ሁኔታ ሲዳፈን ይችላል፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



# መገናኘት... Dating

> ‘ እውነተኛ ፍቅር የሚገኘው ፍፁም የሆነን ሰው በማፈላለግ ሳይሆን ፍፁም ያልሆነውን ሰው ፍፁም አድርጎ በመመልከት ነው ’
>
> ጄሰን ጆርዳን

አንድ ወንድ አንዲት ሴት ላይ ፍላጎት አድሮበት የበለጠ ሊቀርባት... ሊያውቃት ፈልጎ በቀጠሮ ሲያገኛት፤ በተመሳሳይ ሁኔታ አንዲት ሴት አንድ ወንድ ላይ ፍላጎት አድሮባት የበለጠ ለመቅረብ... ለማወቅ በቀጠሮ ስታገኘው እንዲሁም የሚፈላለጉ ጥንዶች በደንብ ተቀራርበው እርስ በርሳቸው ለመተዋወቅ ተቀጣጥረው ሲገናኙ “Dating” ይሉታል።

ሰዎቹ ከመጀመሪያ ቀጠሮ አልፈው ሁለተኛ፣ ሦስተኛ፣ አራተኛ ቀጠሮ እያሉ መገናኘታቸውን ሲቀጥሉ ደግሞ “Date” እያደረጉ ነው ይባላል።

ወደ ዝርዝር ትርጉሙና ይዘቱ ከመግባታችን በፊት “Dating” እና “Date” የሚሉትን ቃላት በአማርኛ እንተካቸው። ሁለት የሚፈላለጉ ሰዎች ለበለጠ ትውውቅና መግባባት

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ተቀጣጥረው የሚገናኙትን ነገር ማለትም "Dating" የሚሉትን ‹መገናኘት› እንበለው:: መገናኘታቸው ሲቀጥሉና "Date" እያደረጉ ነው› የሚለውን ደግሞ ‹ይገናኛሉ... እየተገናኙ ነው› በሚለው እንውሰደው:: ‹መገናኘት... ይገናኛሉ... ታገኘዋለች... ያገኛታል...› የሚሉት ቃላት ሃሳቡን በደንብ ይገልፁታል ብዬ አምናለሁ::

## መገናኘት... Dating በኢትዮጵያ

የ‹መገናኘት› (Dating)... ታሪክ ብዙ ክፍለ ዘመናትን ወደኋላ ሊወስደን የሚችል ጥንታዊ የሰው ልጅ ባህል ነው:: የአገራችንን የ‹መገናኘት› ታሪክ ስንመለከትም ምንም እንኳን እንደ አሁኑ በሁለት የሚፈላለጉ ሰዎች መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ላይሆን ቢችልም ቅድመ ዓያቶቻችን በቤተሰብና በወዳጅ አማካይነት ቀጠሮ ተይዞላቸው እየተገናኙ ተግባብተው፤ ተጋብተው፣ ተዋልደው... እዚህ ደርሰናል::

የአሁኑ ዘመናዊ የ‹መገናኘት› ባህላችን ከድሮ በተሻለ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ግን ነፃ አልወጣም:: አሁንም ድረስ በዋና መዲናችን አዲስ አበባ ሳይቀር ስለ ዘመናዊ ‹መገናኘት› ያለው እውቀትና አስተሳሰብ በጣም ዝቅተኛ ነው::

‹መገናኘት› (Dating)... መተዋወቅ፣ መቀራረብ የሚፈልጉ ሴትና ወንድ ተቀጣጥረው በማውራት... ከተፈላለጉ፣ ከተስማሙ፣ ከተሳሳቡ... በተደጋጋሚ በመገናኘት ወደ ፍቅረኝነት ሊያሳድጉት የሚችሉት ሂደት መሆኑና ካልተግባቡ ደግሞ በዛው በመጀመሪያው ቀጠሮ ሊቋጩት የሚችሉት ቀላል ነገር መሆኑ በቂ ግንዛቤ አለ ብሎ ማለት አይቻልም::

ይልቁንም አንድ ወንድ የሚፈልጋትን ሴት እስኪያገኝ ድረስ ከተለያዩ ሴቶች ጋር መተዋወቁና መገናኘቱ እንደ ነውር...

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

እንደ ብልግና ነው የሚታየው፡፡

በቤተሰብ፣ በዘመድና በጓደኛ የሚመቻቸው ባህላዊው የ‹መገናኘት› ሂደት ላይ ችግር የለብኝም፡፡ በሦስተኛ ወገን የተመቻቸው የ‹መገናኘት› ሂደት የመጨረሻ ውሳኔውን ለሚገናኙት ሴትና ወንድ መስጠት አለበት እንጂ አገናኙ ወገን (ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ወዳጅ) ውሳኔው ውስጥ መግባት የለበትም፡፡ ስለዚህ የመጨረሻው ውሳኔ ለሚገናኙት ከተሰጠ ባህላዊው የ‹መገናኘት› ሂደት መቀጠል አለበት፡፡ ምክንያቱም ቤተሰብ፣ ዘመድና ጓደኛ በዚህ በባህላዊ መንገድ አመቻችቶ ሴትና ወንድን የሚያገናኘው ከሁለቱም ባህሪና ሁኔታ በመነሳት ‹ሊግባቡና ሊዋደዱ ይችላሉ› ከሚል ቀና ሃሳብ ስለሚሆንና በዚህ መልኩም ብዙ ሰዎች ተዋደው ተጋብተው መልካም የፍቅር ህይወት ሲኖሩ ማየት ስለሚቻል ነው፡፡

እንዳውም ባህላዊው የ‹መገናኘት› ሂደት ከዘመናዊው የ‹መገናኘት› ሂደት ተመራጭ የሚያደርገው አንድ እውነታም አለ…

መንገድ ላይ አሊያም እንደ ፌስቡክ በመሳሰሉ የኢንተርኔት ሚዲያዎች ላይ ተዋውቀው ወደ መገናኘት ሂደት ውስጥ ከሚገቡ ሴቶች አስር በመቶ(10%) አስገድዶ የመደፈር፣ አስገድዶ የመደፈር ሙከራና የመደብደብ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል በቤተሰብ፣ በዘመድ ወይም በጓደኛ በኩል የሚመጣላቸውን ወንድ የሚያገኙ ሴቶች በአብዛኛው ከዚህ ሁሉ ጥቃት ነፃ ናቸው፡፡ መጥፎ ወንዶች቎ ቢያጋጥሙዋቸው እንኳን እነዛ መጥፎ ወንዶች ያገናኙዋቸውን ሰዎች (ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ጓደኛ) በመፍራት ወይም በማክበር ሴቶቹ ላይ ምንም ዓይነት ጥቃት ላለመፈፀም ይገደዳሉ፡፡

ስለዚህ ባህላዊው የ‹መገናኘት› ሂደት የመጨረሻውን ውሳኔ ለሚገናኙት ጥንዶች እስከ ሰጠ ድረስ ቢቀጥል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ ጤናማ ለሆነ ዘመናዊ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

የ‹መገናኘት› ሂደትም በራችንን መክፈት ይኖርብናል።

## አዲስ ሰው ማግኘት... Blind Dating

የማይተዋወቁና የመተዋወቅ... ጓደኝነት የመመስረት ፍላጎት ያላቸው ሁለት ሰዎች በቀጠሮ ሲገናኙ Blind Dating ይባላል። ‹አዲስ ሰው ማግኘት› ልንለው እንችላለን።

በዚህ መልኩ... በዘመድ፣ በወዳጅ፣ በጓደኛ ቀጠሮ ተይዞላቸው አሊያም ራሳቸው በፌስቡክ ወይም በትዊተር በኩል ተዋዕፈው... ስልክ ቁጥር በመቀባበል ተቀጣጥረው የሚገናኙ ሁለት የማይተዋወቁ ሰዎች አጀንዳቸው ግልፅ ነው። ሁለቱም ጓደኛ (ፍቅረኛ) ይፈልጋሉ።

እናም በመጀመሪያው ቀጠሮአቸው ተገናኝተው እርስ በርስ ይተዋወቃሉ... አንዳቸው ለአንዳቸው የሚመቹ መሆናቸውን ያጠናሉ። በመጀመሪያው ቀጠሮ ሁለቱም ደስ ብሏቸው ከተለያዩ ሁለተኛ... ሦስተኛ ቀጠሮ እያሉ ጥልቀት ወዳለው ጓደኝነት ሊገቡ ይችላሉ።

በመጀመሪያው እንዲሁም የመጀመሪያው ቀጠሮ ሁለተኛ ቀጠሮ ከወለደ... በሁለተኛው ቀጠሮ ተገናኝተው ‹ኬሚስትሪው› ተስፋ ካላሳየ... ከአባቸው ካልገጠመ ግንኙነቱን ሊያቆሙት ይችላሉ። እንዲሁ ከፍቅር ውጭ በሆነ ጓደኝነትም ሊቀጥሉ ይችላሉ።

‹አዲስ ሰው ማግኘት› (Blind Dating) በአገራችን ረዥምም ታሪክ አለው። ከጥንት ጀምሮ የማይተዋወቁ ሰዎች በቤተሰብ፣ በዘመድና በጓደኛ በኩል ቀጠሮ እየተመቻቸላቸው ይተዋወቃሉ። ከእኛ ትውልድ በፊት የነበሩት ትውልዶች በብዛት

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

በዚህ መልኩ እየተገናኙ የተጋቡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

አሁን ባለንበት የቴክስትና የኢንተርኔት ዘመንም ‹አዲስ ሰው ማግኘት› (Blind Dating) ትንሽ መልኩን ቀይር ቀጥሏል፡፡ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች ከጓደኞቻቸው በሚያገኙዋቸው ስልክ ቁጥሮች በመደዋወልና ቴክስት በመደራረግ ከአዳዲስ ሰዎች ጋር ይገናኛሉ… ይተዋወቃሉ፡፡ ከተመቻቹ ይቀጥላሉ፡፡ ካልተመቻቹ ደግሞ ይለያያሉ፡፡

በተለይ ፌስቡክ ደግሞ እጅግ በጣም ብዙ የማይተዋወቁ ሰዎች እያገናኘ… ለፍቅርና ለጋብቻ እያበቃ ያለ የብዙ ሰዎች አዲሱ እትት… አክስት… ጓደኛ ሆኗል፡፡



## በኢንተርኔት መገናኘት… Online Dating

የማይተዋወቁ ግን ደግሞ ፍቅረኛ የሚፈልጉ ሰዎችን እንደ ፍላጎቶቻቸው፣ ዝንባሌዎቻቸውና ምርጫዎቻቸው የሚያገናኙ የኢንተርኔት ላይ መገናኛ ዌብሳይቶች (Online Dating Sites) ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ይገኛል፡፡ የኢንተርኔት ላይ መገናኛ ዌብሳይቶች እንደ እሸን መብዛት የተጠቃሚው ህዝብ ቁጥር በየጊዜው መጨመርን ያሳያል፡፡ የስርቬይ ስፔሻሊስት የሆኑት አሜንዳ ሌንሃርት በኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ላይ ጥናት አድርገው ይፋ ያደረጉት ውጤት እንደሚያሳየው ሰባ ሁለት በመቶ (72%) የኢንተርኔት ተጠቃሚው ህዝብ ኢንተርኔትን የሚጠቀመው

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ከፍቅርና ፍቅረኛን ፍለጋ ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት የኢንተርኔት ላይ መገናኘት (Online Dating) አገልግሎት በዓመት 3.5 ቢልዮን ዶላር የሚያንቀሳቅስ... ራሱን የቻለ ትልቅ ኢንዱስትሪ መሆን ችሏል፡፡

በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ተፈላላጊ ሰዎችን በማገናኘት ለፍቅርና ለጋብቻ በማብቃት ላይ ከሚገኙት የኢንተርኔት መገናኛ ዌብሳይቶች ግንባር ቀደሙን የያዘው ፌስቡክ ሲሆን እንደ www.match.com, www.zoosk.com, www.eharmony.com, www.chemistry.com, www.ourtime.com, www.dating-direct.com... የመሳሰሉ አገናኝ ዌብሳይቶችም የፍቅረኛ ፈላጊዎች መናኸሪያ ናቸው፡፡ www.eharmony.com የተባለው ዌብሳይት ብቻ በቀን 120 ሰዎች ጋብቻቸውን እንዲፈፅሙ ምክንያት ይሆናል፡፡

## ማስጠንቀቂያ

ፌስቡክን ጨምሮ በተለያዩ አገናኝ ዌብሳይቶች ብዙ ሰዎች የነፍስ አጋራቸውን አግኝተው የመፋቀራቸውና የመጋባታቸውን ያህል የሚጭበረበሩ ቀላል አይደሉም፡፡ እያጭበረበሩ ከሚያስከፍሉ ዌብሳይቶችና በውሸት ከሚያጭበረብሩ ሰዎች መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ የኢንተርኔት ላይ መገናኘት (Online Dating) ለመጭበርበርና ለማጭበርበር የተጋለጠ የመገናኛ (Dating) መንገድ ነው፡፡

## በአንድ ጊዜ ከተለያዩ ሰዎች ጋር መገናኘት... Speed Dating

የዚህ ዓይነት መገናኘት (Dating) እስካሁን ድረስ በአገራችን ሲደረግ አላየሁም፣ አልሰማሁም፡፡ ነገር ግን በቅርቡ መጀመሩ የማይቀር ነው፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ስለዚህ ቀድመን ብናውቀው ጥሩ ነው። ‹በአንድ ጊዜ ብዙ ሰው ማግኘት› (Speed Dating) በተለያዩ አገናኝ ድርጅቶችና ዌብሳይቶች የሚዘጋጅና ጓደኛ (ፍቅረኛ) ፈላጊ ላጤዎች በአንድ ጊዜ ከበርካታ ሰዎች ጋር የመገናኘትና የማውራት ዕድል የሚያገኙበት የመገናኘት ሂደት ነው።

በአሜሪካ፣ በካናዳና በእንግሊዝ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ በዋለውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቻይና እና በሌሎች የአውሮጳ አገሮች እየተለመደ በመጣው በዚህ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች የሚያገናኝ... የሚያስተዋውቅ (Speed Dating) ፕሮግራምን ተጠቅመው በርከት ካሉ ሰዎች ጋር በመገናኘት የሚማርካቸውን የሚፈልጉ ሰዎች መጀመሪያ ቅድሚያ ክፍያ በሚቀበሉ ዌብሳይቶች መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል።ከምዝገባው በኂላ አገናኝ ዌብሳይቱ በሚነግራቸው ቀን፣ ቦታና ሰዓት በመገኘት በተመሳሳይ ሁኔታ በቦታው ከሚገኙ ላጤዎች ጋር አንድ በአንድ የማውራት ዕድል ይሰጣቸዋል።

በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰው ጋር የመገናኘት (Speed Dating) ሂደት ካፌ ወይም ሬስቶራንት በመሰለ ምቹ ቦታ ላይ የሚገኙትና ቁጥራቸው ከ20 እስከ 40 ሊሆኑ የሚችሉ ሴቶችና ወንዶች አንዱ ከአንዱ ጋር ከሦስት እስከ ስምንት ደቂቃ እንዲያወሩ ይደረጋል።

(ከሦስት እስከ ስምንት ደቂቃ በጣም አጭር ነው? ብለህ ካሰብክ በጣም ተሳስተሃል። እ.ኤ.አ በ2006 በኤደንብራ ስኮትላንድ የተካሄደ ጥናት... ሴቶች በ30 ሴኮንድ ወንዶች ደግሞ በ22 ሴኮንድ ውስጥ የሚሆናቸውን ሰው መርጠው እንደሚወስኑ አሳይቷል)

የተመደበው ደቂቃ ሲያበቃ በደወል ወይም በፊሽካ ምልክት ሲሰጣቸው ሁሉም ይቀያየራሉ። በዚህ ሁኔታ እያንዳንዳቸው ከእያንዳንዳቸው ጋር ተገናኝተው በተመደበላቸው ደቂቃ (ከ3 እስከ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

8) እንዲያወሩ ይደረጋል። ሁሉም ከእያንዳንዱ ጋር የማውራት ዕድል አግኝተው የማውራቱ ስነ ስርዓት ሲጠናቀቅ እያንዳንዳቸው በሚስጥር የማረከቻቸውን/የማረካቸውን ሰው ለአዘጋጁ ነግረው በአንድ ጊዜ ብዙ ሰው የማግኘቱ (Speed Dating) ፕሮግራም ይጠናቀቃል።

በዚህ ፕሮግራም ላይ ሁሉም ተሳታፊዎች ስም ብቻ ተዋውቀው ከማውራት ውጪ አድራሻ መቀያየር አይፈቀድላቸውም።

**ውጤት**

በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰው መገናኘት (Speed Dating) ፕሮግራም ላይ የተሳተፉ ጓደኛ ፈላጊ ላጤዎች በአዘጋጁ አማካይነት በተመሳሳይ ሁኔታ ጓደኛ ፍለጋ በፕሮግራሙ ከተሳተፉት ሰዎች በሙሉ ተዋውቀውና አውርተው የማረካቸውን ሰው በሚስጥር ጠቁመው ከሄዱ ከጥቂት ቀናት በኋላ ፕሮግራሙን ካዘጋጀው አካል ውጤት ይላክላቸዋል።

ውጤት አሰጣጡም አንድ ግልፅ ህግ አለው... አዘጋጁ አካል ለአንድ ተሳታፊ የወደዳትን ልጅ አድራሻ የሚልክለት በተመሳሳይ ሁኔታ ያቺ የፈለጋት ልጅም ከፈለገችው ብቻ ነው። ስለዚህ ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀ በኋላ አዘጋጁ አካል የማዛመድ ስራ ይሰራል። 20 ሴቶችና 20 ወንዶች በፕሮግራሙ ከተሳተፉ የማዛመድ ስራው ሲሰራ ውጤቱ ከ0 እስከ 10 ሊሆን ይችላል ማለት ነው።

እርስ በርስ የተፈላለጉት (የተዛመዱት) አንዳቸው የአንዳቸው አድራሻ ይላክላቸውና በራሳቸው መንገድ ግንኙነታቸውን ይቀጥላሉ። በፈለጉት ሰው ያልተፈለጉ (ያልተዛመዱት) ደግሞ ውጤቱ ተነግሯቸው በሌላ ፕሮግራም እንዲሳተፉ ይደረጋል።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰው የመገናኘት (Speed Dating) አመጣጥ

በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰው ጋር የመገናኘት… የSpeed Dating ሃሳብ ያመጡት ራባይ ያቆብ ዲዮ የተባሉ የአይሁድ ሃይማኖት አባት ሲሆኑ ሃሳቡን ያፈለቁበት ምክንያትም ላጤ የሆኑ አይሁዳዊያን ፍቅረኛ አግኝተው እንዲጋቡ በማሰብ ነበር፡፡ እናም በታሪክ የመጀመሪያው የሆነው በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰው የመገናኘት (Speed Dating) የተከናወነው እ.ኤ.አ በ1998 ቤቨርሊ ሂልስ ሎስ አንጀለስ በሚገኘው ፒትስ ካፌ ውስጥ ነበር፡፡



Scanned by CamScanner
@BOOKALEM



## ኢንተርኔት ላይ በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰው መገናኘት
## (Online Speed Dating)

እንደ www.woome.com, www.speeddate.com... የመሳሰሉ በርካታ ዌብሳይቶች ጓደኛ ፈላጊ ላጤዎች በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰዎች ጋር መገናኘት የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች አሉዋቸው። ይህ የOnline Speed Dating ፕሮግራም ሰዎች ርቀት ሳይገድባቸው በቪዲዮ፣ በኦዲዮና በቴክስት በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ ዕድል ይሰጣል። የዚህ የOnline Speed Dating ሌላው ጥቅሙ ሰዎች ካሉበት ቦታ ሆነው ወደ ካፌና ወደ ሬስቶራንት መሄድ ሳይጠበቅባቸው... ስለ አለባበስና ስለ ወጪ ሳይጨነቁ... ያለ ወጪ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ሰዎች እንዲያገኙ ማስቻሉ ነው። እንደ ችግር የሚታየው ሰዎች ፊት ለፊት መተያየትና መነካካት አለመቻላቸው ነው።

## የመገናኘት... የDating ጥቅም

በፍቅር ዙሪያ በርካታ" መፃህፍት በመፃፍ የሚታወቁት ፕሮፌሰር ጆን ግሬይ "Mars And Venus On A Date" በሚለው መፅሃፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል፡

"ትክክለኛ የፍቅር ጓደኛ... የነፍስ ወዳጅ ማግኘት ልክ

አነጣጥር የዒላማ መሃል እንደመምታት ነው። አነጣጥር የዒላማውን መሃል ለማግኘት ደግሞ ብዙ ልምምድ ያስፈልጋል። በቀላሉ ተሳክቶላቸው ዒላማውን መምታት የሚችሉ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው። አብዛኛው ሰው ዒላማውን የመምታት ፍላጎቱን የሚያሳካው በብዙ ልምምድ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በፍቅር ዓለምም ብዙ ሰዎች ትክክለኛ የፍቅር አጋራቸውን የሚያገኙት በተደጋጋሚ የተለያዩ ሰዎችን በማግኘት ነው። በአንድ ጊዜ የነፍስ ወዳጃቸውን የሚያገኙ ሰዎች እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው።

"አነጣጥሮ ዒላማውን ለመምታት ሞክሮ ያልተሳካለት ሰው ካልተሳካው ሙከራው ተምሮ አስተካክሎ በማነጣጠር ዒላማውን ለመምታት ሙከራውን ይቀጥላል። አነጣጥሮ የለቀቀው ቀስት ከዒላማው በቀኝ በኩል ርቆ ከሄደ በቀጣዩ የቀኙን አጥብቦ ወደ ግራ እንዲያዘነብል አድርጎ በማሻሻል ቀስቱን ይለቃል። ዒላማውን እስኪመታ ድረስ ከስህተቱ እየተማረ ይቀጥላል።

"ትክክለኛ ፍቅረኛ... የህይወት አጋር... የነፍስ ጓደኛ ማግኘትም ልክ አነጣጥሮ ዒላማን እንደመምታት ነው። ብዙ በሞከርክና በሳትክ ቁጥር ጭንቅላትህ እንዴት አስተካክሎ ዒላማውን መምታት እንዳለበት እንደሚማር ሁሉ ብዙ ጊዜ ከተለያዩ ሴቶች ጋር እየተቀጣጠርክ በተገናኘህ ቁጥርም የምትፈልገውንና የማትፈልገውን ለይተህ ታውቃለህ"።

የብዙ ሰዎች የፍቅር ግንኙነትና የትዳር ህይወት በአጭሩ የሚቀጨው አሊያም በንዝንዝና በጭቅጭቅ የሚዘልቀው... ሰዎች የመገናኛቱን ጊዜ በአግባቡ ስለማይጠቀሙበትና ትክክለኛ ዒላማቸውን እስኪመቱ ድረስ ስለማይታገሱ እንዲሁም ‹ከዚህ የተሻለ ዒላማ መምታት አልችልም› ብለው ተስፋ ስለሚቆርጡ ነው።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ለፍላጎታችን ፍፁም የሆነ ሰው ማግኘት ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ልዩነቱን በደንብ ማጥበብ ይቻላል። ግንኙነቱ ወደ ፍቅር ጓደኝነት፣ ወደ መተጫጨት፣ ወደ ትዳር ካደገ በኋላ ልዩነቶች ሰፍተው አደጋ ከመፈጠሩ በፊት የአደጋ... የልዩነት... የችግር ማጣሪያ ማድረግ ይቻላል። የሚቻለውም ደስ ከሚሉን... ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር በተደጋጋሚ በመገናኘት እውነተኛ ባህሪያቸውንና ማንነታቸውን በማጥናት ነው። በባህሪና በአመለካከት መግባባት ላይ ልዩነቱ በጣም ከሰፋ ዒላማችንን ስተናል ብቻ ሳይሆን መሰረታዊ የርቀት፣ የመሳሪያ ወይም የአቋም ለውጥ ካላደረግን በስተቀር ደጋግመን ብንሞክርም ዒላማውን ልንመታው አንችልም ማለት ነው። እናም በተለያዩ ጥቃቅን አጓጊና ማራኪ ነገሮች ሳንታለል በባህሪና በአመለካከት በተሻለ ሁኔታ የምንግባባት ፍለጋ መንቀሳቀስ ይኖርብናል ማለት ነው።

ስለሆነም ዒላማው ተሳክቶልህ የነፍስህ ጓደኛ... የህይወት አጋር የምትሆንህን ትክክለኛ ፍቅረኛ ካገኘህ አሪፍ ነው። ካልሆነ ግን ቢያንስ ለዒላማው የቀረበች ለማግኘት ጥረት አድርግ። ተስፋ ቆርጠህ ወይም በስሜት... በሰዎች ተገፋፍተህ ከዒላማህ ውጪ ከሆነች ሴት ጋር የጠለቀ የፍቅር ግንኙነት... ትዳር ውስጥ አትግባ። ለሁለታችሁም አይጠቅምም። አንተም እሷም አንድ ጊዜ ብቻ ነው የምትኖሩት። ስለዚህ ደስታ አልባ የሆነ ህይወት በመኖር የአንድ ጊዜ ዕድሜ ያላት ውድ ህይወታችሁን ማባከን የለባችሁም።

ሲጠቃለል የ‹መገናኘት› ጥቅሙ የምትወዳት የምትወድህ፣ የምታብድላት የምታብድልህ፣ የምታስደስትህ፣ የምታስደስታት... ዕድሜህን ሙሉ በፍላጎትና በደስታ የምትሰጣት ሴት ለማግኘት የምትችልበት ሂደት ነው። እዚህ ላይ እንዲሰመርበት የምፈልገው... ፍፁም የሆነች ሴት ላታገኝ ትችላለህ። ነገር ግን በመነጋገርና

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

በመግባባት የምታምን፣ ላንተ መሰረታዊ ባህሪና አመለካከት የቀረበች መልካም ሴት ታገኛለህ። መልካም ሴት ለማግኘት መልካም ወንድ መሆን የግድ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ማለቴ ነው።

ስለዚህ ዒላማህን መተህ የምትሆንህን እስክታገኝ ድረስ በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መንገድ መገናኘትህን (Date ማድረግህን) ቀጥል።

## ምርቃት፡

ከሁሉም የመገናኘት ዓይነቶች ብዙ ሰዎችን ለፍቅርና ለትዳር በማብቃት በጣም ውጤታማ የሆነው የመገናኘት ዓይነት በጓደኞች በኩል የሚመቻቸው መሆኑን በበርካታ ጥናቶች ተረጋግጧል። በጋራ ጓደኞቻቸው በኩል የሚገናኙ ጥንዶች ተግባብተው… በፍቅር ጎዳና ተጉዘው ለጋብቻ ሰገነት የሚበቁበት አንዱ ሚስጥር በሚያገናኙዋቸው ጓደኞቻቸው ላይ የሚኖራቸው እምነት ነው።

ጓደኞቻችን ከማይሆን ሰው ጋር እንደማያገናኙን እናምናለን። ብዙ ጊዜም ይሰራል። ሌላኛው የስኬቱ ሚስጥር ደግሞ ጓደኞቻችን ከአንዲት ቆንጆ ጋር ቀጠሮ ይዘው የሚያገናኙን የሚያመሳስሉን ስሜቶች፣ ፍላጎቶች፣ ዝንባሌዎችና ራዕዮች አሉ ብለው ስለሚያምኑ ነው። ስለሆነም በጓደኛና በወዳጅ በኩል የሚመቻቹ ትውውቆች… ግንኙነቶች… ከሌሎች መንገዶች የበለጠ ውጤታማ ናቸው።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

# ሴቶች በፍቅር እንዲያሳድዱህ የሚያደርጉ 10 ጥበቦች

> የዕድሜ ልክ ዘላቂ ፍቅር የሚጀምረው ራስን ከመውደድ ነው
>
> አስካር ዋይልድ

የወንዶች የተለመደው አስተሳሰብ ሴቶችን አሳድዶ መማረክ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሴቶችን ለመተዋወቅና ለመማረክ የምንጠቀምበት መንገድም ይህ የማሳደድ ስትራቴጂ ነው፡፡ አንዲት ሴት ከስራ ወይም ከቤት የምትወጣበትን ሰዓት አሊያም ፌስቡክ ላይ ቻት የምታደርግበትን አጋጣሚ ጠብቆ ትኩረቷን ለመሳብ በመሞከር የሚደረገው አሳድዶ የመተዋወቅና የመማረክ ስትራቴጂ ውጤቱ ሁልጊዜ ያማረ አይሆንም፡፡ ማሳደድ ሊያስንቅ ይችላል፡፡ ማሳደድ የሴቷን ፍላጎት ሊገድል ይችላል፡፡

በተቃራኒው ሴቷ ራሷ እንድታሳድድህ ማድረግ ግን መልካም ውጤቱ የተረጋገጠ ነው፡፡ ቀጥለው የተዘረዘሩትን ጥበቦች ልብ ብለህ በማንበብ የልብህ ቋሚ ነብረት አድርጋቸው፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## ጥበብ 1፡ ማግኔት ሁን

- ብዙ ወንዶች ቆንጆ ሴቶች ሲያዩ ይንሰፈሰፋሉ፡፡ አንዳንዶቹ የሚያደርጉት ይጠፋቸውና ይርበተበታሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ልክ ማግኔት እንደሚስበው ብረት እየተጎተቱ ሴቶቹ ጋር ሄደው ይጣበቃሉ፡፡ መንሰፍሰፍ፣ መርበትበትና መጣበቅ ደግሞ የሴቶችን ትኩረት የሚስቡ ብቃቶች አይደሉም፡፡ ይልቁንም የሴቶችን ፍላጎት የሚገድሉ የደካማ ወንዶች ባህሪያት ናቸው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሰዓት አንተ የምትሳብ ብረት ሳይሆን ጎትቶ የሚስብ ማግኔት መሆን አለብህ፡፡ ሁሉም ወንድ ሲደናበርና ሲረባረብ አንተ ዘና ባልክ ቁጥር የሴቶችን ትኩረት ትስባለህ፡፡ ‹እሱ ምን ስለሆነ ነው እንዲህ የሚዝናናው?› የሚል ጥያቄ ታጭራለህ፡፡ የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘትም ሴቶች ወዳንተ ይመጣሉ፡፡

## ጥበብ 2፡ ብዙ ትኩረት አትስጥ

- ሴቶች ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጣቸው ይልቅ ትኩረታቸውን መሳብ ለሚችል ወንድ ይማረካሉ፡፡ በራስህ ህይወትና በራስህ ዓለም ደስተኛ የሆንክ ሰው እንደሆንክና እሷ መጣች ቀረች ደስታህ የማይጓደል ዓይነት ሰው ሆነህ ከታየህ ባንተ ዓለም ውስጥ መኖር የሚፈልጉ ሴቶች ያሳድዱሃል፡፡

## ጥበብ 3፡ የሚጠየቅና የማይጠየቅ ነገር እወቅ

- ከሴት ጋር ስትተዋወቅ ለምታደርገውና ለምትለው ነገር ጥንቃቄ አድርግ፡፡ ምክንያቱም ሴቶች ቀድሞ የሚመጣባቸው ነገር መጀመሪያ ስትተዋወቅ ያልከውና ያደረግከው ነገር ነው፡፡ በአሪፍ ሁኔታ ከተዋወቅካቸው አሪፍ ነገር ይመዘግቡልሃል፡፡ ድክም ባለሁኔታ ከተዋወቅካቸው ደግሞ በደካማነትህ ያስታውሱሃል፡፡ ስለዚህ ከሴት ጋር ስትተዋወቅ ማለት ያለብህና የሌለብህን ማወቅ አለብህ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

መጠየቅና መጠየቅ የሌለብህን ነገርም እንደዛው።
ፍፁም መጠየቅ የሌለባቸው ጥያቄዎች… ምን ዓይነት ወንድ ነው ይሉ የሚልሽ?፣ ሕኔ አንቺ የምትፈልጊው ዓይነት ወንድ ነኝ?፣ ጓደኛ አለሽ?…።

ክፍተኛ ፍላጎት እንዳለህና ራስህን ዝቅ አድርገህ የምታይ ሰው መሆንህን የሚጠቁሙ ዓይነት ጥያቄዎችን በፍፁም አትጠይቅ። ራስህን ብሬት ሳይሆን ማግኔት… ፈላጊ ሳይሆን ተፈላጊ አድርገህ እመን… ቅረብ።

## ጥበብ 4፡ ድንጋይ ሳይሆን አልማዝ ሁን

- አልማዝና ወርቅ የድንጋይ ዘር ናቸው። ነገር ግን በቀላሉ… የትም ስለማይገኙ በጣም ውድና ቷጥ ሊሆኑ ችለዋል። ድንጋይ ግን የትም… በቀላሉ ስለሚገኝ የወርቅና የአልማዝን ያህል ክብር ሊያገኝ አልቻለም።

በምትፈልጋት ሴት ዙሪያ ሁልጊዜ የማትጠፋ ከሆነ ላንተ የተለየ ክብርና ፍላጎት አይኖራትም። ልክ እንደ አልማዝ ብርቅ ከሆንክ ግን ሁሉም የራሳቸው ሊያደርጉህ… ሊያገኙብህ ይፈልጋሉ። ያሳድዱሃል።

ናፍቆት ልብ ውስጥ ፍቅር ይዘራል። ተናፋቂ ሁን። በናፍቆት የምትታይ… በናፍቆት የምትሰማ (አልፎ አልፎ የምትደውል) ከሆነ የበለጠ ትፈለጋለህ።

‹ብእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል› የሚባለው ያለ ምክንያት አይደለም።

## ጥበብ 5፡ ከልክ ካለፈ አድናቆት ተቆጠብ

- እውነት ነው ሴቶች አድናቆት ይወዳሉ። ነገር ግን አድናቆት

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ሲቸራቸው ከመስማት ይልቅ አድናቆት ለመስማት የሚጓጉት ጊዜ የበለጠ ስሜታቸውን ከፍና ዝቅ በማድረግ እንዲማረኩ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ በሆነ ባልሆነው በአድናቆት አታወድሳቸው፡፡ በተለያዩ ስጦታዎች አታንበሻብሻቸው፡፡

ብዙ ወንዶች እንደሚያደርጉት ውበታቸው ላይ ከማተኮር ይልቅ እውቀታቸው፣ ስራቸውና ባህሪያቸው ላይ ያተኮረ አድናቆት ቸራቸው፡፡አንዲት ሴት አድናቆት ከምታዘንብላት ይልቅ ‹ብህልሚ እየሁሹ› የሚል ጨዋታ ቀለል አድርገህ ጣል ብታደርግላት የበለጠ ትደሰታለች፡፡ ለየትና የተቆጠበ የአድናቆት ስታይል የምትከተል ከሆነ የበለጠ የመስማት ፍላጎት ያድርባታል፡፡

**ጥበብ 6፡ እንዲያስቡህ አድርጋቸው**

- ሴቶች እንዲያሳድዱህ ከፈለግክ መጀመሪያ እንዲያስቡህ ማድረግ አለብህ፡፡ ብዙዎቻችን እንዲያስቡን ከማድረግ ይልቅ እነሱን በሃሳባችን በማመላለስ ውስጥ እንዘፈቃለን፡፡ እነሱን በማሰብ የመዘፈቁ ነገር ይብቃና አሁን አንተ ታሪኩን ቀይረው፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በትክክል ተግባር ላይ ካዋልካቸው ማግኔት ሆነህ ሴቶችን መሳብ ትጀምራለህ፡፡ እናም አንዳንድ ሴቶች ሊያገኙህ በመፈለግ ‹ሻይ እንጠጣ›፣ ‹ሲኒማ እንግባ› የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ያቀርቡልሃል፡፡ ምክንያት አቅርበህ የመጀመሪያ ጥያቄያቸውን በትህትና ውድቅ ካደረግክባቸው ጠቅልለህ ጭንቅላታቸው ውስጥ ትገባለህ፡፡ በሃሳባቸው ትመላለሳለህ... አንተን ለማግኘት ብዙ እቅዶችን በመንደፍ ይጠመዳሉ፡፡

  ‹... ደስ ይለኝ ነበር፤ ግን የአሁኑ ዓርብ ሌላ ፕሮግራም አለኝ›፣ ‹...አሪፍ ሃሳብ ነበር ነገር ግን በዚህ ሳምንት ጨርሼ ማስረከብ ያለብኝ ስራ ስላለ አልችልም›... ግብዣቸውን ላለመቀበል ለምትጠቀምባቸው ምክንያቶች በምሳሌነት የቀረቡ ናሙናዎች ናቸው፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

## ጥበብ 7፡ መራጭ እንጂ ተመራጭ አትሁን

- ሴቶች እንዲያሳድዱህ ከፈለግክ የተለመደውን የመራጭና የተመራጭ አስተሳሰብ ለውጥ አድርገህ ተንቀሳቀስ፡፡ ብዙ ወንዶች በሴቶች ተመራጭ ለመሆን በሚፈጋበብበት ዓለም አንተ የተለየ... መራጭ የመሆን አቋም ይዘህ ብቅ ስትል ወዲያው ከሌሎች ወንዶች ጎልተህ ትታያለህ፡፡

እንደ ቀልድ አስመስለህ ‹ከሌሎች ሴቶች የበለጠ ማራኪ የሚያደርግ ነገር ምን አለሽ?› የሚል ጥያቄ ጣል ስታደርግላቸው የፉክክር መንፈስ ያድርባቸዋል፡፡ ከሌሎች በልጠው ለመመረጥ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

## ጥበብ 8፡ ስታገኛቸው አስቃቸው

- ብዙ ጊዜ ወንዶች ሴቶችን የማነጋገር እድል ስናገኝ ውሃ እስኪጠማን ድረስ ስለራሳችን በማውራት እናሰለቻቸዋለን፡፡ ስለሆነም ለሁለተኛ ጊዜ እንዲያገኙን ፍላጎት ሊያድርባቸው ቀርቶ ሲያስታውሱን ራሱ ያቅለሸልሻቸዋል፡፡

ስለዚህ ከሴቶች ጋር ስትገናኝ ስለ ራስህ የፊደል ካስትሮን ዓይነት ረዥም ንግግር ከማድረግ ይልቅ አንድ ጊዜ አስቃቸው፡፡ ሴቶች በተፈጥሮ (ባዮሎጂካሊ) ለሚያስቃቸው ወንድ ይማረካሉ፡፡ ማሳቅ የሴት ልብና ጭንቅላት ውስጥ ለመግባት አቋራጭ መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም ሴቶች ለተመሳሳይ ሳቅና ጨዋታ ሊያገኙህ ይፈልጋሉ፡፡

## ጥበብ 9፡ ጥይት አታባክን

- ራስህን የተገለጠ መፅሃፍ አድርገህ እንደፈለጉ እንዲያነቡህ አታድርግ፡፡ በሆነ አጋጣሚ ጨዋታ ሲጀመር አውቶማቲክ አትተኩስ፡፡ ስምህን ለማስተዋወቅ ከዛም አልፎ ስለ ራስህ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ለመናገር አትቸኩል፡፡

ስለ ራስህ ለመናገር... ራስህን ለማስተዋወቅ ባልተጣደፍክ ቁጥር ስላንተ የማወቅ ጉጉታቸው ከፍ ይላል፡፡ ስምህን ሲጠይቁህ ብቻ ንገራቸው፡፡ ጥልቅ ወደሆነ ጨዋታ ሲገቡ ሲፈልጉ ‹ይቅርታ አሁን መሄድ አለብኝ...ምናልባት ሌላ ጊዜ እንገናኛለን› በላቸው፡፡ የማወቅ ፍላጎታቸው ሊያሳብዳቸው ይደርሳል፡፡ ሚስጥራዊነት ጉጉት ይፈጥራል፡፡ ሁለቱም ሲደመሩ ደግሞ መማረክን ያስከትላሉ፡፡ ስለዚህ ራስህን ለማወቅ የሚያጓጓ ሚስጥራዊ ሰው አድርገህ ቀረብ፡፡

## ጥበብ 10፡ ያሳድዱህ እንጂ አታሳድዳቸው

- ራስህ ላይ ኢንቨስት በማድረግ ሴቶች የሚመኙት ዓይነት የራስህ ደስ የሚል ዓለም ፍጠር፡፡ ደስታን ከሌሎች ለማግኘት የሚንቀዠቀዥ ሳይሆን ለሌሎች የሚተርፍ ደስ የሚል አንጊ ህይወት ያለው ስብዕና ገንባ፡፡ ያኔ ሴቶችን የምታሳድድ ሳትሆን ሴቶች የሚያሳድዱህ ተፈላጊ ሰው ትሆናለህ፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



# የመተዋወቅ ጥበብ

ማፍቀር ልክ በመብረቅ እንደመመታት ነው ይባላል፡፡ መብረቅ በቀጠሮ አይመታም፡፡ ፍቅርም እንደዛው ነው፡፡ መቼና የት እንደሚይዝህ አታውቀውም፡፡ የመብረቅ መከላከያ ባለባቸው ቦታዎች ስትሆን መብረቅ እንደማይመታህ ሁሉ ሴቶች የማይከሰቱበትን ቦታ የምታዘወትር ከሆነም የፍቅር መብረቅ ሊመታህ አይችልም፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን የስራ ወይም የመኖሪያ ቦታህ በፍቅር መብረቅ ለመመታት የማያስችልህ ቢሆንም በእረፍት ጊዜህም ቢሆን ለፍቅር መብረቅ ወደሚያመቻቹህ ስፍራዎች መንቀሳቀስ ይኖርብሃል፡፡

ጊዜው ደርሶ የፍቅር መብረቅ ሲመታህ ደግሞ ‹ትውውቅ› የሚባለው ጥበብ ይከተላል፡፡ ደስ ያለችህን ቆንጆ ለመተዋወቅ ልታደርጋቸውና ላታደርጋቸው የሚገቡ እውነታዎችን በዝርዝር እንያቸው…

## 1. ቦታና ጊዜ ምረጥ

- ደስ የምትልህን ሴት ለመተዋወቅ የምትመርጠው ቦታና ጊዜ ወሳኝ ነው፡፡ ጭር ባለ ቦታ ጠብቀህ ልትተዋወቃት ብትሞክር

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ፈርታህ ልትሸሽ ትችላለች። ጨለማ ላይ ከጠበቅካትም እንደዛው። በስራ በተጠመደችበትና ከሰዎች ጋር በተመስጦ በምታወራበት ጊዜ ለመተዋወቅ ከቀረብካትም አስፈላጊውን ትኩረት ላትሰጥህ ትችላለች... ዴንዘል ዋሺንግተን ካልሆንክ በስተቀር። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ፍፁም አትጠቀም።

- በማያስፈራ ጊዜና ቦታ... እንደ ካፌ፣ መንገድ፣ ሞል፣ ባር፣ ክለብና ማንኛውም መዝናኛ ስፍራዎች ቀርቦ ለማናገር... ለመተዋወቅ አሪፍ ቦታዎች ናቸው።

## 2. ዓይኖችዋን በዓይኖችህ ተመልከት

- ዓይኖችዋን በዓይኖችህ ለተወሰኑ ሴኮንዶች ተመልከታቸው። ይህ ሁለት ጠቀሜታ አለው... አንደኛ ዓይኖችዋን ትኩር ብለህ ስትመለከታቸው በቀጥታ ቬንትሪያል ስትራተም ከተባለው አንጎልዋ ውስጥ ከሚገኘው አካል ጋር አስተዋውቆ ያስመዘግብሃል። ሁለተኛ ትኩር ብለህ ስታያት የማትፈራ ደፋር እንደሆንክ መልዕክት ታስተላልፋለህ። ዓይን ለዓይን መተያየቱ በዝቶ ወደ ማፍጠጥ መሸጋገር ግን የለበትም። አይተሃት መልሳ ስታይህ ደንግጠህ ወይም አፍረህ ማጎንበስም የለብህም።

 ...'እሺ ታዲያ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ... ቶሎ ንገረኝ' እያልክ እንደሆነ ይሰማኛል።

- ዓይን ለዓይን ከተያያችሁ በኋላ ፈገግ ብለህ በራስ በመተማመን ስሜት ወደ እሷ ተራምደህ ታወራታለህ።

## 3. መክፈቻ ጨዋታ

- ዓይኖችዋንና ዓይኖችህን አስተዋውቀህ ፈገግታህን አስከትለህ በራስ መተማመን ስሜት ከቀረብካት በኋላ ቀጣዩ ነገር ትኩረቷን

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

የሚስብልህን መክፈቻ ንግግር ማድረግ ነው፡፡ ጨዋታውን ለመጀመር ያላችሁበትን አካባቢ ሁኔታ ብትጠቀም ይመረጣል፡፡ በተለይ መረጃ በመጠየቅ መጀመር ሁልጊዜ ውጤቱ አሪፍ ነው፡፡ ሰዎች በተፈጥሮ የሚያውቁትንና የሚችሉትን ማድረግ ያስደስታቸዋል፡፡

ለምሳሌ ሱፐርማርኬት ውስጥ ከሆናችሁ ‹ታዲያስ… ብዙ ዓይነት ቆሎ ነው የተደረደረውና አሪፉ ቆሎ የትኛው ነው?› ብለህ ልትጀምር ትችላለህ፡፡ የአካባቢህን ሁኔታ በመጠቀም የሆነ መረጃ ወይም አቅጣጫ በመጠየቅ ጨዋታውን መክፈት ትችላለህ፡፡ ሌላ አሪፍ ጨዋታ መክፈቻ ርእስ ደግሞ በሆነ ጉዳይ የእሷን አስተያየት መጠየቅ ነው፡፡

**ለምሳሌ…**

‹ጓደኛዬ ለማግባት እየተዘጋጀ ነው፡፡ ድንገት ሊያገባ ሲል የቀድሞ ፍቅረኛው መደወል ጀመረች … ጓደኛዬ በሁኔታው ግራ ተጋብቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ያንቺ አስተያየት ምንድነው?›

በእንደዚህ መልኩ ጨዋታውን ጀምረህ ትኩረቷን ከያዝክ በኋላ ቀልብ ማራኪ ወደሆኑ የወሬ ርእሶች መግባት ነው፡፡ ‹በነገራችን ላይ አለባበስሽ ያምራል›… በሚል አድናቆት ፍላጎትህን አንፀባርቀህ ሌላ የወሬ አጀንዳ መክፈት ትችላለህ፡፡

ጨዋታውን ለማድራት በምትሰጥህ አስተያየት ብስለቷን፣ የአነጋገር ለዛዋን፣ አለባበሷን… ሳይበዛ ማድነቅ ትችላለህ፡፡ ከዛ አልፈህ በሌላ የሰውነት አካላቷ ላይ አስተያየት አትስጥ፡፡ በመጀመሪያው ትውውቅ ዘሎ ወደ ጡትና ዳሌ ጉብ ማለት ትውውቁን አደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡

- ልትተዋወቃት የፈለግካት ልጅ ተመሳሳይ ፍላጎት እንዳላትና እንደሌላት የማንበብ ጥበብ ሊኖርህ ይገባል፡፡ ስታወራት አጭር

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

መልስ ሰጥታ የምትሸሽ ዓይነት ከሆነች ፍላጎት የላትም ሊባል ይችላል። በፈገግታ የምትመልስና ለተጨማሪ ጨዋታ ዝግጁ ከሆነች ፍላጎት እንዳላት ያሳያል። ፍላጎት ከሌላት ሴት ጋር ከሆነች ፍላጎት እንዳላት ያሳያል። ፍላጎት ከሌላት ሴት ጋር በግድ ለማናገር መሞከር የሰው መብት ጊዜህን አታጥፋ። በግድ ለማናገር መሞከር የሰው መብት መጋፋት ጭምር መሆኑንም አትርሳ።

## 4. ጨዋታውን በአሪፍ ሁኔታ ቋጨው

- ከማረከችህ ልጅ ጋር የተጀመረን ጨዋታ መቋጨት ፈታኝ ነው። በተለይ በደንብ ፊት ሰጥታህ እያዋራችህና እየሳቀችልህ ከሆነ ጨዋታው እንደ ማር ይጣፍጥሃል። ትታለላለህ። ይሄንን ደጋግመህ አንብበህ ብትሄድም ጨዋታውን ማቋረጥ ይፈትንሃል። ውስጥህ ‹ብርሃኔ የፃፈውን ተወው ባክህ…ማነው እሱን አዋቂ ያደረገው› ይልሃል። ግን እመነኝ በቅፅበታዊ ደስታ ሳትታለል ጨዋታውን እየጣፈጠህ መቋጨቱ ልጅቷን የግልህ ለማድረግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

እንዴት በለኝ…

በመጀመሪያው ትውውቅ ራስህን ጥለህ ጨዋታውን ስታራዝም ሳታውቀው… ስራ ፈት መሆንህንና በእሷ መዝረክረክህን የመሳሰሉ ጥሩ ያልሆኑ መልዕክቶች ታስተላልፋለህ። ጨዋታው በጣም ጣፋጭ እያለ ካሳጠርከው ደግሞ በተቃራኒው… የምትቸኩልና ከእሷ ጋር ለመጫወት ስትል ከእቅድህ ውጭ የማትወጣ ጠንካራ ወንድ መሆንህን ታሳያለህ። በመጀመሪያው ትውውቅ እንደዚህ ዓይነት ጥሩ ነጥቦች ማስመዝገብ ለግንኙነቱ ቀጣይነት መሰረት ይጥላል። በዚህ ከተስማማን ጨዋታውን እንዴት በአሪፍ መቋጨት እንዳለብህ እንመልከት።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## 5. የትውውቁ መልካም አጨራረስ

- የትውውቁ ሂደት የሚጠይቀውን በሙሉ በጥሩ ሁኔታ አከናውነህ በወሳኙ ምዕራፍ ላይ ደርሰሃል። ትውውቁ በመልካም ሁኔታ ተጠናቀቀ የምንለው ደግሞ የሁለታችሁን ግንኙነት የሚያስቀጥል ስራ ስታከናውን ነው። ጨዋታው ተመችቷት ብዙ ለማውራት ፍላጎት እያላት ወሬውን አሳጥረህ ሌላ ጊዜ እንዲቀጥል ቀጠሮ አስይዘህ መለየት ራሱን የቻለ ጥበብ ነው።ሰዓትህን እየት አድርገህ ሊሆን ይችላል... ‹ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ... ካንቺ ጋር ማውራት በጣም ደስ ይላል... ግን አሁን የግድ መሄድ አለብኝ... ሌላ ጊዜ ተገናኝተን ጨዋታውን ብንቀጥለው ደስ ይለኛል› በሚል ዓይነት ስልኳን ተቀብለህ ላጥ ማለት አለብህ። ሌላ ጊዜ ለመገናኘት ስልኳን ተቀብለህ ስትሄድ ብቻ ነው የትውውቁ ሂደት አስደሳች ፍፃሜ አገኘ የሚባለው።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



‘ ወንዶች መጨረሻ ላይ የተሳሙትን ማስታወስ
ሲያቅታቸው፤ ሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ
የተሳሙትን ዕድሜ ልክ አይረሱትም ’

ሬሚ ዴ ጉርሞንት

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

# ፍላጎት እንዳላት የሚያሳዩ 10 ምልክቶች

አለመታደል ሆኖ ሴቶች ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን የሚያሳዩት... የሚገልፁት በብዛት በድርጊትና በእንቅስቃሴ ነው፡፡ አሁንም አለመታደል ሆኖ እኛ ወንዶች ደግሞ ሴቶች ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን የሚገልፁባቸውን ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎች አንብቦ የሚረዳ የስሜት ህዋስ የለንም፡፡ ስለሆነም ብዙ ጊዜ የመግባባት... የመናበብ ችግር ይፈጠራል፡፡ ቬነሳዊያን ሴቶች) የሚናገሩዋቸውን ልዩ ልዩ ቋንቋዎች (የምልክት ቋንቋ፣ ቀጥተኛ ያልሆነ የአነጋገር ቋንቋና የዝምታ ቋንቋ) ማጥናት እንዳለብህ ተነጋግረናል፡፡ ሶሻል ሪሰርች ሴንተር የተባለ የጥናት ማዕከል በዚህ ጉዳይ ላይ ያደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው ሴቶች የመማረክ ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ለመግለፅ ሰላሳ ስምንት በመቶ (38%) ንግግር የሚጠቀሙ ሲሆን ሃምሳ አምስት በመቶ (55%) ደግሞ ድርጊትና እንቅስቃሴ ይጠቀማሉ፡፡ ቀሪው ሰባት በመቶ (7%) ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ለመግለፅ ሳይሆን እንዲሁ ለመግባባት የሚጠቀሙበትን ንግግር ይሸፍናል፡፡

በጥናቱ መሰረት ከማድመጥ ችሎታ በተጨማሪ (በላይ) ድርጊታቸውንና እንቅስቃሴያቸውን በማንባ የሚከታተልና የሚተረጉም ንቃ ያለ የስሜት ህዋስ ሊኖረን ይገባል፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

አንዲት ሴት ሆን ብላ በማወቅና ባለማወቅ በድርጊቷና በንግግር የምታሳያቸውን ምልክቶች በሚገባ በማስተዋልና በመተርጎም ፍላጎቷን መረዳት ይቻላል።

ቀጥለው ከተዘረዘሩት የድርጊትና የንግግር ምልክቶች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ካስተዋልክ ልጅቷ ፍላጎት አላት ማለት ነው። ምልክቶቹን አንድ በአንድ እንያቸው...

## ሀ. ፀጉር መጠቅለል... በፀጉር መጫወት

- አጠገብህ ተቀምጣም ይሁን በርቀት አንተን እያየች ፀጉሯን የምትጠቀልል... በፀጉሯ የምትጫወት ከሆነ ፍላጎቷን እየገለፀች ነው። ፀጉሯን የምትጠቀልለው አሊያም በፀጉሯ የምትጫወተው ሆን ብላ ላንተ መልዕክቱን ለማስተላለፍ ሳይሆን ውስጧ ያለው ፍላጎትና ስሜት ሳይታወቃት እንደዛ እንድታደርግ ስለሚያስገድዳት ነው።

## ለ. ከንፈር መምጠጥ... ከንፈር መንከስ

- ከንፈር መምጠጥ... ከንፈር መንከስ ሴቶች ሳይታወቃቸው የሚያከናውኑት ሌላ የፍላጎት... የስሜት ምልክት ነው። ይህ ምልክት ያንተን ትኩረት ወደ ከንፈሯ ለመሳብና የመሳም ፍላጎት እንዳላት ለመግለፅ የሚተላለፍ ምልክት ነው።

**ማሳሰቢያ:**

ይህንን ምልክት በደንብ አስተውሎ መተርጎም ያስፈልጋል። አልፎ አልፎ የምታደርገው ከሆነ ከላይ የተገለፀውን መልዕክት ያስተላልፋል። ነገር ግን ልጅቷ ሁልጊዜ ከንፈሯን የምትመጥና የምትነክስ ከሆነ መጥፎ ልማድ እንጂ ‹ና ሳመኝ› የሚል ምልክት

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

አይሆንም። ስለዚህ ዘለህ ጉብ ከማለትህ በፊት ምልክቱን በሚገባ ማጥናትና መረዳት ያስፈልጋል።

ልጅቷ የምታደርጋቸው ሌሎች ምልክቶችና የምትናገራቸውን ቃላት እንደ ተጨማሪ ማስረጃ ተጠቀም። የከንፈር መምጠጥና መንከሷ ‹ና ሳመኝ› የሚል ምልክት ከሆነ በሌሎች ድርጊቶቿና በምትናገራቸው ነገሮች ታጠናክረዋለችና ነው።

## ሐ. በአካል መጠጋት

- አንድ ላይ ፊት ለፊት ተቀምጣችሁ በምታወሩበት ጊዜ ወዳንተ የበለጠ የምታዘነብል ከሆነ ሌላው በፍላጎት ማሳያነት የሚጠረጠር ምልክት ነው። እጆቿን አጣምራ ወደኋላ ለጠጥ ስትል የፍላጎት አለመኖርን እንደሚያሳይ ሁሉ እጆቿን ከፍታ… ፈታና ዘና ብላ ወዳንተ ከተጠጋች ደግሞ ካንተ ጋር በአካል የመቀራረብ… የመተቃቀፍ ፍላጎት እንዳላት የሚያሳይ ነው።

## መ. ያልተጠበቀ ግልፅነት

- ሰዎች ሚስጥራቸውን የሚነግሩት በጣም ለሚቀርቡት… ለሚወዱት ሰው ነው። ሚስጥር መጋራት የወዳጅነትና የቅርበት መለኪያ ተደርጎም ይወሰዳል። እናም ሚስጥር እንኳን ባይሆን ገና በደንብ ሳትቀራረቡ ባልተጠበቀ ግልፅነት የተለያዩ የራሷና የቤተሰቦቿን ታሪኮች ካወራችህ ካንተ ጋር ያላትን የመቀራረብ ፍላጎት የሚያሳይ አንድ ምልክት ነው።

ሴቶች ታሪካቸውን በዝርዝር ከነገሩህ በኋላ ግራ ተጋብተው ‹ምን አስነክተኸኝ ነው እንደዚህ የዘከዘኩልህ?› ይላሉ። ይህ የሚሆነው ውስጣዊ ፍላጎታቸው ገፋፍቶ ሳይታወቃቸው ካወሩ በኋላ ብንን ስለሚሉ ነው።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

## ሰ. የምታደርገውን መድገም

- ሴቶች ሳይታወቃቸው ከሚያደርጉዋቸው ነገሮች መካከል አንዱ "Mirroring" የሚባለው ምልክት ነው። አንዱ የሚያደርገውን ሌላው ሰው ሲደግመው ‹ሚረሪንግ› ይባላል። ልክ ራሳችንን መስተዋት ፊት ላይ ቆመን የምናደርገውን እንቅስቃሴ በሙሉ መስተዋቱ ላይ እንደምናየው ማለት ነው። ‹ሚረሪንግ› የተባለውም ለዛ ነው። ስለዚህ አንዲት ሴት አንተ የምታደርገውን እንቅስቃሴ የምትደግም ከሆነ ፍላጎት እንዳላት የሚያሳይ ምልክት ነው። ለምሳሌ አንድ ላይ ምግብ እየበላችሁ እያለ ያንተን እንቅስቃሴ እየተከተለች... አንተ ስታነሳ እያነሳች... ስትጎርስ የምትጎርስ... የውሃ ብርጭቆህን ስታነሳ... የምታነሳ... ስትጠጣ የምትጠጣ... እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎችን አንተን እየተከተለች የምትደግም ከሆነ ሳታውቀው ፍላጎትዋን እየገለፀችልህ ነው። ይህ ምልክት ሳትቀራረቡ በርቀትም ሊታይ ይችላል። በርቀት እያየችህ አንተ የምታደርገውን ልታደርግ ትችላለች።

## ረ. አንገት መስበር + ፈገግታ

- የሴት ልጅ ፈገግታ በራሱ የሚያስተላልፈው የምስራች አለው። በተለይ አንገት መስበር እና ፈገግታ ተደምሮ የሚሰጠው ውጤት ደግሞ ‹ልቤ እንደወደደህ ተረዳልኝ› የሚል ዓይነት ነው። ከርቀትም ይሁን ከቅርበት አንገቷን ወደ ጎን ሰበር አድርጋ ፈገግታ ብልጭ ካደረገችልህ... እንኳን ደስ አለህ።

## ተ. የዓይን ጨዋታ

- ሴቶች መፈለጋቸውንም ሆነ አለመፈለጋቸውን ለማሳየት የሚጠቀሙበት ትልቁ መሳሪያቸው... ኒኩሌራቸው ዓይናቸው

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ነው። ከፈለጉህ ደጋግመው ኒኩሌራቸውን ስለሚተኩሱብህ (ደጋግመው ስለሚያዩህ) ዓይን ከፈንጅ ትደዛቸዋለህ። ካልፈለጉህ ደግሞ ጭራሽ ላያዩህ ይችላሉ። እንደምንም ብለህ በራስህ ጥረት ዒላማቸው ውስጥ ብትገባላቸው እንኳ አንዴ በዓይናቸው ድባቅ ያደርጉሃል እንጂ ደግመው አያዩህም። ስለዚህ ሴት ከፈለገችህ ዓይኗ ልክ ለሃይል ማመንጫ እንደሚያገለግል የልማት ኒኩሌር ይሆናል። ካልፈለገችህ ደግሞ እንደ ሂሮሺማና ናጋሳኪ አጋይታህ የምታልፍበት የጦርነት ኒኩሌርዋ ነው። ስለዚህ ደጋግማ ስታይህ ዓይን ለዓይን ከተጋጫችሁ መልካም መልዕክቱ ይድረስህ።

## በ. ትጠይቅሃለች

- ፍላጎት ሲኖራት የበለጠ አንተን የማወቅ ጉጉት ስለሚያድርባት በተለያዩ ጥያቄዎች ታጣድፍሃለች። ከልጅነትህ ጀምሮ እስከ አሁኗ ቅፅበት ድረስ ያለውን ታሪክህን መስማት ትፈልጋለች። ስታወራት በከፍተኛ ጉጉት ታዳምጣለች።

**ማሳሰቢያ፡**

ምንም እንኳን አንተን የማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖራትም የምትጠይቅህን ጥያቄ በሙሉ በመመለስ ማወቅ የፈለገችውን ሁሉ በአንዴ አታሳውቃት። በአንዴ ካወቀችህ ሌላ ጊዜ አንተን የማግኘት ፍላጎቷ ሊቀንስ ይችላል። ‹ቀሪውን ደግሞ ሌላ ጊዜ› ብለህ ጨዋታውን አሳጥረው።

## ቸ. ትንከባከሃለች… ትመታሃለች

- በጨዋታ መሃል በእጇ እጅህን፣ ትከሻህንና ጀርባህን ከነካካችህ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሳይታወቃት ፍላጎት እንዳላት እየነገረችህ ነው። አሁንም በጨዋታ መሃል በቀልድ መልክ ‹አንተ!› በሚል ዓይነት መታ የምታደርግህ ከሆነ… ‹ብንነካካ… የበለጠ ብንቀራረብ… ብንተቃቀፍ ደስተኛ ነኝ› የሚል ስውር መልዕክት እየተላለፈልህ ነው።

## ከ. ትስቅልሃለች

- ለጓደኞችህ ነግረሃቸው ያላሳቃቸውን ቀልድ ስትነግራት ከት ብላ ከሳቀች ‹ይኸው ቀልዴ ያስቃል!› ብለህ እንዳትኩራራ። ከት ብላ የሳቀችው ቀልድህ የሚያስቅ ሆኖ ሳይሆን ስለምትወድህ… ስለምትፈልግህ ነው። ምክንያቱም ሴቶች ፍላጎታቸውን የሚያሳዩበት መንገድ አንዱ መሳቅ ነው። ከወደዱህ የምትነግራቸው ቀልድ ቢያስቅም ባያስቅም ይስቁልሃል።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

# ስልክ ቁጥር የመቀበል ጥበብ

'በፍቅር ግንኙነት፤ የመጀመሪያው ጥበብ
ስልክ ቁጥር መቀበል ነው'
እኔ

ከሴት ልጅ ስልክ ቁጥር መቀበል እና ከአውሮፕላን በፓራሹት መዝለል አንድ ናቸው። መቶ ጊዜ ከአውሮፕላን በተሳካ ሁኔታ የመዝለል ልምድ ቢኖርህም ለመቶ አንደኛ ጊዜ ስትዘል መፍራትህ አይቀርም። ከሴት ልጅ ስልክ ቁጥር ስትቀበልም ተመሳሳይ ነው። አስር ሺ የሴቶች ስልክ ቁጥር የያዘ ማውጫ መፅሃፍ (ዳይሬክተሪ) ለማሳተም የአንዲት ሴት ስልክ ቁጥር ብቻ ቢቀርህ እንኳን አንዷን ስልክ ቁጥር ለማሟላት ወደ አዲስ ሴት ስትራመድ ልብህ ድው ድው ማለቱ አይቀርም። ከአውሮፕላን ለመዝለል ስትዘጋጅ የሚያስፈራህ የመከስከስ አደጋ ሲሆን ከሴት ልጅ ስልክ ቁጥር ለመቀበል ስትራመድ የሚያስፈራህ ደግሞ ‹እምቢ ልትለኝ ትችላለች› የሚል ስጋት ነው። ወደ ሴት ልጅ ተራምዶ ስልክ ቁጥር የመቀበል ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ወንዶችም ልባቸው ድው ድው ይላል።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ጠረቀት ሰጥተህ ጠይቃት... እንዳትዝረከረክ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ተደራጅተህ ከጠየቅካት ባለ አስር ዲጂት ስልክ ቁጥሯን ትሰጥሃለች፡፡ እንደውም ሂደቱን ለማቅለልና ዘና ለማድረግ በጣም እርግጠኛ ሆነህ ‹09...› ብለህ ቀሪውን እንድትነግርህ አመቻቻት!

- ልብ በል... ጨዋታው ጣፍጦህ ተንከርፍፈህ እስክትሰለች ድረስ ካወራሃት... የመለማመጥ ስሜት ካሳየህ... ከተርበተበትክ... ስልክ ቁጥሯን የማግኘት ዕድልህ ከዜሮ እስከ እጅግ በጣም በጣም አነስተኛ ድረስ ይሆናል፡፡ ካዘነችልህ ደግሞ የአንዱ ኤፍ ኤም ሬድዮ ስልክ ቁጥር ወይም አንድ ዲጂት የጎደለው ስልክ ቁጥር ሰጥታ ታሰናብትሃለች፡፡

- ደስ የምትልህን ሴት ቀርበህ ማነጋገር... መተዋወቅና ስልክ ቁጥር መቀበል ወደ ጦር ሜዳ እንደመዝመት አድርገህ አትየው፡፡ ቀለል አድርገው፡፡

- አያቶችህ ምናልባትም ወላጆችህ የሞባይል ስልክ፣ የቴክስት፣ የኦንላይን ዴቲንግ፣ የፌስቡክና የትዊተር ቴክኖሎጂ ባልነበረበት ጊዜ ተዋውቀው... ተቀጣጥረው... ተፋቅረው... መርፌና ክር ሆነው አንተን ወልደዋል፡፡ አንተ በዚህ ሁሉ የዘመኑ ቴክኖሎጂ እየታገዝክ የህይወትህ ውበትና ጣዕም የምትሆን ሴት እንዴት ማግኘት ያቅትሃል? በል ተንቀሳቀስ፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



## ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ሄደህ መርከብ አትጠብቅ! ፍላጎት እንደሌላት የሚሳዩ 7 ምልክቶች

> "ፍቅር ሁለት ሰዎች ተወዳድረው ሁለቱም አሸናፊ የሚሆኑበት ጨዋታ ነው"
>
> ኢቫ ጋቦር

የማትወድህ... የማትፈልግህ ሴት ጋር መጣበት አውሮፕላን ማረፊያ ሄዶ መርከብ እንደመጠበቅ ነው። መርከብዋ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ መጥታ ልታገኛት እንደማትችል ሁሉ የማትወድህ... የማትፈልግህ ልጅም እጅህ ልትገባ አትችልም። ስለዚህ አውሮፕላን ማረፊያ ቁጭ ብለህ መቼም የማትመጣውን መርከብ ከመጠበቅ ይልቅ መርከቧ ወደምትመጣበት ወደብ መሄዱ ትክክለኛ ውሳኔ ነው።

ደስ ያለችህ... የወደድካት ልጅ ቀጥለው ከተዘረዘሩት ምልክቶች መካከል አብዛኞቹን ካሳየችህ ፍላጎት የላትም ማለት ነው። ጊዜህን ሳታባክን ሌላ የምትሆንህን ቆንጆ ፍለጋ ጀምር።



Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

፩...ካላስታወሰችህ

- የሆነ ጊዜ የሆነ ቦታ ላይ ተዋውቃችሁ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስታገኛት ስምህን ከረሳችው አንተ ላይ ፍላጎት እንደሌላት የሚያሳይ ምልክት ነው። ስምህ አበበ ሆኖ እያለ በቀለ እያለች ከጠራችህም እንደዛው። ምክንያቱም ስምህን እንኳን አጥርታ ለማወቅ ያልፈለገች ልጅ አንተን ትፈልጋለች ተብሎ አይታሰብም። ስምህን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው አንተን ካላስታወሰችህ ደግሞ ያለ ጥርጥር ምንም ዓይነት ስሜት አልፈጠርክባትም ማለት ነው።

፪... ካልመለሰችልህ

- ከአንድም ሁለት ጊዜ ስልክ ደውለህላት፣ ቴክስት አድርገህላት ፣ ፌስቡክ ላይ ኢንቦክስ አድርገህላት (መልዕክት ፅፈህላት)፣ ኢ-ሜይል አድርገህላት...መልስ ካልሰጠችህ መልዕክቱ ግልፅ ነው። ፍላጎት የላትም።

፫... በደንብ የማታወራህ ከሆነ

- ከምትወዳት ልጅ ጋር ስትገናኝ ጥያቄዎች እያቀረብክ እሷ እንድታወራ በማድረግ ሁለመናህን ጆሮ አድርገህ እንድታዳምጥ ነው የሚመከረው። አንተም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ እረፍ አረፍ ጥያቄዎች እየጠየቅክ ለማዳመጥ የመስማት የስሜት ህዋስህን ዘርግተህ ስትጠብቅ አጫጭር መልስ እየሰጠች ዝም የምትል ከሆነ ችግር አለ። ለጥያቄዎችህ አጫጭር መልስ ከመስጠት በተጨማሪ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጨዋታውን ለማራዘም ምንም አስተዋፅኦ የማታደርግ ከሆነ ኤርፖርት ላይ መርከብ እየጠበቅክ መሆንህን አውቀህ ኤርፖርቱን ለቀህ ወደ ወደብ ተንቀሳቀስ።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

፬... ድንገት እቸኩላለሁ ካለችህ

- ካፌ ውስጥ ጭማቂ እየጠጣች አግኝተሃት ደስ ብሎህ አብረሃት ቁጭ ብለህ ጨዋታ ስትጀምር ጭማቂዋን ግማሽ ሳታደርሰው ድንገት እቸኩላለሁ ብላህ ተነስታ ከሄደች እርምህን አውጣ። እኔ ባንተ ቦታ ብሆን ለማስተዛዘኛ ትታው የሄደችውን ጭማቂ በአንድ ትንፋሽ እጨልጠዋለሁ።

፭... የማያሳምን ምክንያት የምትሰጥህ ከሆነ

- ልታገኝት... ልትጋብዛት ፈልገህ ስትጠይቃት የማያሳምን ምክንያት ነግራ እንደማይመቻት የምትነግርህ ከሆነ ፍላጎት የላትም። በከፍተኛ ጉጉት የሚጠበቅ ፊልም ሲመረቅ ልትጋብዛት ፈልገህ ጥያቄ ስታቀርብላት ‹ብጣም ደስ ይለኝ ነበር፤ ግን ዛሬ ማታ አባዬ ቀዶ ህክምና ስለሚያደርግ ከእሱ ጋር መሆን አለብኝ› የሚል ዓይነት ምክንያት ልትነግርህ ሲገባት... ‹አይመቸኝም! ብዙ የሚታጠብ ሳህንና ድስት አለኝ› የሚል ዓይነት ምክንያት ከሰጠችህ... ካንተ ጋር አዲስ ፊልም ከማየት ይልቅ ቆሻሻ ሳህንና ድስት ማጠብ መርጣለች። ስለዚህ ‹አዲዮስ አሚጎ› ልትላት ይገባል።

፮... የምትደበቅ ከሆነ

- መንገድ ላይ ስታይህ መንገድ የምትቀይር... ከዛም አልፎ ለመደበቅ የምትሞክር ከሆነ ሁለተኛ እንዳታስባት እዛው ለራስህ ቃል ግባ። ይህንን ነጥብ ከዚህ በላይ እንዳብራራልህ እንደማትጠብቅ ተስፋ አደርጋለሁ።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

## ፮... ሌሎች ምክንያቶች

- ብዙ ጊዜ ልታገኛት ስትፈልግ ‹ቢዚ› ነኝ የሚል ምላሽ የምትሰጥህ ከሆነ፤ ስልክ ስትደውልላት ‹አሁን ማውራት አልችልም› እያለች የምታሳጥርብህ ከሆነ፤ በጨዋታችሁ መሃል በተደጋጋሚ ስለሌሎች ወንዶች የምታነሳብህ ከሆነ፤ ከሌሎች ሴት ጓደኞችዋ ጋር ልታያይዝህ የምትጥር ከሆነ፤ ፍቅረኛ የመያዝ ፍላጎት እንደሌላት ከነገረችህ... ካንተ ጋር የፍቅር ግንኙነት የመጀመር ምንም ዓይነት ፍላጎት እንደሌላት የሚያሳዩ ምክንያቶች ናቸው።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## የመጀመሪያው የስልክ ጥሪ

ስልክ ቁጥር ስጠችህ ማለት ሁሉም ነገር አከተመ… ያንተ ሆነች ማለት አይደለም። ስልክ ቁጥሯን ሰጠችህ ማለት ካንተ ጋር የማውራት ፍላጎት አላት ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት ተግባብታችሁ በፍቅር ረዥም ርቀት ተጉዛችሁ የመጋባትና ቤተሰብ የመመስረት ዕድል አላችሁ።

የዛን ያህል ግንኙነቱ ገና በመጀመሪያው የስልክ ጥሪ የመቀጨት አደጋም ሊያጋጥመው ይችላል። ለሁለቱም ውጤቶች ወሳኝ ሚና የምትጫወተው ግን አንተ ነህ። ወንዶች የስልክ ላይ ጨዋታውን አሳምረን ግንኙነቱን ልናስቀጥለው የመቻላችንን ያህል አኮላሽተን የማስቀረት ብቃትም አለን። ጎበዞች ነን።

የእኔ ፍላጎት ተሳክቶልህ ሰብለ ወንጌልና በዛብህ(ሮሚዮና ጁሌት) እንድትሆኑ ነው። ያ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የመጀመሪያውን የስልክ ጥሪ በጥበብ ማከናወን ስትችል ነው።

**ራስህን ለማጥፋት አትቸኩል**

- አንዳንድ ወንዶች ስልክ ቁጥር የመቀበል ሂደቱን በትክክል ካሳኩ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

በኋላ ራሳቸውን ለማጥፋት ይጣደፋሉ። ስልክ ቁጥሩን ተቀብለው ከልጅቷ ትንሽ ሄድ ብለው ይደውሉና… ‹ሃይ አሁን የተዋወቅኩሽ ልጅ ነኝ… ስልኩ ያንቺ መሆኑን ለማረጋገጥ ብዬ ነው…› የሚል ዓይነት አስቀያሚ ዲስኩር ያደርጉና ፍላጎትዋን ይገድሉታል። ከዛ በኋላ ሲደውሉ ስልካቸው አይነሳም። አጥፍቶ መጥፋት ማለት ይሄ ነው።

ከእነዚህ አጥፍቶ ጠፊዎች መማር ያለብህ ሌላ ነገርም አለ… ‹ስልኳን ሰጥታኛለች› በሚል ቶሎ ቶሎ እየደወሉ አለማሰልቸት… ‹ድምፅሽ በጣም ያምራል› በሚል አሰልቺ አድናቆት ስልኩ ላይ አለመተኛት… የመሳሰሉትን ለአጥፍቶ መጥፋት የሚዳርጉ ስህተቶችን ከመፈፀም መጠንቀቅ አለብህ።

- ሴቶች ከሚወዱዋቸው ሚልዮን ነገሮች መካከል አንዱ በጉጉት መጠበቅን ነው። አለመታደል ሆኖ እኛ ወንዶች ደግሞ መቸኮል እንወዳለን። ስልክ ቁጥር ስንቀበል እጃችንን ይበላናል… ደውል ደውል የሚል ስሜት አንቆ ይይዘናል። ስልክ ቁጥር ተቀብለን 24 ሰዓት እንኳን መቆየት አንችልም። ደውለን ያንን ሴቶች በጉጉት ጠብቀው የማግኘት ደስታቸውን በአጭሩ እንቀጨዋለን። ለዚህ ነው ይህንን ‹ደውል ደውል› የሚለውን የሚገፋፋ ስሜት ተቋቁመው የሚቆዩ ወንዶች ስኬታማ የሚሆኑት። ስለዚህ ስልክ ቁጥሯን ከሰጠችህ በኋላ በጉጉት የምትጠብቅበትን አንድ ሁለት ቀን ስጣት።

## ደውለህ ምን ማለት አለብህ?

- ለመደወል ብቻ ሳይሆን ደውለህ ለምትናገረው ነገርም ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። በመጀመሪያው የስልክ ጥሪ ወደ ተንዛዛ ጨዋታ መግባት የለብህም። ሁልጊዜ ያለመሰልቸት ምርጫህ ይሁን።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

የማውራት፤ አብሮ የመቆየት ፍላጎት እያላት ወሬውን መቋጨት... መስነባበት ሌላ ጊዜ ልታወራህ... ልታገኝህ እንድትጓጓ ያደርጋታል። ይዘህ የማትለቅ... ወሬ ከጀመርክ የማትቆርጥ ከሆንክ ግን ስልክህን ለማንሳትም ሆነ በአካል ለመገናኘት ፍላጎት አይኖራትም። ቀላልና ግልፅ ስሌት ነው።

- ስለዚህ በመጀመሪያው የስልክ ጥሪ ማድፈግ የሚጠበቅብህ በግልፅ ቋንቋ ራስህን ማስተዋወቅ... መቼና የት እንደተገናኛችሁ... ከዛ ቀለልና አጠር ያለ... ቀልድ አዘል ቆይታ በማድረግ በቀጣይነት የመደዋወል ሁኔታ ክፍት አድርገህ ስልኩን መዝጋት።

  እዚህ ላይ የምትደውልበት ሰዓትም ወሳኝነት አለው። በስራ ሰዓት ከደወልክላት ተረጋግታ ላታናግርህ ትችላለች። ከስራ ሰዓት ውጪ... በተለይ ምሽት ቢሆን ይመረጣል። በጣም ሳይመሽ... ከ12 ሰዓት እስከ 2 ሰዓት ባለው ጊዜ ማለቱ ነው። በዚህ ሰዓት ተረጋግታ ታናግርሃለች፤ በዛ ላይ ምሽት ሲሆን ለስለስ ያሉ ስሜት ነክ ቃላት ለመጠቀምና ጨዋታውን ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ፍቅር ወሬ ለማሳደግ ዕድል ይከፍታል።

### መልመጃ አንድ፡ ማታ፡ የመጀመሪያው የስልክ ጥሪ

**አንተ**

(ስልኩ ብዙ ከጠራ በኋላ ከሆነ የምታነሳው)

‹ሃይ ሰብለ... ተኝተሻል እንዴ?›

**እሷ**

‹አዎ ትንሽ ሸለብ አድርጎኝ ነበር›

**አንተ**

‹በህልምሽ እኔን ለማየት ነው መቼም እንዲህ በጊዜ የምትተኚው... ሳቅ›

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

**እሷ**

‹ኧረ ባክህ... ማን ልበል?›

**አንተ**

‹በዛብህ ነኝ... ባለፈው ማፌ ሞል ተዋውቀን ነበር›

**እሷ**

‹ሂይ... አዎ አስታወስኩህ... ደህና ነህ?›

**አንተ**

‹አንቺ አለመደወል በስተቀር ደህና ነኝ›

**እሷ**

‹እንዴ! ስልክ ቁጥርህን እኮ አልሰጠኸኝም ነበር›

**አንተ**

‹እኔማ ከቴሌ ጠይቀሽ ትደውይልኛለሽ ብዬ ነበር...›

**እሷ**

‹ሳቅ... ኧረ ባክህ... ቀልደኛ ነህ›

**አንተ**

‹ሰብሊ ድምፄን ስላሰማሁሽ ብቻ ሳይሆን ድምፅሽን ስለሰማሁትም

በጣም ደስ ብሎኛል... እንደዋወልና እንገናኛለን›

**እሷ**

(በስሱ እየሳቀች)

‹ብል እሺ አትጥፋ›

**አንተ**

‹ቻው›

ስልኩን ጥርቅም!

**መልመጃ ሁለት፡ ማታ፡ የመጀመሪያው የስልክ ጥሪ**

**አንተ**

(ስልኩ ብዙ ሳይጠራ ካነሳችው)

‹በከፍተኛ ጉጉት እየጠበቅሺኝ ነበር ማለት ነው›

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

**እሷ**

‹አቤት?›

**አንተ**

‹ስልኩ ሳይጠራ ብድግ አደረግሺው›

**እሷ**

‹ደጅ መጥናት የምትወድ ከሆነ ዝጋውና ደግመህ ደውላ›

**አንተ**

‹ስልክ ተቀብለህ ቶሎ አይደወልም የሚባለውን ለማክበር ብዬ ድምፅሽን ሳልሰማ እስካሁን የቆየሁት ደብቃኛል›

**እሷ**

‹ማን ልበል?›

**አንተ**

‹በዛብህ ነኝ… ባለፈው ካልዲስ ስልክ ቁጥርሽን የተቀበልኩሽ›

**እሷ**

‹ኦ… አስታወስኩህ… ደህና ነህ?›

**አንተ**

‹አሁን ድምፅሽን ስለሰማሁ የበለጠ ደህና እሆናለሁ… ሳቅ›

**እሷ**

‹ድምፄ መድሃኒት ከሆነህ ጥሩ›

**አንተ**

‹እንዲያውም አንድ አሪፍ ሃሳብ መጣልኝ…›

**እሷ**

‹ምን?›

**አንተ**

‹ድምፅሽን በብልቃጥ እያሸግን ቸብችበን ሚልዬነሮች እንሆናለን›

**እሷ**

‹ሳቅ›

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

**አንተ**

‹ሰብለ. ብዙ ባወራሽ ደስ ይለኛ ነበር፤ ነገር ግን ወደ አንድ ቦታ እየገባሁ ነው... እደውላለሁ›

**እሷ**

‹ብል እሺ. አትጥፋ›

## የመጀመሪያው የስልክ ጥሪ ማጠቃለያ

አጭር... ያልተንዛዛ ቀለል ያለ ጨዋታ፡፡ እንደ ብዙ ወንዶች ስልኩ ላይ ሙጭጭ አለማለትህ ብዙ ጥቅም አለው፡፡ በመጀመሪያው ቀን የወሬ እጥረት አያጋጥምህም፡፡ አትሰለችም፡፡ የሴት ድምፅ ሰምቶ እንደማያውቅ ሰው ‹ባሬ ነው ያገኘሁት፤ አለቅም› የሚል ዓይነት ስሜት አታንፀባርቅም፡፡ የመለማመጥ ዓይነት ሁኔታ አይነበብብህም፡፡ በዚህ ሁኔታ ጨዋታው እየጣፈጣት እያለ የስልኩን ወሬ ራስህ ማሳጠርህ በጣም ትላልቅ ነጥቦች ያስመዘግብልሃል፡፡ ሌላ ቀን እንድትደውልላት ከፍተኛ ፍላጎት እንዲኖራት ያደርጋል፡፡

ለመገናኘት ቀጠሮ ከመጠየቅህ በፊት በዚህ ሁኔታ አንድ ሁለት ጊዜ አናግራት፡፡ የእንገናኝ ጥያቄ ለማቅረብ አለመጣደፍህ ጥሩ ነጥብ የሚያስጥህ ከመሆኑ በተጨማሪ ‹መቼ ነው እንገናኝ የማትለኝ?› የሚል ጉጉትም ይፈጥርባታል፡፡ ሴቶች ጉጉት እንደሚወዱ ደግሞ ተነጋግረናል... ተግባብተናል፡፡

ወደ የመጀመሪያው መገናኘት ከመሻገራችን በፊት አንድ ተጨማሪ ነጥብ... በስልክም ሆነ በቴክስት ብዙ አታውራት፡፡ በስልክና በቴክስት ጨዋታውን ከጨረስከው የመገናኘት ፍላጎትዋ ሊሞት ይችላል፡፡

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



# የመጀመሪያው መገናኘት

የመጀመሪያውን ቀጠሮ የምታስይዘው በስልክ ነው። ከላይ እንደገለፅኩት ደጋግመህ እየደወልክ በተንዛዛ ወሬ ካላሰለቸሃት ‹እንገናኝ› የሚለውን ጥያቄ በጉጉት መጠበቋ አይቀርም። የመገናኘት ፍላጎት ይኖራታል።

የመጀመሪያውን ቀጠሮ ለማስያዝ ከመደወልህ በፊት ግን መቼና የት ልታገኛት እንደምትፈልግ አስቀድመህ ወስን። ደውለህ የእንገናኝ ጥያቄ ካቀረብክ በኋላ ‹እሺ. መቼና የት?› ስትልህ ‹እኔንጃ ደስ ያለሽ ቀንና ቦታ› ብለህ ከተንተባተብክ ነጥብ ይቀነስብሃል። ሴቶች መወሰን የሚችልና አስቀድሞ የሚያቅድ ወንድ ይወዳሉ… ያደንቃሉ።

የመጀመሪያውን ቀጠሮ ለማስያዝ ስትደውል ጉዳዩን በጣም አታክብደው… ቢቻል እንደ እግረ መንገድ አስመስለህ…

‹ሄይ ሰብሊ… አዲስ አበባ ውስጥ ቁጥር 1 ማኪያቶ ያለበት ቦታ አውቃለሁ… ከሐሙስ ወይም ከቅዳሜ የትኛው ይመችሻል?›…

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

በማለት ጠይቃት፡፡ ሁለት ቀን ለአማራጭ ማቅረብህ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዱ ቀን ወጉ እንዳይቀር የምትግደረደርበት ሲሆን ሁለተኛው ቀን የምትመጣበት ነው፡፡ አንዱን ቀን መርጣ ‹እሺ› ስትልህ የምትገናኙበትን ቦታና ሰዓት ነግረህ ተሰናበታት፡፡ ስልኩ ላይ ብዙ በቆየህ ቁጥር ሃሳቧን የመቀየር አጋጣሚ ልትፈጥር ትችላለህ፡፡ ስልኩን ቶሎ ስትዘጋው የመገናኘት ጉጉቷ ይጨምራል፡፡

## ማስጠንቀቂያ

- ቀጠሮ ይዛችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ… ጥቂት ሰዓታት ወይም ደቂቃዎች ሲቀሩት ደውላ ወይም ቴክስት አድርጋ ቀጠሮውን ልትሰርዘው ትችላለች፡፡ የምትሰርዘው የምር ከአቅሟ በላይ በሆነ ምክንያት አሊያም እንዲሁ ልትፈትንህ ሊሆን ይችላል፡፡ ለመገናኘት ከፍተኛ ጉጉት ስለሚኖርህ ድንገት ስትሰርዝብህ ልታብድ ትችላለህ፡፡ በስልክ ከነገረችህ ስሜትህን ተቆጣጥረህ… ንዴትህንና ጉጉትህን ዋጥ አድርገህ… ‹ምንም ችግር የለም፤ ሌላ ቀን እንገናኛለን› ልትላት ይገባል፡፡

ቀጠሮውን ለመሰረዝዋ ያቀረበችው ምክንያት ‹ችግር ገጥሞኝ ነው› ብላ ከሆነ ለቀጠሮው መሰረዝ ምንም ቦታ ሳትሰጥ ‹የማግዝሽ ነገር አለ?› የሚል ዓይነት ጥያቄ አቅርብላት፡፡ ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ ደግሞ እንዴት እንደሆነች ጠይቃት፡፡ በዚህ ሰዓት በጣም ችግሩ እንደተፈታ… ሰላም እንደሆነች ብትነግርህ እንኳን ስለ ቀጠሮው በፍፁም እንዳታነሳ፡፡

የደወልከው ‹እንዴት ሆንሽ?› ለማለት ብቻ ነው፡፡ ጥያቄው ከራሷ ከመጣ እሰየው ነው፡፡ ካልመጣ ደግሞ ‹ብቃ እንዴት ሆንሽ ልልሽ ነው የደወልኩት… ሁሉም ነገር ሰላም በመሆኑ ደስ ብሎኛል› ብለህ ስልኩን ዝጋው፡፡

በሁለት ምክንያቶች በጣም ዳጎስ ያለ ነጥብ ታገኝበታለህ፤

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

አንደኛ... በቀጠሮው መሰረዝ አልተናደድክም... ለመገናኘት አልተስገበገብክም። ሁለተኛ... በችግሯ ሰዓት ከጎኗ መሆንህን አረጋግጠሃል።

## ለመጀመሪያ ጊዜ ስትገናኙ

- የሚያምርብህንና ምቾት የሚሰጥህን አለባበስ ልበስ (ስራ ለመቀጠር ቃለ ምልልስ ለማድረግ ስትሄድ የምትለብሰው ዓይነት አለባበስ እንዳትለብስ... ሙሉ ልብስና ከረቫት ማለቴ ነው)
- በዚህ ቀን እጅግ በጣም አሪፉ ራስህን ይዘህ ነው እሷን ማግኘት ያለብህ። አሪፍ አለባበስ፣ አሪፍ ባህሪ፣ አሪፍ ጨዋታ፣ አሪፍ ጠረን... ከምንጊዜም የበለጠ በሁሉም ነገር አሪፍ መሆን አለብህ። ‹ሌላ ጊዜ የማልደግመው ነገር በኋላ አደጋ አያመጣብኝም... አስመሳይ አልባልም?› የሚል ጥያቄ ከመጣብህ... መልሱን ልስጥህ... በተቻለ መጠን ሁሌም እንደዛ ዓይነት እጅግ በጣም አሪፍ ስብዕና እንዲኖርህ ጥረት አድርግ። ይቻላል። ‹አስመሳይ!› የሚያስብልህ ነገር እሷን ለመማረክ ብለህ የማታምንበትን ነገር ስታደርግ ብቻ ነው። እሷን ለመማረክ ብለህ የሌለህን እንዳለህ ስታወራ... እሷን ለመማረክ ብለህ ማንነትህን ስትቀይር... በአጠቃላይ በማትስማማባቸው ወሳኝ ነገሮች ስትስማማ ነው። ስለዚህ እሷን ለመማረክ ብለህ እሷ በምትለው ነገር ሁሉ መስማማት የለብህም። በአክብሮት ልዩነትህን መግለፅ ትችላለህ። እንዳውም የምትማርካት ትክክለኛውን እምነትህንና ስሜትህን በመግለፅ ነው።

እናም ስቲም ገብተህም ይሁን የፀጉር ቤት ሳሎን በጣም ፀዳ፣ ዘንጥ፣ ፈካና ዘና ብለህ ተገኝ። ሁልጊዜ እንደዛ መሆን ከቻልክ አሪፍ ነው። ካልቻልክ ብዙ አትጨነቅ። ንፁህና የሚያምርብህን ልብስ ለብሰህ በመልካም መዓዛ በተዝናና እና በአሪፍ መንፈስ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ከተገኘህ በቂ ነው። ሴቶች በመጀመሪያው ቀን ለእነሱ ብለን ተጨማሪ ጥረት አድርገን በቀጠር ቦታ እንደምንገኝ ይገባቸዋል። ይወዱታል። የማይወዱት ነገር ‹ሁልጊዜ እንደምሆነው ሆኜ ነው የምሄደው... ካሁኑ ትልመደው› በሚል ምንም ዓይነት ጥረት ሳናደርግ ስንቀር ነው።

ስለዚህ በመጀመሪያው ቀን የቻልከውን ነገር ሁሉ አድርገህ እጅግ አሪፉ ራስህን ይዘህላት ሂድ። ሴቶች ፌስቡክ ላይ ፎቶግራፎቻቸውን በፎቶሾፕ ያስማምሩት የለ እንዴ? ...እንደዛ ማለት ነው። በፎቶሾፕ ያበደ ፎቶዋን አይተን... ተማርከን ያገኘናት ሴት በአካል ያለ ፎቶሾፕ ስትመጣ ‹ፌስቡክ ላይ ያየሁት ውበት ይሄ ብቻ አልነበረም!› ብለን ጥለን እንሄዳለን እንዴ? አንሄድም። በጣም የተጋነነ ልዩነት ካላሳየ በስተቀር ያለ ፎቶሾፕ የመጣውን እሷነቷን እንቀበላለን። ያንተም ሁኔታ ከመጀመሪያው መገናኘት (ቀጠሮ) በኋላ ትንሽ ግሸበት ካሳየ እንደዛው ነው። በጣም የተጋነነ ግሸበት ካላሳየ በስተቀር ትቀበለዋለች። ወደ ሌሎች ነጥቦች እንለፍ...

- ★ በቀጠሮው ቦታ ቀድመህ ተገኝ
- ★ ፍቅረኛሞች ወደሚተሻሹበት... የሚሳሳሙበት ዓይነት ቦታ አትውሰዳት
- ★ የቦታ ምርጫህ ጨለማ የሚበዛበትና ጭር ያለ አይሁን
- ★ በርካታ ሰዎች ወዳሉበት ግልፅና የማያስፈራ ቦታ ውሰዳት
- ★ ገና ለመተዋወቅ የቀጠርካት እንጂ የፍቅር ጓደኛህ አለመሆኗን አስታውስ
- ★ አላስፈላጊ የመነካካትና የመጠጋጋት ሁኔታ እንዳትፈጥር ተጠንቀቅ
- ★ በቦታ ምርጫህ፣ በስርዓትህና በጨዋታህ ፍፁም ምቾት እንዲሰማት አድርግ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM



## የጨዋታ ርእሶች

★ በመጀመሪያው ቀን ስለ ራስህ የጠለቀ መረጃ ከመዘርዘር ተጠንቀቅ

★ የእሷንም ዝርዝር መረጃዎች ለማወቅ አጥብቀህ አትጠይቅ

★ ማናቸውም ክርክር የሚፈጥሩ እንደ ሃይማኖት፣ ፖለቲካና ዘር የመሳሰሉ ርእሶችን ከማንሳት ተቆጠብ

★ እንደ ዝንባሌ፣ ሙዚቃ፣ ፊልም፣ ጉብኝትና ራዕይ በመሳሰሉ ርእሶች ዙሪያ አተኩር

★ በተቻለ መጠን ቀለል ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን እያነሳህ እንድታወራ አበረታታት

★ አስተናጋጆችን ስታዝ ስርዓትና ትህትና ይኑርህ... ለሰዎች ያለህ አክብሮትም ጭምር መጨረሻ ላይ ታርሞ ነጥብ ይሰጥበታል

★ ከተገናኘህበት ቅፅበት አንስቶ ሙሉ ትኩረትህን እሷ ላይ አድርግ። ከሌሎች ሰዎች ጋር ቴክስት መደራረግ፣ የፌስቡክና የትዊተር ገፆችህን መግለጥ፣ ወይም መደዋወል ፍፁም የማይመከሩ ነገሮች ናቸው። ለአደጋ ጊዜ የምትፈለግ ሃኪም፣ ወታደር፣ ፖሊስ፣ የእሳት አደጋ ሰራተኛ ካልሆንክ በስተቀር ስልኩን አጥፍተህ ብትገላገል አሪፍ ነው።

★ ስለ ወሲብ... ስለ ቀድሞ የፍቅር ህይወትህ ፈፅሞ እንዳታነሳ፣ የእሷንም አትጠይቃት

★ ዘና ብለህ ተጫወት... በራስ መተማመን ይኑርህ... አትሽቆጥቆጥ... አትደናገጥ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## አድምጥ... አድምጥ አሁንም አድምጥ!

‹ሴቶች ዝምተኛ ወንዶችን ይወዳሉ።
ምክንያቱ ደግሞ የሚያደምጡዋቸው ስለሚመስላቸው ነው›

ማርሴል አቻርድ

ማድመጥ ብዙ ነጥብ የሚያሰጥ ትልቅ ጥበብ ነው። የብዙ ወንዶች መሰረታዊ ችግር ከማድመጥ ይልቅ ብዙ ነገር በመቀባጠር ለመማረክ የሚደረግ የተሳሳተ ሙከራ ነው።

ያለህንና የሌለህን በመቀባጠር ለመማረክ ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ ይልቅ አረፍ አረፍ ጥያቄዎችን እያነሳህ ከልብ ማድመጥ በሴቶች ዓለም ከፍተኛ አድናቆት የሚቸረው ብዙ የማይገኝ የወንዶች ችሎታ ነው። ከልብ አድምጠህ ከምትናገራቸው ነገሮች ውስጥ ጥያቄ እየመዘዝክ ለተጨማሪ ማብራሪያ ከጋበዝካት... የማብራራት ችሎታዋን ካደነቅካት ... በእርግጠኝነት ለሁለተኛ ቀጠሮ ታልፋለህ።

ከአፏ ቃላት እየነጠቅክ የራስህን ድምፅ ብቻ የምታደምጥ ከሆነ ግን አይደለም ሁለተኛ ቀጠሮ ልታገኝ ቀርቶ የመጀመሪያው ቀጠሮም ራሱ ድንገት በአጭር ሊቀጭ ይችላል።

## የመጀመሪያው ቀጠሮ ሁለተኛ ቀጠሮ ይወልዳል?

ከብዙ ችግሮቻችን መካከል አንዱ በጥቃቅን ስኬቶች ትላልቅ የደስታ ድግሶች መደገሳችን ነው። ቆንጆ ሴት ፈገግ ካለችልን ጓደኞቻችን... የስራ ባልደረቦቻችን ግራ እስኪጋቡ ድረስ ሳምንት እንፍለቀለቃለን። ስልክ ቁጥር ሲሰጡን ሰበር ዜና ነው። የቀጠርናት ሴት ስትመጣማ... በቃ አለቀ ደቀቀ። እሷን ብቻ አይደለም ዓለምን የጨበጥን ይመስለናል። ይህ ሁኔታችን ደግሞ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሴቶቹን ያቅለሸልሻቸዋል... ያሸሻቸዋል።

ስለዚህ ሲወርድ ሲዋረድ ወንድሞችህ የፈፀምነውን ዓይነት ስህተት እንዳትፈፅም። በመጀመሪያው ቀጠሮ መጣች ማለት የፍቅር ጓደኛህ ሆነች ማለት አይደለም። ነገር ግን ከላይ በተዘረዘረው ዓይነት በመጀመሪያው ቀጠሮ መደረግ ያለባቸውን ብቻ በትክክል ካደረግክ ወደፊት የፍቅር ጓደኛህ የማድረግ ዕድል አለህ። ስለሆነም በዚህ በመጀመሪያው ቀጠሮ ላይ ማተኮር ያለብህ ቀለልና ዘና ያለ የትውውቅ ጊዜ አሳልፋችሁ ሌላ ቀጠሮ እንዲወልድ ማድረጉ ላይ ነው።

ለመሄድ ካልተጣደፈች፣ ጨዋታው ላይ ከተሳተፈች፣ በምትቀልዳቸው ቀልዶች ከሳቀች፣ ሰዓቷን ቶሎ ቶሎ ካልተመለከተች፣ አንተን ቁጭ አድርጋ ጓደኞችዋ ጋር እየደወለች ወሬ ካላንዛዛች... እንኳን ደስ አለህ፤ የመጀመሪያው ቀጠሮ ተሳክቷል። ይህ ማለት ደግሞ በሁለተኛ ቀጠሮ የመገናኘት ዕድላችሁ ሰፊ ነው ማለት ነው።

## የመጀመሪያው መገናኘት አሪፍ አጨራረስ

መገናኘቱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ አሪፍና ጣፋጭ የማድረግ ሃላፊነት ያንተ (የኛ) ነው። ምክንያቱም ሴቶች በቀጠሮው ለመገኘት ብዙ ጥረት አድርገው ነው የሚመጡት። ፀጉር መሰራት... የእግርና የእጅ ጥፍር ማስዋብ፣ ልብስ መምረጥ፣ ማራኪ ሽቶ ማርከፍከፍ... ብዙ ጣጣ አለባቸው። ያንን ሁሉ የሚያደርጉት ለእኛ ነው። ስለዚህ እኛ ደግሞ ጥሩ ጊዜ እንዲያሳልፉ የተቻለንን ያህል ጥረት ማድረግ አለብን። ስለዚህ ከተገናኛችሁበት ቅፅበት አንስቶ ለመለያየት እስከደረሳችሁበት ደቂቃ ድረስ አሪፍ ጊዜ እንዲኖራትና ሌላ ቀንም ለመገናኘት እንድትመኝ አድርገሃታል

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ብዬ ሳስብና ቆይታውን ለመደምደም ልታደርጋቸው የሚገቡ ጥቂት ነገሮች ልንገርህ...

★ ስለ ቀጣይ ቀጠሮ አታንሳ... ‹እንገናኝ ይሆን?› የሚል ጉጉት እንዲኖራት ያደርጋል። (ሴቶች ጉጉት ይወዳሉ... እቺን ነገር አትርሳ)

★ ለመሰነባበት ሆድህ ባር ባር አይበለው... ሙጥኝ አትበል... የመሄድን ሃሳብ አንተ ቀድመህ አንሳ

★ ‹እንዴት አገኘሺኝ?... ወደድሺኝ?› ዓይነት ነገር አይደለም ለመናገር ጭራሽ እንዳታስብ... የምታስብ ከሆነ ማሰብ ያለብህ ‹ከእኔ ጋር እንዲህ ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ አግኝታው ነው እንዴ?› የሚል መሆን አለበት። ግን ይሄም ከአፍ የሚወጣ አይደለም። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገብቶሃል ብዬ አስባለሁ... ልበ ሙሉ ሁን።

★ በቀጠሮው ቦታና ሰዓት መምጣቷ: በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንጂ ላንተ ውለታ ልትውልልህ አይደለም። ስለዚህ ምስጋና... ጎንበስ ቀና አታብዛ፡ ‹ስለተገናኘን በጣም ደስ ብሎኛል› ብለህ ተሰናበታት። በቃ።

★ ከተለያያችሁ በኋላ... የዛኑ ቀን አትደውል። አብራችሁ በሳሳለፋችሁት ጊዜ እያመላለሰች እንድታስብና እንድትናፍቃት ጊዜ ስጣት። ...ገብቶኛል ‹በሰላም መግባትና አለመግባቷን ደውዬ መጠየቅ አለብኝ› ልትል ነው። እቺ ልጅ ሳለፉት በርካታ ዓመታት እየወጣች እየገባች በሰላም ኖራለች... አንተ ጠብቀሃት፤ ግን አይደለም (ለአቅመ ሄዋን ስለደረሰች ልጅ ነው እያወራን ያለነው)።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

# ቀጣይ ግንኙነቱን በላላ ዘዴ ማጥበቅ

"ፍቅር በሁለት አካላት ውስጥ የሚኖር
የአንድ መንፈስ ትንብር ነው"

አሪስቶትል

ከብዙ ስህተቶች ተቆጥበህ እዚህ ደረጃ በመድረስህ እንኳን ደስ አለህ... እዚህ ደረጃ መድረስ የብዙ ወንድሞችህ ህልም ነው፡፡ ነገር ግን ለዚህ ደረጃ የሚበቁት በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ጉዞው ገና ይቀጥላል፡፡ ቀጣዩ ጉዞ ስኬታማ እንዲሆን ደግሞ ተጨማሪ ስንቅና ትጥቅ ያስፈልግሃል፡፡ ለስንቁና ትጥቁ አታስብ... ካንተ የሚጠበቀው ዝግጁነት ብቻ ነው፡፡ እንቀጥል...

ልብ በል በመጀመሪያው ቀጠሮ መጣች... ጥሩ ጊዜ አሳለፋችሁ... ማለት ሁሉም ነገር ተጠናቀቀ... ጓደኛህ ሆነች ማለት ግን አይደለም፡፡ ስለዚህ እንዳትቃዥ... በነጋታው ወደ ተለመደው ህይወትህ ተመለስ፡፡

ሌላ ማወቅ ያለብህ ነገር ሴቶች በራሱ የቆመ... ጊዜውን ለስኬት በአግባቡ የሚጠቀም ወንድ ይወዳሉ... ያደንቃሉ፡፡ ቢዚ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ሆኑብኝ ለሚል እንደ አማራጭ 24 ሰዓት ይያዝለት፡፡ አሁን ጥያቄው 24 ሰዓት ላይ ፆሙን የሚያፈርስ ሰው ምን ማድረግ አለበት የሚል ነው… መልሱም ‹ቴክስት› ነው፡፡

በመጀመሪያው ቀጠሮ ካገኘሃት በኋላ ለ48 ሰዓታት ያህል ስለ እሷ ከማሰብ መፆም አቅቶህ በ24 ሰዓት ከተሸነፍክ… ቀለል ያለ ቴክስት አድርግላት…

‹ታዲያስ ሰብለ! ትላንት ስለተገናኘን ደስ ብሎኛል› አራት ነጥብ፡፡

በራሳቸው የሚተማመኑ አሪፍ ሴቶች ቶሎ ይመልሳሉ… ግን በጣም ብዙ አይደሉም፡፡ ቶሎ ከመለሱ የተዋረዱ የሚመስላቸው አሉ፡፡ ስለዚህ ቶሎ ካልመለሰችልህ እንዳትረበሽ፡፡

ዝም ብለህ ስታስበው የቀዶ ህክምና ሃኪም አሊያም ከጅቡቲ ኢትዮጵያ የምትመላለስ የከባድ መኪና ሾፌር ካልሆነች በስተቀር ቴክስት ደርሷት ምላሽ ለመስጠት አስር ሴኮንድ የምታጣ ሴት የለችም፡፡ አለመታደል ሆኖ ግን ብዙ ሰዓታት ያቆዩናል… ይቀጡናል፡፡ ሴቶች መንጓት ብቻ ሳይሆን ማንጓትም ይወዳሉ፡፡ ስለዚህ ለላክው ቴክስት መልስ ሳታገኝ ሰዓታት ቢያልፉ እንዳትሸበር

በፍፁም፤ በፍፁም፤ አሁንም እደግመዋለሁ በፍፁም መልስ ሳታገኝ ደግመህ ቴክስት እንዳታደርግ፡፡ እንዳትደውል፡፡ ሴቶች በተለያየ መንገድ የወንዱ ጥንካሬ ምን ያህል እንደሆነ ይፈትሻሉ… ይፈትናሉ፡፡ ፈተናውን የሚያልፉ ጠንካራ ወንዶች ይወደዳሉ፡፡ ፈተናውን እንዳትወድቅ፡፡

ፈተና ሲፈትኑህ ሆን ብለው … ‹ልፈትነው!› ብለው ሳይሆን ይችላል፡፡

ምክንያቱም ብዙ ጊዜ እንዲሁ በተፈጥሮ ሳያስቡት… ‹አጥኑ› ሳይሉን ከሚኒስትሪ እስከ ማትሪክ ድረስ የተለያዩ ፈተናዎች ይፈትኑናል፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ስለዚህ ‹ለምን ፈተንሽኝ?› ብለህ አታካራ እንዳትፈጥር።

ይህን በዚህ እንቋጨውና ለቴክስትህ መልስ ቴክስት ካደረገች ምን ማድረግ እንዳለብህ እንነጋገር…

**መልመጃ፡ ቀን/ማታ፡ የቴክስት መልዕክት**

**አንተ**

‹ታዲያስ ሰብለ! ትላንት ስለተገናኘን ደስ ብሎኛል›

- ሺ..ው! ተላከ።

የደቂቃ ርዝመት አሁን ነው የሚገባህ… አንድ ደቂቃ… አምስት ደቂቃ… አስር ደቂቃ… ሃያ ደቂቃ… ዲንዲን!… መልስ መጣ።

**እሷ**

**ሀ. ‹ሃይ በዛብህ! እኔም ደስ ብሎኛል›**

**ለ. ‹ሃይ በዛብህ! እኔም ደስ ብሎኛል… ደህና ነህ?›**

**ሐ. ‹አመሰግናለሁ›**

- ቆይ… ቆይ! ቴክስት ለማድረግ… አጥፍተህ ለመጥፋት አትቸኩል። ቴክስት በጎም ለአደጋ የሚያጋልጥ ተፈጥሮም አለው። ማስተላለፍ የፈለከውን ነገር አስበህ ለመላክ ዕድል ይሰጥሃል። በሌላ በኩል ደግሞ ድምፅህን ወይም ምስልህን ስለማያካትት ሰዎች በተሳሳተ መንገድ እንዲረዱህ በር ይከፍታል.. ሳትቆጣ እንደተቆጣህ አድርገው ሊወስዱት ይችላሉ።

ስለዚህ በዚህ ደረጃ… በደንብ አስክትተዋወቁ ድረስ ሁሉንም ነገር እያሰብክና እየተጠነቀቅክ ማድረግ ይኖርብሃል።

ቴክስት ከማድረግህ በፊት ምን መፃፍ እንዳለብህ አስብ። ከፃፍክ በኋላም በደንብ አንብበው… ለተሳሳተ መልዕክት ክፍተት የሚሰጥ ነገር ያለ መስሎ ሲሰማህ ኤዲት ማድረግ ይኖርብሃል። ሁሉንም

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ስለዚህ ‹ለምን ፈተንሽኝ?› ብለህ አታካራ እንዳትፈጥር።

ይህን በዚህ እንቋጨውና ለቴክስትህ መልስ ቴክስት ካደረገች ምን ማድረግ እንዳለብህ እንነጋገር...

**መልመጃ፡ ቀን/ማታ፡ የቴክስት መልዕክት**

**አንተ**

‹ታዲያስ ሰብለ! ትላንት ስለተገናኘን ደስ ብሎኛል›

- ሺ..ው! ተላከ።

የደቂቃ ርዝመት አሁን ነው የሚገባህ... አንድ ደቂቃ... አምስት ደቂቃ... አስር ደቂቃ... ሃያ ደቂቃ... ዲንዲን!... መልስ መጣ።

**እሷ**

**ሀ. ‹ሃይ በዛብህ! እኔም ደስ ብሎኛል›**

**ለ. ‹ሃይ በዛብህ! እኔም ደስ ብሎኛል... ደህና ነህ?›**

**ሐ. ‹አመሰግናለሁ›**

- ቆይ... ቆይ! ቴክስት ስማድረግ... አጥፍተህ ለመጥፋት አትቸኩል። ቴክስት በጎም ለአደጋ የሚያጋልጥ ተፈጥሮም አለው። ማስተላለፍ የፈለከውን ነገር አስበህ ለመላክ ዕድል ይሰጥሃል። በሌላ በኩል ደግሞ ድምፅህን ወይም ምስልህን ስለማያካትት ሰዎች በተሳሳተ መንገድ እንዲረዱህ በር ይከፍታል.. ሳትቆጣ እንደተቆጣህ አድርገው ሊወስዱት ይችላሉ።

ስለዚህ በዚህ ደረጃ... በደንብ እስክትተዋወቁ ድረስ ሁሉንም ነገር እያሰብክና እየተጠነቀቅክ ማድረግ ይኖርብሃል።

ቴክስት ከማድረግህ በፊት ምን መፃፍ እንዳለብህ አስብ። ከፃፍክ በኋላም በደንብ አንብበው... ለተሳሳተ መልዕክት ክፍተት የሚሰጥ ነገር ያለ መስሎ ሲሰማህ ኤዲት ማድረግ ይኖርብሃል። ሁሉንም

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

የምታስተውለው ግን ለተላከልህ ቴክስት ለመመለስ ከመቸኮል ስትቆጠብ ነው፡፡ በዚህ ከተግባባን አሁን ‹ሰብሉ› የላከችልህን ቴክስት በደንብ ሰባብረን እንመልከተው...

## ሀ. ‹ሃይ በዛብህ! እኔም ደስ ብሎኛል›

ብላ ከላከችልህ... ካስቻለህ ዝም በል፡፡ ሌላ ቴክስት አትላክ፡፡ ዝምታህ ሌላ ቴክስት እንድትልክ ሊያደርጋት ይችላል፡፡ ሳትመልስላት ሌላ ቴክስት ከላከች... እንዴ ብድግ ብለህ በደስታ መጮህ ትችላለህ... ከዛ የቴክስት ልውውጡም ሊቀጥል ይችላል... ግን አታርዝመው... የሆነ ምክንያት ፈጥረህ በጥሩ ቋንቋ... በትህትና ቋጨው፡፡

እሷም ሌላ ቴክስት ካልላከችና አንተም ዝም ማለት አላስችል ካለህ ‹እንደግመዋለን› በሚል አሪፍ ቃል የቴክስት ጨዋታውን ዝጋው፡፡ ያልተንዛዛ... ልብ አንጠልጣይ!

## ለ. ‹ሃይ በዛብህ! እኔም ደስ ብሎኛል... ደህና ነህ?›

ጥያቄ ያለው መልዕክት በጣም አሪፍ ነው፡፡ የማውራት ፍላጎት እንዳላት የሚገልፅ መልካም ዜና ነው፡፡ ስለዚህ ‹ደህና ነህ?› ለሚለው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ መስጠት ይጠበቅብሃል፡፡ ከመልሱ በተጨማሪ የቴክስት ተኩስ ልውውጡ ትንሽ እንዲቀጥል ማድረግም አለብህ፡፡ ከተለያያችሁ በኋላ ስላደረግከው አሪፍ ነገር በመጥቀስ ደህንነትህን ከገለፅክ በኋላ በእሷ በኩል ምን አዲስ ነገር እንዳለ በመጠየቅ ጨዋታው ማስቀጠል ትችላለህ፡፡

አንድ ማወቅ ያለብህ ነገር ግን ለማውራት ፍላጎት አሳይታለች ብለህ እስክትሰለችና ‹ስራ ፈት ነው እንዴ?› የሚል ጥያቄ እስኪፈጠርባት ድረስ ቴክስቱ ላይ አትወዘፍ፡፡ ጥቂትና አሪፍ የቴክስት ልውውጥ ካደረጋችሁ በኋላ በሚያምር አጨራረስ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

አሳርገው።

ቴክስት እየተደራረግክ የመቆየት ፍላጎትህን ገድበህ... ስሜትህን ተቆጣጥረህ ጨዋታው እየጣፈጣት... ሳትሰለች መቋጨትን የዘወትር ልማድ አድርገው።

## ሐ. ‹አመሰግናለሁ›

መልሷ ይሄ ብቻ ከሆነ የማውራት ፍላጎት የላትም ወይም ደግሞ ጥንካሬህን ልትፈትነው ነው። ስለዚህ መልስ አያስፈልገውም። ከዚህ በኋላ ይውሰህ ሁለተኛ ቀጠሮ ለማስያዝ ነው መዘጋጀት ያለብህ። ወደ መደወሉ ከመሄዳችን በፊት ስለ ቴክስት አንድ ወሳኝ ነጥብ ልጨምርልህ... የ‹እንገናኝ› ጥያቄ በቴክስት እንዳታቀርብ። ብዙ ጊዜ ‹እምቢ› መባልን የሚፈሩ ወንዶች ናቸው በቴክስት የሚጠይቋት። ስለዚህ ለእምቢታውም ሆነ ለእሺታው መጠየቅ ያለብህ በድፍረት ስልክ ደውለህ ነው። ከቴክስት ይልቅ በስልክ ስትጠይቅ እሺ የመባል ዕድልህ ሰፊ ነው።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

# ከመጀመሪያው መገናኘት በኋላ የሚደረግ የስልክ ጥሪ

48 ሰዓታት ፆመህ ከቆየህ በኋላ አሊያም በ24 ሰዓታት ፆምህን አፍርሰህ ቴክስት ካደረግክ በኋላ መደወልህ ግድ ነው፡፡

ሄሎ! ከማለትህ በፊት ግን አሁንም ጥሩ ጊዜና የበለጠ የሚያቀራርብ ቀለል ያለ የመነጋገሪያ ርእስ ምረጥ… ደውለህ መንተባተብ የለብህም፡፡ በተቻለ መጠን ክፍተት መፍጠር አያስፈልግም፤ ወንድም ዓለም! ስለዚህ ከመደወልህ በፊት ቀጥዩ ሁለት መልመጃዎችን አስቀምጥልሃለሁ… በደንብ ተለማመዳቸው… የመጀመሪያው መልመጃ አንተ እንድትለምደው… እንድትሆነው የምፈልገው ነው፡፡ ሁለተኛው መልመጃ ደግሞ ፍፁም ላለመሆን የምትለማመደው ነው፡፡

## መልመጃ አንድ፡ ምሽት፡ ሁለተኛው የስልክ ጥሪ

**አንተ**

‹ታዲያስ ሰብሊ›

**እሷ**

‹ሃይ በዛብህ›

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

**እኔ**

‹እዚህ ላይ ቀልድ ነገር ጣል ማድረግህ የበለጠ ቅርርብን ይፈጥራል›

**አንተ**

‹አለሁ… ናፍቆቱ እንዴት ይዞሻል?›

**እሷ**

‹አንተን ልጠይቅህ እንጂ እንዴት እያደረገህ ነው?›

**አንተ**

‹እኔማ ይኸው ደወልኩ… አንቺ ግን ለመደወል አቅም እስኪያንስሽ ድረስ ናፍቆቱ የጎዳሽ ይመስላል…›

**እኔ**

‹በጣም አሪፍ›

**እሷ**

‹ኧረ ባክህ፤ ማን ነው ያለው?›

**አንተ**

‹ባለፈው የነበረን ጊዜ ደስ ብሎኛል… ጨዋታሽ ደስ ይላል›

**እሷ**

ሀ. ‹አመሰግናለሁ›

ለ. ‹እኔም ደስ ብሎኛል›

ሐ. ‹አንተም ጨዋታ ትችላለህ›

**እኔ**

‹ለ ወይም ሐ ካገኘህ በጣም አሪፍ ነው… በመቀጠል እዚህ ላይ ባለፈው ከነገረችህ ነገሮች አንዱን አንሳላት… ምን ያህል ከልብ እንዳደመጥካት ያስረዳታል… ያስደስታታል›

**አንተ**

‹እናትሽ ከክፍለ ሃገር ተመለሱ እንዴ?›

**እሷ**

(በደስታ)

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

‹አዎ! መጣች እኮ›

**አንተ**

‹ብጣም አሪፍ... እደውልልሽና በዚህ ሳምንት መጨረሻ አካባቢ ተገናኝተን ጨዋታውን ብንቀጥለው ደስ ይለኛል›

**እኔ**

‹እደውልልሽና... ማለትህ ኳሱን ባንተ እጅ ያደርገዋል... በራስ የመተማመን ስሜት አለው... ‹ደስ ይለኛል› ማለትህ ደግሞ ስርዓት ያለህ ያደርግሃል... ጥሩ ነው›

**እሷ**

ሀ. ‹እሺ›

ለ. ‹እኔም ደስ ይለኛል›

ሐ. ‹ይመቸኛል›

**እኔ**

‹ብቃህ! ጨዋታው እየጣፈጠ እያለ አሳጥረው... አሳጥረው›

**አንተ**

‹ስላወራን ደስ ብሎኛል... በናፍቆት እንዳትሞቺ አልፎ አልፎ ደውይ... ሳቅ›

**እሷ**

‹ሳቅ... ጉረኛ›

**አንተ**

‹ሳቅ... እሺ ደህና እደሪ›

- ስልኩን ጥርቅም:: ያልተንዛዛ ... ምንም ዓይነት ስህተት ያልተፈፀመበት ፀዳ ያለ የስልክ ጨዋታ! ለማነፃፀሪያና ስህተት እንዳትፈፅም ለማስተማሪያ አንድ መልመጃ ልጨምርልህ::

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

## መልመጃ ሁለት፡ ጠዋት፡ ሁለተኛው የስልክ ጥሪ

**አንተ**

‹ታዲያስ ሰብሊ›

**እሷ**

‹ሃይ›

**አንተ**

‹እንዴት አደርሽልኝ የእኔ ቆንጆ?›

**እሷ**

‹እ...እ...እ... ደህና›

**አንተ**

‹ትላንት ከተለያየንበት ጊዜ ጀምሮ በቃ ስላንቺ ሳስብ ነበር... ለጓደኞቼም ለእናቴም ስላንቺ ነግሬያቸው በጣም ነው የወደዱሽ... እንዳውም እናቴ ቤት አምጣት ብላኛለች... ዛሬ ማታ አንገናኝም?›

**እሷ**

‹ትላንት ተገናኝተን ዛሬ?›

**አንተ**

‹አዎ፤ ምናለበት›

**እሷ**

‹አይ... አይመችኝም›

**አንተ**

‹እሺ ነገስ?›

**እሷ**

‹ነገም የምችል አይመስለኝም›

**አንተ**

‹እሺ ከነገ...

**እሷ**

‹ይቅርታ አሁን ስራ ላይ ነኝ መልሼ እደውልልሃለሁ›

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

- ጥርቅም… ተዘጋ፡፡ መቼም አትደውልም፡፡ ብትደውልላትም ላታነሳ ትችላለች፡፡ ምክንያቱም ልክ ሴት አግኝተህ በማታውቅ ዓይነት ከፍተኛ ጉጉትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነው ያናገርካት፡፡ ሴቶች እንደዚህ ዓይነት አቀራረብ ያቅለሸልሻቸዋል፡፡ ምን ለማለት እንደፈለግሁ የገባህ ይመስለኛል፡፡ ካልገባህ ወደ ላይ ተመልሰህ ሁለቱንም መልመጃዎች ከልሳቸውና በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ይገለፅልሃል፡፡ እንቀጥል…

- በመጀመሪያው ቀጠሮ ከተገናኛችሁ በኋላ 48 ሰዓታት ቴክስት ከማድረግ… ከመደወል … ፌስቡክ ላይ ‹ኢንቦክስ›፣ ‹ኮሜንት›፣ ‹ፖክ› እንዲሁም ‹ላይክ› ከማድረግ ትዊተር ላይም ተመሳሳይ ስህተቶች ከመፈፀም… ሰፈሯና መስሪያ ቤቷ አካባቢ ከማንዣበብ ተቆጥበሃል፡፡

(በነገራችን ላይ ይህን ሁሉ የምዘረዝረው ያለ ምክንያት አይደለም… አንዴ ያገኙዋትን ሴት በሁሉም ባህላዊና ዘመናዊ መንገዶች በማጨናነቅ የሁላችንንም ገፅታ ገደል የሚከቱ ወንዶች ስላሉ ነው)፡፡

አንተ ግን በሚገባ 48 ሰዓታት ከፆምክ በኋላ ወይም በ24 ሰዓት አጭር የቴክስት ልውውጥ ካደረግክ በኋላ… ደውለህ ልክ በመጀመሪያው መልመጃ እንደተገለፀው ዓይነት አሪፍ፣ አጭርና ጣፋጭ የስልክ ቆይታ በማድረግ ግዳጅህን በአግባቡ ተወጥተሃል ልበልና ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ላሳልፍህ…

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

"ከቢል ጌትስ ጋር እንዳችን የእንዳችን የነፍስ ወዳጅ መሆናችንን ያረጋገጥነው ለበርካታ ዓመታት እየተገናኘን ከተዋወቅን በኋላ ነው"

ሜሊንዳ ጌትስ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM



# ሁለተኛው መገናኘት

ሬ ንጅ ሳትረግጥ (ስህተቶችን ሳትፈጽም) እንዲሁም የሚተከሉብህን ጥይቶች (ፈተናዎች) ሽል እያልክ እያሳለፍክ... ጥሩ ነጥቦች እያስመዘገብክ እዚህ ምዕራፍ ከደረስክ በሁለተኛው ቀጠሮ በአንዱ አሪፍ የከተማችን ሬስቶራንት ውስጥ ከሴብለ ጋር ምሳ ለመብላት ትሰየማለህ፡፡

ለሁለተኛው ግንኙነት ደውሎ ቀጠሮ ማስያዝን ያለ መልመጃ ልመደው... እስካሁን ከላይ የዘረዘርኩትን ነገር ከቀልብህ ሆነህ ከተከታተልከኝ ያለ ችግር ደውለህ ቀጠሮውን ማስያዝ አያቅትህም፡፡ ስለዚህ ቅጠራችና በአንዷ ሬስቶራንት ለምሳ እንገናኝ፡፡

## ቀን፡ ሬስቶራንት ውስጥ - ሁለተኛው ቀጠሮ

ሁለተኛው ቀጠሮ ከመጀመሪያው ቀጠሮ ለየት ማለት አለበት፡፡ ለየት እንዲል የምታደርገው ደግሞ አንተ ነህ፡፡ አስታውስ ሴቷ አምሯና ተውባ ወዳንተ ለመምጣት... አንተን ለማግኘት

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ከፍተኛ ዝግጅት ታደርጋለች፡፡አንተም ለዓይን ማራኪና ባለ ጥሩ መዓዛ ሆነህ ለመገኘት መዘጋጀትህ የግድ ነው፡፡ ያንተ ዝግጅት ግን በዚህ አያበቃም… ስለምትገናኙበት ቦታ፣ ተገናኝታችሁ ስለምትሄዱበት ቦታ(ሬስቶራንት፣ ካፌ፣ ሲኒማ ቤት…)፣ ከተገናኛችሁ በኋላም ቆይታው አሪፍ እንዲሆን… መዘጋጀት አለብህ፡፡

‹አልፋ ወንድ ነው› እንድትባል የምትፈልግ ከሆነ ሁለገብ ዝግጅት አድርገህ መገኘት ይጠበቅብሃል፡፡

ሁለተኛው ቀጠሮ ከመጀመሪያው ቀጠሮ ለየት ማለት አለበት ብዬሃለሁ… ለምን በለኝ?…

ሀ. ተመሳሳይ ነገር ይደብራል … በተለይ ሴቶች ተደጋጋሚ ነገር ይሰለቻቸዋል፡፡ ያንተ ተልዕኮ ደግሞ ከእሷ ጋር አሪፍ ጊዜ ማሳለፍ ነው፡፡

ለ. ትውውቃችሁ በመጀመሪያው ቀጠሮ ከነበረበት ደረጃ ከፍ እንዲል

ሐ. የምታደርገውን ነገር (የምትወስዳትን ቦታ) እንዳትገምት፡፡ ‹ዛሬ ደግሞ የት ይሆን የሚወስደኝ?› በሚል መጓጓት አለባት፡፡ ስለ ‹ጉጉት› ብዙ አውርተናል… አስታወስክ?›

ስለዚህ ከላይ በዘረዘርኩዋቸውና በሌሎች ብዙ ስውር ጠቃሚ ምክንያቶች ሁለተኛው ቀጠሮ ምሳ ቢሆን አሪፍ ነው፡፡ በእርግጠኝነት በመጀመሪያው ቀጠሮ ላይ ከተጨዋወታችሁባቸው ቀላል ወሬዎች መካከል ስለምትወዱዋቸው የምግብ ዓይነቶች ይገኙበታል፡፡ ስለዚህ ለምሳ ስትቀጥራት የትና ምን እንደምትበሉ መጠየቅም ሆነ መንገር አይኖርብህም፡፡ ከነገርካት ‹ጉጉት› እና ‹ሰርፕራይዝ› በሚባሉ ወሳኝ ቃላት ላይ… የቃላት ማጥፋት ወንጀል ትፈፅማለህ፡፡



Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

አሁን ስብለ የምትወደው ምግብ ወደሚገኝበት… የሚጣፍጥ ምግብ በአሪፍ ጨዋታ ወደሚወራረድበት… ግርግር ወደማይበዛበት ሬስቶራንት ገብታችኋል። በዚህ ቀጠሮ ማሳካት ያለብህ ነገር ምንድነው? … ‹ዓላማ ፣ ግብና ራዕይ› በመስሪያ ቤቶች ብቻ አይደለም የሚሰራው። ስለሆነም የሁለተኛው መገናኘት ‹ዓላማ፣ ግብና ራዕይ›ን በግልፅ ማወቅ አለብህ…

**ዓላማ**

- የዚህ ቀጠሮ ዓላማ ትውውቁን ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነው። ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ደግሞ ከባለፈው የበለጠ አድማጭ፣ ተጨዋች፣ አስተዋይና አሳቢ ሆነህ በመገኘት የበለጠ ልትማርካት ይገባል።

**ግብ**

- የዚህ ቀጠሮ ግብ ሌላ ቀጠሮ እንዲወልድ… ማለትም በስብዕናህና በጨዋታህ እንድትማረክና ሌላ ጊዜም ለመገናኘት ፍላጎት እንድታሳድር ማድረግ ነው።

**ራዕይ**

- የምትለውና የምታደርገው ነገር ሁሉ እውነት እንደሆነ እንድታውቅ… ባንተ ላይ እምነት እንድታሳድርብህ… ጊዜያዊ ጥቅም ፈላጊ ሳትሆን ዘላቂ ግንኙነት የምትፈልግ ሃቀኛ ሰው እንደሆንክ አምና ለጓደኝነት ልቧን እንድትከፍትልህ ነው - ራዕይህ።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

## ዓላማ፣ ግብና ራዕይን ማሳካት

እስካሁን የመጣህበት ርቀት ቀላል አይደለም… ከመጀመሪያው ቀጠሮ ጀምሮ ጥሩ ነጥቦች እያስመዘገብክ ሁለተኛው ቀጠሮ ላይ ደርሰህ… ጥንዶች ለስለስ ባለ ጨዋታ ጥሩ ምግብ ወደሚመገቡበት ሬስቶራንት ገብተሃል። አካባቢህን ዞር ዞር ብለህ ተመልከት… ከቆንጆ ሴት አጠገብ ቁጭ ብለው የሚመገቡ ወንዶች ይታዩሃል?... እንዳንተ ዓይነት የቤት ስራቸውን በትክክል የሰሩ በጣም ጥቂት ዕድለኞች ናቸው።

በዚህ ሰዓት ብዙ ወንድሞችህ አንተ ባለህበት ቦታ ለመሆን እየተመኙ በጠራራ ፀሃይ እየተንገላወዱ ናቸው።

አትዘናና… እቺን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ ካላጠናቀቅክ አንተም ወደዛ ልትመለስ ትችላለህ።

ዓላማ፣ ግብና ራዕይህን ለማሳካት በሁለተኛው ቀጠሮ ልታደርጋቸውና ልትላቸው የሚገቡ ነገሮች…

ሀ. ትዕዛዝ ላይ እሷን አስቀድማት (ከክፍያና ከፈንጂ በስተቀር ሁሉም ቦታ እሷን አስቀድም)

ለ. በአበላልህ መጥፎ ነጥብ እንዳታስመዘግብ ተጠንቀቅ… ለአበላል የሚመችህን ምግብ እዘዝ። ምግብ አፍህ ውስጥ እያለ ከማውራትና ከመሳቅ ተቆጠብ። በፍንጣሪዎች ጉዳት እንዳታደርስባት ጥንቃቄ አድርግ። ስታኝክ አፍህን ዘግተህ መሆን አለበት። (ይቅርታ… በማንኛውም ነገር ክፍተት ፈጥረህ እንዳትወድቅ ነው)

ሐ. ምሳ ጋባዥ መሆንህን እንደ ትልቅ ነገር አትቁጠረው… ጭራሽ ቦታ አትስጠው። ጨዋታው ላይ… መገናኘቱ ላይ አተኩር።

መ. በዓለም ላይ ያለህን ትኩረት በሙሉ እሷ ላይ አድርግ። ስልክ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ማውራት፣ ቴክስት ማድረግ… እንዳታስበው። አያድርገውና ሬስቶራንቱ ውስጥ ቦንብ ቢፈነዳ እንኳን ትኩረትህን ከእሷ ማንሳት የለብህም። ምን ለማለት እንደፈለግኩ የገባህ ይመስለኛል። የምትሰጣት ያልተከፋፈለ ትኩረት ልዩ የሆነ ደስ የሚል ስሜት ይፈጥርባታል። ይማርካታል። ትኩረት ስል ግን መሽቆጥቆጥን፣ መፍራትን፣ መለማመጥን አያካትትም)።

ሠ. በመጀመሪያው ቀጠሮ ወይም በሌላ መንገድ የነገረችህን መረጃ በመጥቀስ አስገርማት ተጨማሪ ነጥብ ታስመዘግብበታለህ። ለምሳሌ አስቴር አወቀን እንደምትወድ ነግራህ ከነበረ… ‹አስቴርን እንደምትወጃት አውቃለሁ… የትኛውን አልበሟን ብሰማ ነው እንዳንቺ ልወዳት የምችለው?› በላት። ከልብ እንደምታደምጣት ያረጋግጥላታል።

ረ. አድንቃት! መንጃ ፈቃድ እንዳወጣች፣ የራሷን ስራ እንደጀመረች፣ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ለመማር እንደተመዘገበች፣ አክሱም፣ ላሊበላና ጎንደርን ጎብኝታ ጅማ፣ ሃዋሳና ሐረርን ለመጎብኘት እንዳቀደች… ዓይነት ወሬዎች ከነገረችህ አድንቃት። እንደ ቀልድ ‹አሪፍ ነው› ብቻ ብለህ እንዳታልፈው። እንዴት፣ መቼ፣ የት… እያልክ በዝርዝር እንድትነግርህ አበረታታት። ደስ ይላታል። አንተም የበለጠ ስለ እሷ ለማወቅ ዕድል ታገኛለህ።

ተ. አሁንም አድንቃት! በአለባበሷ፣ በአስተሳሰቧ፣ በአገላለጿ… አለባበሷን በምታደንቅበት ጊዜ አድናቆትህን ልብሱ ላይ ሳይሆን በእሷ የቀለም ምርጫና የፋሽን እውቀት ላይ ያተኮረ አድርገው።

- በዚህ ደረጃ ውበቷን ለማድነቅ አትጨነቅ… ውበቷን የሚያደንቁና የሚያወድሱ ብዙ ወንዶች አሉ። ጥሩ ነጥብ የምታስመዘግበው የማይታዩ ጠንካራ ጎኖችዋን እያፈላለግክ ማድነቅ ስትችል ነው

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ቸ. በአካልም ሆነ በስልክ በምታወሩበት ጊዜ አለፍ አለፍ እያልክ ስሟን መጠቀምም ጥሩ ነው። ‹ሰብሊ አንድ ነገር ልጠይቅሽ?›... ‹ዋው! ሰብሊ በጣም ጎበዝ ነሽ›... ‹ሐይ ሰብሊ!›... የጨዋታው ማጣፈጫ እንደ ቅመም በመሆን በጣም ደስ የሚል ስሜት ይፈጥርባታል።

**ማሳሰቢያ፡**

- ተሳስተህ የሌላ ሴት ስም ከጠራህ ያጠራቀምከው ነጥብ ሁሉ ድባቅ ይመታል። ኔጋቲቭ ውስጥ ትገባለህ። የሌላ ሴት ስም ከመሰጠህ የእህትህ ስም እንዲሆን እመኝልሃለሁ።

**ምርቃት**

- በሁለተኛው ቀጠሮ ለመገናኘት በምሳ ሰዓት ቀጥረህ ወደ አንድ አሪፍ... የተረጋጋ ሬስቶራንት እንድትወስዳት ተግባብተናል። ለእራት ብትቀጥራት ችኩል ሊያስብልህ ይችላል... ችኩልነትም ነው። የምሽት ቀጠሮ አላስፈላጊ ፍርሃትና ጥርጣሬ ሊፈጥርባትም ይችላል። ስለዚህ ዘለህ ለእራት ቀጠሮ አለመጠየቅህ ጥሩ ነጥብ እንድታስመዘግብ ያስችልሃል። ነገር ግን አንተ ለምሳ ስትቀጥራት እሷ ‹ማታ ነው የሚመቸኝ... እራት ይሁንልኝ› ካለችህ የደስታ እጣን አስጭስ... መድፍ አስተኩስ!

ይህ ማለት ግን ወደፈለከው ቦታ ወስደህ የፈለግከውን ታደርጋለህ ማለት አይደለም። ከእራትና ከአሪፍ ጨዋታ በኋላ ወደ ቤቷ ትሸኛታለህ። እያወራን ያለነው ወደፊት ሚስትህ... የልጆችህ እናት... የህይወትህ አጋር ልትሆን ስለምትችል የተከበረች ሴት ነው። ስለዚህ ለእሷና እውነተኛ ፍቅር ለሚጠይቀው ሂደት ተገቢውን ክብር ስጥ።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

# ሦስተኛው መገናኘት

የዓለማችን ጥቂት አሪፍ ወንዶች… ፈታኝና አሳሳች የሆኑ ስሜቶችን ተቋቁመው… አልፈው የሚደርሱበት ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሰሃል:: አሁንም እንኳን ደስ አለህ:: በሁለተኛው መገናኘት ምሳ እየበላችሁ ብዙ ተጫውታችኋል… ተግባብታችኋል ብዬ እገምታለሁ:: ስለሆነም ከምሳው በኋላ ለምታደርጉት የስልክና የቴክስት ጨዋታዎች መነሻ የሚሆኑ በርካታ የወሬ ርእሶች አግኝተሃል:: እናም ከሁለተኛው መገናኘት በኋላ የስልክና የቴክስት ግንኙነቱ በፊት ከነበረው ይጨምራል:: ምክንያቱም ቅርርባችሁና ትውውቃችሁ ስር እየሰደደ ስለሆነ የቴክስትና የስልክ ጨዋታው መጠንም ጨምሮ ግንኙነቱን ወደ ቀጣዩ… ከፍ ያለ ደረጃ መድረስ አለበት::

ልብ በል የስልክና የቴክስቱ ጨዋታ ግንኙነቱን ማጠናከር እንጂ ማላላት የለበትም:: ይህ ማለት ስልኩና ቴክስቱ ከመጠን ማለፍ … ማሰልቸት የለበትም:: ከላይ እንዳስቀመጥኩት ቴክስት ስታደርግ ምላሽ ካላገኘህ ደግመህ ቴክስት ማድረግ የለብህም:: ለቴክስቶችህ የምትሰጥህ ምላሽ በጣም አጭርና ጨዋታውን ለመቀጠል የማይጋብዝ ሆኖ ከተሰማህ ፍሬን ያዝ:: ‹Eshi, K, Tnx, Me Too…› ዓይነት መልሶችን ማለቴ ነው::

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ግንኙነቱ ወደዚህ ዓይነት ደረጃ ከወረደ መቀጠሉ በጣም አስጊ ነው። ስለዚህ ከመጀመሪያው ጀምሮ የስልክና የቴክስት ጨዋታውን በሁለታችሁ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ወደሚሆንበት ደረጃ ማሸጋገር አለብህ።

ሁልጊዜ ደዋይና ቴክስት አድራጊ አንተ ብቻ መሆን የለብህም።

በዚህ ከተስማማን ዘንዳ ወደ አንጊውና አዝናኙ... ሦስተኛው መገናኘት እንሂድ። ሦስተኛው ቀጠሮ እራት፣ ሲኒማና የእግር ጉዞን (ምክ) ያካተተ ቢሆን ይመረጣል። ሦስቱንም ማድረግ ካልተቻለ ሁለቱን ማከናወን ግድ ነው። ምክንያቱም ይህ ቀጠሮም ዓላማ፣ ግብና ራዕይ አለው።

በዚህ ቀጠሮ ልታሳካቸው የሚገቡ ነገሮች... ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ፣ ናፍቆት መጠጣትና የበለጠ መቀራረብን ናቸው።

በአንደኛውና በሁለተኛው መገናኘት ያደረግካቸውና አሁንም ልታደርጋቸው የሚገቡ ወሳኝ ነገሮች አሉ... አንዴ እንከልሳቸው...

- እሷን ማግኘት ማለት ልክ የምትወደውን ዓመት በዓል እንደማክበር ቁጠረው። ስለዚህ አስፈላጊውን ዝግጅት ሁሉ አድርግ። ወረተኛ እንዳትሆን ተጠንቀቅ። ልክ እንደመጀመሪያውና ሁለተኛው ቀጠሮ አሁንም በንፁህና ጥሩ መዓዛ ባለው አለባበስ ቀድመህ በቀጠሮ ቦታው ተገኝ።

- አስደሳችና አሪፍ ጊዜ እንዲኖራችሁ አስቀድመህ አቅድ። ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ፣ ናፍቆት መጠጣትና የበለጠ መቀራረብ... በዚህ ቀጠሮ ልታሳካቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮች ሲሆኑ ሲኒማ፣ እራትና የእግር ጉዞ ጉዳዮችህን የምታሳካባቸው መንገዶች ናቸው

## ሲኒማ

- በሁለታችሁ ግንኙነት ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የማይፈጥር

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

አዝናኝ ፊልም ያለበት ሰዓትና ሲኒማ ቤት ምረጥ። ፊልሙ ከሚጀምርበት ሰዓት ቀደም ብላችሁ እንድትገናኙ አድርግ። ተረጋግታችሁ... ፊንዲሻ ገዝታችሁ እንጂ ተጣድፋችሁና ተሯሩጣችሁ መግባት የለባችሁም። እያንዳንዷን ቅፅበት ልታጣጥሚትም ይገባል። የፍቅር ታሪክ እየፃፋችሁ መሆኑንም አትርሳ... ምናልባት መዋደዱ... መፋቀሩ ስር ሰዶ ወደ ትዳርና ቤተሰብ ልታመሩ ትችላላችሁና።

- ዛሬ አንተ ላይ እምነት የምትጥልበት ቀን ነው... ስለዚህ አንተን አምና ካንተ ጋር ውጭ ለማምሸት መወሰኗ ትክክል እንደሆነ ልታረጋግጥላት ይገባል... ታማኝ በመሆን። ታማኝነትህና ጨዋነትህ ከፍተኛ ነጥብ ያስጥሃል።

- ሲኒማ ቤት የምትወስዳት ፊልም እንድታይ ነው። አለቀ። ጨለማን ተገን አድርገህ ለማቀፍ... ለመሳም... በፍፁም እንዳትሞክር። አንደኛ ገና ለመሳሳም አልደረስክም... ሁለተኛ የጨለማውን አጋጣሚ ተጠቅመህ ለመሳም... ለመዳበስ መሞከርህ እስገድዶ እንደመድፈር ይቆጠርብህና ግንኙነቱን አደጋ ላይ ትጥለዋለህ። አሪፍ ወንድ አይቸኩልም... ሁሉንም ነገር የሚያደርገው ትክክለኛ ሰዓቱን ጠብቆ ነው። ስለዚህ ፊልሙ በሚታይበት ጊዜ ሙሉ ትኩረትህን ፊልሙ ላይ አድርግ። ፊልም እየታየ ማንሾካሾክና ማውራት ተመልካቾችን የሚረብሽ መጥፎ ባህሪ ነው። እንዳትሞክረው።

## እራት

- ስለምትሄድበት ቦታ አስቀድመህ ማቀድ እንዳለብህ ከአንድም ሁለት ጊዜ ነግሬሃለሁ። አሁንም ላስታውስህ... አስቀድመህ ማሰብህና ማቀድህ ከመደናበርና ግራ ከመጋባት ያድንሃል። ብዙ ጊዜ ከምንፈልጋት ከምንወዳት ሴት ጋር ስንሆን አዲስ አበባ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ትጠብብናለች... የምናውቀው ቦታ ሁሉ ይጠፋብናል። ስለዚህ አስቀድመህ አቅድ።

- የምትወስዳት ቦታ ጥራትና ውበት ራሱ ነጥብ ያስጣል። ለሬስቶራንቱ ውድነት አትጨነቅ። ለጥሩ ምግብና አሪፍ ጨዋታ የሚመች ደስ የሚል ቦታ መሆኑን ብቻ አረጋግጥ። ሌላ ጊዜ የማታደርገው... ከአቅምህ በላይ የሆነን ነገር ለማድረግ አትሞክር።

- ከሲኒማ ቤት ወጥታችሁ አስቀድመህ ወዳቀድከው ሬስቶራንት ሄዳችሁ ስትመገቡ ዋናው የጨዋታችሁ ርእስ ባያችሁት ፊልምና በአጠቃላይ ስለ ፊልም ሊሆን ይችላል። ጨዋታውን እንድትመራው ጥያቄዎች እየጠየቅክና እያደመጥክ አበረታታት።

## የእግር ጉዞ (ምክ)

- ጫማዋና ጊዜዋ የሚፈቅድላት ከሆነ አጭር ርቀትም ቢሆን አብራችሁ የእግር ጉዞ አድርጉ። ቤቷ ገብታ ስላንተ ታስብ... ታሰላስል ዘንድ በእያንዳንዷ እርምጃ... በጥሩ አድማጭነትና ለዛ ባለው ጨዋታ ታሪክ ስራ።

ምንም ዓይነት የጥርጣሬና የፍርሃት ስሜት ሳይሰማት ይልቁንም አዝናንተህ በጨዋ ደንብ ወደ ቤቷ ከሸኘሃት... ሦስተኛው መገናኘት ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ተጠናቋል ማለት ነው።

በአንደኛውና በሁለተኛው ቀጠሮዎች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን መሰናክሎች አልፈህ ሦስተኛው ላይ ደርሰህ... ሦስተኛውም እንከን የለሽ ሆኖ አለፈ። ብራቮ!

ሦስተኛ መንጃ ፈቃድ እንዳወጣህ ቁጠረው። ሦስተኛ መንጃ ፈቃድ ከያዝክ ደግሞ ማንኛውም ዓይነት መኪና መንዳት ትችላለህ ማለት ነው።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

በዚህ ስኬታማ ሂደት ሦስተኛውን መገናኘት ማጠናቀቅም ከማንኛውም ሴት ጋር መልካም ግንኙነት የመፍጠር ችሎታ እንዳለህ ያረጋግጣል።

## ምርቃት

- ሴቶች ጨዋታ ለሚችሉ ወንዶች ልዩ ቦታ ይሰጣሉ… ለተጨዋች ወንዶች በቀላሉ እጅ ይሰጣሉ… ይማረካሉ። ስለዚህ በተገናኛችሁ ቁጥር ከተቻለ የሚያስቁ ካልሆነ ደግሞ ዘና… ፈገግ የሚያደርጉ ጨዋታዎች ማቅረብ ይጠበቅብሃል። በተፈጥሮ ማሳቅ…ማዝናናት የምትችል ሰው ከሆንክ እንኳን ደስ አለህ። ካልሆንክም ችግር የለም… ትንሽ ጥረት ማድረግ ብቻ ነው የሚጠበቅብህ። የሚያስቁና የሚያዝናኑ ቀልዶች፣ ወሬዎች፣ ዜናዎች መከታተል… ማደን ይኖርብሃል።

- እሷ የምታወራቻውን ወሬዎች ከልብ በማዳመጥ… በሚያስቁ ወሬዎች ላይ መሳቅ ደግሞ ካንተ ማሳቅ በላይ ከፍተኛ ነጥብ ያስጥሃል። ቀጥለህ ስለምትናገረው ነገር ስታስብ እሷ የምትነግረህን አስቂኝ ነገር ሳታዳምጥ… ሳትስቅ ካመለጠህ ክፉኛ ትጎዳለህ። ነጥብ ይጎመድብሃል። ስለዚህ ለማውራት… ለማሳቅ ስትጨነቅ የሚያስቅ ጨዋታ እንዳያመልጥህ ጥንቃቄ አድርግ። ከልብ አድምጥ። አስቀህ ማስደሰት ካልቻልክ ስቀህ ማስደሰትም ትችላለህ።

- አንዴ ማሳቅ… ምግብ፣ መጠጥና ፊልም ከመጋበዝ የበለጠ ነጥብ ያስገኛል። ግልፅ ላድርግልህ… ምግብ፣ መጠጥና ሲኒማ አንድ ላይ ተደምረው ከሚያስጡህ ነጥብ የበለጠ አንዴ ማሳቅ የተሻለ ነጥብ ያስመዘግብልሃል። ለጨዋታ ምን ያህል ግምት ልትሰጠው እንደሚገባ በሚገባ ግልፅ ያደረግኩልህ ይመስለኛል።

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

# ግንቡ ይፍረስ... ይናድ! የመነካካት ጥበብ!

“... እጇን ይዞ ለማስገባ... ክንዱ ትከሻዋን፣
ቀኝ እጁ ቀኝ እጇን፣ ትኩስ ትንፋሹ ጆሮዋን፣ አንገትዋን ሲነካት...
ሙቀት እንደ ኤሌክትሪክ በሰራ አካላትዋ ጎርፎ አጋላት...
ያ ውብ አካላትዋ ከማር ሰፈፍ እንደተሰራ... ትንሽ በትንሽ
መቅለጥ... ትንሽ በትንሽ መፍሰስ ጀመረ። ሰውነትዋን መግዛት፣
በሰውነትዋ ማዘዝ አቃታት...”

ፍቅር እስከ መቃብር (መጽሐፍ)

ልብ ብለህ ከሆን እስካሁን ድረስ ከአምስቱ የስሜት ህዋሳት ያተኮርነው ሦስቱ ላይ ነው ... ማየት፣ መስማትና ማሽተት ላይ ብቻ። እስካሁን ውበቷን አይተሃል፣ መዓዛዋን አሽትተሃል፣ እንዲሁም ለዛ ያለው ጨዋታዋን ሰምተሃል። አሁን ደግሞ ከተቀሩት ሁለት የስሜት ህዋሳት ማለትም ከመዳበስና ከመቅመስ ጋር የምትተዋወቅበት ጊዜ ነው።

መዳበስና መቅመስ ልክ እንደ ማዳመጥ፣ ማሽተትና ማየት ቀላል አይደሉም። ለመዳበስና ለመቅመስ ከመንቀሳቀስህ በፊት ሁለት ነገሮች ላይ እርግጠኛ መሆን አለብህ።

አንደኛ በመካከላችሁ የተገተረውን ፀረ-መዳበስና ፀረ-መቅመስ ግንብ

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

ማፍረስ አለብህ፡፡ ግንቡን መናድ ስትችል ብቻ ነው መዳበስም ሆነ መቅመስ የምትችለው፡፡ ግንቡን መናድ ደግሞ ለብዙ ወንዶች አስቸጋሪ የቤት ስራ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የመጀመሪያውን ማለትም ግንቡን የማፍረስ ስራ የሚያቀልልህ ሲሆን እሱም ‹በእሷ በኩልስ ግንቡ እንዲፈርስ ይፈለጋል ወይ?› የሚል የማረጋገጥ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ሁለቱም ላይ አተኩረን እንነጋገርና ግንቡን አፍርሰን ሁለታችሁም በሁለቱም የስሜት ህዋሳት እንድትዋሃዱ የማድረግ ስራ እንስራ፡፡

## ግንቡ እንዲናድ ትፈልጋለች ወይስ አትፈልግም?

ስልክ ቁጥሯን ሰጥታህ... በመጀመሪያው፣ በሁለተኛውና በሦስተኛው ቀጠሮዎች መጥታ ጥሩ ጊዜ ካሳለፋችሁ... በመካከልም መደዋወሉና ቴክስት መደራረጉ ተፋፍሞ... መገናኘቱ ቀጥሎ ዓርብና ቅዳሜ ምሽቶችን ቅድሚያ ላንተ መስጠት ከጀመረች... ምን ትጠብቃለህ?

ይህን ያህል ርቀት በደስታ አብራህ ከተጓዘች ግንቡ እንዲናድ ፍላጎት አላት ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ስለዚህ በልበ ሙሉነት... በራስ በመተማመን ስሜት ግንቡን ናደውና አካል ለአካል ተቀላቀል፡፡

‹አካል ለአካል ተቀላቀል› ስል ታዲያ ወደዛ ወደሚጣፍጠው ነገር ዘለህ ገብ ትላለህ ማለት አይደለም... አካል ለአካል ስል መነካካቱን ማለቴ ነው፡፡ አሁን በመካከላችሁ የተገነባውን ግንብ እናፍርስ...

## ግንቡን ለመናድ ምን ምን ማድረግ አለብህ?

በመካከላችሁ ያለው ፀረ መነካካትና ፀረ መሳሳም ግንብ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

የሚፈርሰው በአንድ ጊዜ በጉልበት ሳይሆን ቀስ በቀስ በታላቅ ጥበብ ነው፡፡

ነክተሃትና ነክታህ የማታውቅን ልጅ በአንዴ ልትስማት አትችልም፡፡ ያንን ማድረግ የሚከለክልህ እውነታን ነው ‹ግንብ› የምለው፡፡

እናስ? ግንቡን ለመናድና ከግንቡ ጀርባ ያሉትን ጣፋጭ ነገሮች ለማግኘት ዝግጁ ነህ?... ምን ጥያቄ አለው!

ግንቡን ለማፍረስ ልትጠቀምባቸው የሚገቡ የጥበብ መዶሻና ዶማ የሚከተሉት ናቸው...

### ሀ. በጨዋታ መሃል ቸብ አድርጋት

- ‹ቸብ አድርጋት› ስል ምን እንዳሰብክ ይገባኛል፤ ግን ይቅር ብዬሃለሁ፡፡ ያንን የተከበረና የተወደደ የሰውነቷን ክፍል ‹ቸብ ለማድረግ› ገና በጣም ብዙ ይቀርሃል፡፡

  ቁጭ ብላችሁም ሆነ እየሄዳችሁ በምታወሩበት ጊዜ የሆነ የሚገርም ወይም የሚያስቅ ነገር ስትነግርህ ባለማመን ወይም በጣም በመገረም ዓይነት እጇ ላይ ቸብ አድርጋት፡፡ የማይታመን ነገር ከነገረችህ ደግሞ እየሳቅክ ‹እውነት?› ብለህ እንድትምልበት እጅህን ዘርጋላት፡፡ መነካካት ተጀመረ ማለት ነው፡፡

### ለ. እጅህን ዘርጋላት

- ከታክሲ ወይም ከመኪና በምትወርድበት ጊዜ አንተን ይዛ ዘና ብላ እንድትወርድ እጅህን ዘርጋላት፡፡ ይህ አጋጣሚ ከፍ ያለ ደረጃ በምትወጣበት ወይም ቱቦ መሰል ነገር በምትሻገርበት ጊዜም ልትጠቀምበት ትችላለህ፡፡ በአንድ ድንጋይ ሰባት ወፍ የምትገድልበት አጋጣሚ ነው፡፡ ከመነካካት የሚገድብህን ግንብ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

ታፈርስበታለህ፤ እንዲሁም ትህትናህንና ጨዋነትህን ታሳይበታለህ፡፡

## ሐ. ቅድሚያ ስጣት

- ቅድሚያ ስለመስጠት ቀደም ሲል ተነጋግረናል፡፡ ስለዚህ የትም ቦታ ስትገቡ ቅድሚያ ለእሷ እንደምትሰጣት ታውቃለህ፡፡ ቅድሚያ በመስጠትህ ነጥብ ታስመዘግብበታለህ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ ፀረ መነካካት ግንቡንም ታፈርስበታለህ፡፡ እንዴት?...

  የትም ቦታ ቆም ብለህ ቅድሚያ ስትሰጣት በእጅህ ጀርባዋን ነካ ወይም ገፋ በማድረግ የመንካት ግዳጅህን ትፈፅማለህ፡፡ እዚች ላይ ለጥንቃቄ ያህል አንድ ነጥብ ልጨምርልህ... መቀመጫዋን እንዳትነካ፡፡

  ‹እሺ መነካት ያለበትን ትክክለኛ ቦታ አክብብልኝ› ካልከኝ... በመቀመጫዋና በጀርባዋ መካከል የምትገኝ ጎድጎድ ያለች ስፍራ አለች... እም፤ እሷ ላይ ነው ነካ... ወይም ገፋ በማድረግ የምታስቀድማት፡፡

## መ. አልብሳት

- ጃኬት ወይም ኮት ለብሳ ስትመጣ... ካፌ፣ ሬስቶራንት ወይም ሲኒማ ቤት እንደገባች ሲሞቃት አሊያም ዘና ለማለት ልታወልቀው ትችላለች፡፡ አንተም ‹ዘና እንድትይ አውልቂው› ብለህ ሳሳ ያለ ማበረታቻ ልትሰጣት ትችላለህ፡፡ ማውለቅ ካልፈለገች አታስገድዳት፡፡

  በራሷ ጊዜ ወይም ባንተ ማበረታቻ ካወለቀች ግን በኋላ መልበስ በምትፈልግበት ሰዓት ጃኬቷን/ ኮቷን አስተካክለህ ከኋላ አልብሳት፡፡ ስታለብሳት ጃኬቷ/ኮቷ ፀጉሯ ላይ ያርፋል፡፡ ይሄኔ ነው እጅህን በፀጉሯና በአንገቷ መካከል አስገብተህ በጃኬቷ/በኮቷ

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

የታፈነውን ፀጉሯን ነፃ የማውጣት ኦፕሬሽን የምታካሂደው፡፡

‹ፀጉር ከሌላትስ?›… አታስብ እድሜ ለ‹ሂዩማን ሄር› በአሁኑ ሰዓት 99.9% ሴቶች ረዥምም ፀጉር አላቸው፡፡ ፐርሰንቱን ካጋነንኩት ቀንሰው፡፡

ጃኬቷ/ኮቷ ያረፈበትን ፀጉር ከውስጥ ለማውጣት በምታደርገው ጥረት ሁለት በጣም ወሳኝና ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ የሰውነቷ ክፍሎችን ትነካለህ - ፀጉሯንና አንገቷን፡፡

## ሰ. የሆነ ነገር አሳያት

- መፅሔት ላይ ወይም ሞባይል ስልክህ ላይ ያለ ፎቶ… ቀልድ ሊሆን ይችላል ወደ እሷ ቀረብ ብለህ አሳያት፡፡ ስለምታሳያት ነገር ድምፅህን ዝቅ አድርገህ አስረዳት… አብራራላት፡፡ ሁኔታው ለመጠጋጋት፣ ትንፋሽ ለትንፋሽ ለመለዋወጥና እጅ ለእጅ ለመነካካት ዕድል ይፈጥራል፡፡

## ረ. አብራችሁ ምግብ አብስሉ

- ብቻህን የምትኖር ከሆነ ወይም እሷ ብቻዋን የምትኖር ከሆነ አንድ ላይ ምግብ አብስላችሁ ምሳ የምትበሉበትን ሁኔታ አመቻች፡፡ ቤትህ እንድትመጣ ወይም አንተ ቤቷ እንድትሄድ በጣም አሪፍ አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡

አብራችሁ በምታበስሉበት ወቅት ደግሞ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችና የማብሰያ ቁሳቁሶች የመቀባበል ሁኔታ ይኖራል፡፡ ያው ምግብ ያለ ሽንኩርት አይሰራም… ሽንኩርት ካለ ደግሞ ማንባት ግድ ነው፡፡ ማንባት ካለ ደግሞ በሶፍት ዕንባ የመጥረግ ዕድል ይፈጠራል፡፡

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

- ግንቡን ለመናድ ጠቃሚ የሆኑ ዘዴዎች ተዘርዝረውልሃል...

ሁሉንም በደንብ አጥናቸውና አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ ተጠቀምባቸው። አጋጣሚዎቹ ራሳቸው ካልተፈጠሩ ደግሞ ራስህ ፍጠራቸው። በዚህ መልኩ በመካከላችሁ የተጋረደውን ግንብ ደርምሰውና የመነካካት፣ እጅ ለእጅ የመያያዝና የመተቃቀፍ ነፃነትህን አውጅ።

Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

‘ ከጭንቀትና ከስቃይ ነፃ ሊያወጣን የሚችል
አንድ አስማተኛ ቃል አለ፤ እሱም ‹ፍቅር› ነው ’

የአፍሪካ አባባል

Scanned by CamScanner
@BOOKALEM




Info

t.me/BookAlem

Invite Link

@BOOKALEM